
«ማኅበረ ቅዱሳን»
እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣
የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣
ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን
ስያሜ አግኝቷል።



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰ/ት/ቤቶች ማ/መ
ማኅበረ ቅዱሳን ኅትመት
ሚዲያ መምሪያ የሚታተም
ትምህርታዊ መጽሔት

# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ
ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣
ሥርዓተ እምነትና
ክርስቲያናዊ ትውፊት
ጠብቆ የሚወጣ

፳፱ኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
ሐምሌ ፳፻፲፬ ዓ.ም.

ም/ዋና አዘጋጅ፡-
*ዲያቆን አሻግሬ አምጤ*
አድራሻ፡- የካ ክፍለ ከተማ
*ወረዳ 01/02 የቤት ቍጥር 521/522*
*+251- 911361580*
ከፍተኛ ሪፖርተር፡-
*ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን*
*ኮፒ አርታዒ፡-*
*ቀሲስ ልዑል ታመነ*
የገጽ መልክእ ባለሞያና ጸሐፊ፡-
*ገነት ታደሰ*

አሳታሚ በማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት አስተዳደር
*አ.አ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06*

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ፡-
*+251-118-124222*
*ፖ. ሣ. ቍ.80078*
*magazine@eotcmk.org*

የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት አድራሻ፡-
*+251-962 17 17 17*

የልማት ተቋማት ሽያጭና ስርጭት መምሪያ
*0111 54 04 84/24 61 84/944 25 90 14*

የገበያ ጥናት ልማት መምሪያ
*0111 26 65 49*

*የማስታወቂያና የገበያ ጥናት ባለሞያ*
*ጌዴዎን አክሊሉ*
*09 44 25 90 26*

# ማውጫ

**መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን**
ለሰላም ዘብ እንቁም ፤ ለተጎዱትም እንድረስላቸው............... ፪

**ዐውደ ስብከት**
የተለያየ ዘር አትዝራ (ዘሌ.፲፱፥፲፱)........................... ፬

**ትምህርተ ሃይማኖት**
ደመናውንም ከላይ አዘዘ (መዝ.፸፯፥፳፫)...................፯

**ዐቢይ ጉዳይ**
ሰላም እንዲሰፍን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ድርሻችንን እንወጣ .... ፲

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
የተዘነጋውን የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ እንደ ገና ማጠናከር..... ፲፬

**እናስተዋውቃችሁ**
ከወላይታ ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት እስከ
ጦመ ግራር....................................................... ፲፯

**የነገዋ ቤተ ክርስቲያን**
ሊመጣ ካለው ፈተና ለማምለጥ የአኃት አብያተ ክርስቲያናት
አንድነት የሚኖረው ሚና.............................................. ፳

**ኪነ ጥበብ**
ከዓይን ጋር የተገባ ቃል ኪዳን.................................... ፳፫

**የጥያቄዎቻችሁ መልስ**
.....................................................................፳፮

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።*

# ለሰላም ዘብ እንቁም ፤ ለተጎዱትም እንድረስላቸው

የሰው ልጆች ሁሉ ለሰላም ዘብ ካልቆሙ፣ አንዱ ሲጎዳ ሌላው በፍጥነት ደርሶ ኀዘኑን ካልተካፈለው ሰው የመሆን ምሥጢሩ ምንድን ነው ከሚያሰኝበት ዘመን ደርሰናል። የሰላም ዋጋው የሚታወቀው የታጣ ጊዜ መሆኑን ባለፉት አራት ዓመታት በገሃድ አይተነዋል። ሁላችንም የጥፋቱን ምንጭ ወደ ሌላ ስለምንጠቁም መፍትሔ ማምጣት አልተቻለም። ሰዎች ለመከራ ሲዳረጉ ፈጥነን ከችግር ለመውጣት ከመሞከር ይልቅ ምክንያት በመደርደር ጊዜያችንን እናጠፋለን። እንዲህ መሆኑ ደግሞ ችግሩ እየሰፋ፣ ይበልጥ እየተወሳሰበ እንዲሄድ አድርጎታል።

ችግር በችግር ላይ እየተደራረበ እያየንም ልቅሷችን ማንነትን ዓይተን፣ ዘር ቈጥረን እየሆነ መምጣቱ ከሰብአዊነት እያወረደን ነው። ኢትዮጵያውያን የምንታወቀው በመከባበር እና በመደጋገፍ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መልካችን ተለውጦ እርስ በርስ በመጠፋፋት እንታወቅ ጀምረናል። በዚህ ዘመን ማከናወን የሚገቡን ሁለት ተያያዥ እና ተደጋጋፊ ተግባራት ናቸው። የመጀመሪያው ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለሰላም ዘብ መቆም ነው። በዚህም አንዳችን ለሌላችን መከታ እየሆንን የአጥፊዎችን ጥቃት መቀነስ ቀስ በቀስም ጨርሶ ማቆም እንችላለን። ሌላኛው ተግባር  የተጎዱትን መደገፍ ነው። የተጎዱትን መደገፍ ሰብአዊ ርኅራኄ ብቻ ሳይሆን አምላካዊ ትእዛዝም ነው። የሰዎች በጎ ምግባር የሚገለጠው ለተጎዱ ወገኖቻቸው በሚያሳዩት ርኅራኄ እና በሚያደርጉት ድጋፍ ነው። አምላካችን በተራብኩ ጊዜ አብልታችሁኛል የሚለን በልዩ ልዩ ምክንያት ከቀያቸው የተፈናቀሉትን ስንደግፍ፣ የጥፋት ተባባሪ እና የአጥፊዎች መጠቀሚያ ላለመሆን ስንጠነቀቅ ጭምር ነው።

የሩቁን እንተወውና ሐምሌ ፳፰ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም ጅግጅጋ ይኖሩ በነበሩ ክርስቲያኖች ላይ ጥቃት ማድረስ ከጀመረ አንሥቶ ብዙ ክርስቲኖች መተኪያ የሌለውን ሕይወታቸውን፣ ለፍተው ያጠራቀሙትን ጥሪታቸውን አሳጥቶ አገር ለቀው እንዲሰደዱ ማድረጉ ይታወቃል። ከተጠቀሰው ዕለት ጀምሮ በክርስቲኖች ላይ ሲፈጸም የኖረው ለሰሚው ግራ የሚያጋባ ነበር። ልቅሶም ማንነት እየታየ በመሆኑ የዓለም ማኅበረሰብእ እንኳ የክርስቲያኖችን ሞት አይቶ እንዳላየ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ ያልፈው ነበር። አስቀድሞ ክርስቲኖችን ብቻ ዒላማ አድርጎ የነበረው ግድያ፣ ንብረት ውድመት እና ስደት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ተጨማሪ የሰዎች ማጥፊያ መስፈርት ወጥቶለት ጥቃቱና ጥፋቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ከኀምሳ እና ስድሳ ዓመታት በፊት እንደ ቀልድ ሲቀነቀን መፍትሔ ያላበጀንለት ዘረኝነት ዛሬ ፍሬውን እያጨድን ነው። በዚህ ምክንያት ወገን ወገኑን ካለማመን ደረጃ ደርሷል። በዚህ ከቀጠልን መጨረሻችን ምን እንደሚሆን መናገር ነቢይነትን አይጠይቅም። ዘረኝነት መዳረሻው እልቂት መሆኑን ቤተ ክርስቲያን እንደምታስተምር የተረዱት አጥፊዎች እርሷን እያንቋሸሹ ጥፋታቸውን ሲቀጥሉ አይተን እንዳላየን፣ ሰምተን እንዳልሰማን ስለተውነው ዛሬ መዋቅር ተጠቅመው የሚያጠቁ አካላት ካሉበት የዝቅጠት ደረጃ ደረስን። አገራችን ኢትዮጵያ ዳር እስከ ዳር በመከራ ተወጥራ እያየን ቢሆንም የምንወስደው መፍትሔ ችግሩን ከሥሩ የሚነቅል ሳይሆን ችግሩን የሚያባብስ፣ በእሳት ላይ ቤንዚን የሚጨምር በመሆኑ አገራችን ሰላም ውላ እንድታደር ከዚህ ድርጊታችን እንድንቆጠብ ማስገንዘብ እንወዳለን።

የሚገርመው እየደረሰ ያለውን መከራ በአስተማማኝ መረጃ በአኃዝ አስደግፈው የሚያቀርቡ አካላት ቢኖሩም መረጃውን ተቀብሎ አስተማማኝ ሰላም ለማምጣት የሚሠራ አካል አለመኖሩ ነው። ወደድንም ጠላንም በዚህ ጊዜ የሚያስፈልገን ኢትጵያውያን ሁሉ ያለምንም ልዩነት ተባብረን አስተማማኝ ሰላም የሚመጣበትን ተግባር መፈጸም ነው። በዘር የተደራጀው ፖለቲካችን አንዱን አንሥቶ ሌላ በተካ ቍጥር እርስ በርስ እየተጠፋፋን እስከ መቼ እንደምንቀጥል የሚያውቁት የርዕዮተ ዓለሙ አቀንቃኞች ናቸው። የሚበጀን ጥፋቱንም፣ ጥላቻውንም አንድ ቦታ ላይ በቃ ብለን የተጎዱትን እየጠገንን ያልተጎዱትን እየጠበቅን መጓዝ ነው።

በሰው ልጅ ላይ መከራ እንዳይደርስ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት በቅዳሴዋ "እግዚአብሔር ይቅርታ ባለው ቀኝ መርቶ በፍቅርና በደኅንነት ወደ ማደሪያቸው ይመልሳቸው ዘንድ በባሕርና በደረቅ ስለሚሔዱ ሰዎች እንማልዳለን:: እግዚአብሔር የዕለት የዕለት ምግባቸውን ይሰጣቸው ዘንድ ስለ ተራቡና ስለ ተጠሙ ሰዎች እንማልዳለን:: እግዚአብሔር ፈጽሞ ያረጋጋቸው ዘንድ ስለ አዘኑና ስለ ተከዙ ሰዎች እንማልዳለን:: እግዚአብሔር ከእሥራታቸው ይፈታቸው ዘንድ ስለ ታሠሩ ሰዎች እንማልዳለን:: እግዚአብሔር በሰላም ወደ አገራቸው ይመልሳቸው ዘንድ ስለ ተማረኩ ሰዎች እንማልዳለን:: እግዚአብሔር ትዕግሥትን፣ በጎ ትምህርትንም ይሰጣቸው ዘንድ የድካማቸውንም ፍጹም ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ ስለ ተሰደዱ ሰዎች እንማልዳለን" የምትለው በሰው ልጅ ላይ የሚደርሰው መከራ ይቆም ዘንድ ነው (መጽሐፈ ቅዳሴ ገጽ ፳፪)::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት ወደ ፈጣሪዋ ጸሎትና ተማጽኖ የምታቀርበው ለሰው ልጅ ሁሉ እንጂ ለተወሰኑ አካላት አለመሆኑን በተግባር ከሚገልጡ አስተምህሮዋ አንዱ ይህ ነው:: በዚህ ጸሎቷ ምልጃ ያቀረበችው የሃይማኖት ልዩነት ሳታደርግ ለሰው ልጅ ሁሉ ነው:: ቅዱሳን ወደ ፈጣሪያቸው ጸሎት የሚያቀርቡት ዓለም ሁሉ ድኅነት ያገኝ ዘንድ እንጂ አንዱ ተርፎ ሌላው ይጠፋ ዘንድ አለመሆኑን መረዳት የሚገባው እንዲህ ያለውን ጸሎቷን ቀርቦ በመሳተፍ ነው:: ሰሞኑን ለደረሰው ጅምላ ጭፍጨፋ አስተማማኝ መፍትሔ እንዲፈለግለት ያሳሰበችውም ለሰው ልጅ ሁሉ ስለምታዝን ነው::

አስቀድሞ የተጠቀሰው ጸሎት በዚህ ዘመን ለምንገኝ የሰው ልጆች ሁሉ የሚያስፈልገን፣ ይልቁንም እየተመረጡ ለሞት የተዳረጉ ወገኖቻችንን አምላካችን በምሕረቱ እንዲጎበኝ እና ለአገራችን ሰላም እንዲሰጣት ነው:: በሁሉም አካባቢዎች በሚባል መልኩ ኢትጵያውያን ዕለት ዕለት መከራ ቢዘንብባቸውም መፍትሔ የሚሰጣቸው፣ ከሞት የሚታደጋቸው፣ ቢሞቱ እንኳ በአግባቡ የሚቀብራቸው በጠፋበት በዚህ ክፉ ዘመን ስለ ስዱዳን መጸለይ ቀዳሚው የቤተ ክርስቲያን ተግባር በመሆኑ የተጎዱትን በመርዳት ጭምር እንጂ በቃል በመናገር ብቻ አለመሆኑን መረዳት ይገባል::

መጸለይ ብቻውን በቂ ባለመሆኑ መልካም እየሠሩ አምላክን ማስደሰት፣ የተሰደዱትን ወገኖቻችንን ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር መወያየት፣ ሀብት ንብረታቸው ወድሞ ባዶ እጃቸውን የቀሩትን ከማጽናናት በተጨማሪ መደገፍ ከኢትጵያውያን ሁሉ የሚጠበቅ ነው:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን "ስለ ተሰደዱ ሰዎች እንማልዳለን" በማለት እንደመሰከረች ሁሉ ቀርባ ማጽናናት፣ የሚያስፈልጋቸውን ማቅረብ፣ ሥነ ልቡናቸውን መጠገንን አጠናክራ መቀጠል ይኖርባታል::

እንዲህ ዓይነቱ መጥፎ ድርጊት የአገራችንን መልካም ገጽታ የሚያጠፋ መሆኑን ተረድቶ  ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት መልካም ገጽታችንን የሚገልጥ ሕግ የማስከበር ተግባር መፈጸም ይገባዋል::  እየተፈጸመ ያለው ጅምላ ጭፍጨፋ ገጽታችንን ስለሚያጠለሽ ስማችንን የሚያድስ ብቻ ሳይሆን ተጎጂዎችንም የሚክስ ተግባር መፈጸም ከመንግሥት እንደሚጠበቅ ማስገንዘብ እንፈልጋለን:: ጥቃቱ እና ግድያው በዚሁ ከቀጠለ ንጹሓን ወጥተው ለመግባት እየተሳቀቁ መኖር ሲሰለቻቸው የአጥፊዎችን የጥፋት መንገድ እንዲከተሉ በር ስለሚከፍት አጥፊዎችን ለሕግ ከማቅረብ ጎን ለጎን የተጎዱትን በመደገፍ መልሶ ማቋቋም፣ የተበተኑትን መሰብሰብ፣ የራቁትን ማቅረብ ቀዳሚው የመንግሥት ተግባር ቢሆንም ኢትጵያውያን ሁሉ የሚጠበቅብንን ማከናወን ይኖርብናል እንላለን::✥

# የተለያየ ዘር አትዝራ

(ዘሌ.፲፱፥፲፱)

**ክፍለ ማርያም**

እንደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የዘመን አቈጣጠር ከሰኔ ፳፮ ጀምሮ እስከ መስከረም ፳፭ ድረስ ዘመነ ክረምት ወርኃ ክረምት እየተባለ ይጠራል። በዚህ በወርኃ ክረምት ውስጥም ደግሞ በርካታ ንኡሳን ክፍሎች አሉ። ከሰኔ ፳፮ ጀምሮ እስከ ሐምሌ ቀርቆስ ድረስ ዘርእ፣ ደመና፣ እየተባለ ይጠራል። በእነዚህ ሳምንታት ስለ ዘርእ፣ ስለዘሪው፣ ዘሩ ስለሚዘራበት መሬት፣ ስለደመና ወዘተ. ይነገራል።

ቤተ ክርስቲያን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" (ማቴ.፮፥፴፫) በማለት ያስተማረውን ትምህርት መሠረት አድርጋ ሰማያዊውን እንድናስቀድም በአጽንኦት ታስተምራለች። ይህ ማለት ግን እንደ ሚያስፈልገን አውቆ እርሱ ራሱ ያዘጋጅልናልና ከሰማያዊው ይልቅ ለምድራዊው ቅድሚያ እንዳንሰጥ ነው እንጂ አያስፈልግም የሚል ትምህርት የላትም። ይልቁንም ለአእምሮ የረቀቀውን፣ ለልቡና የራቀውን፣ ከዓይን የራቀውን፣ ከልቡና የተሰወረውን ረቂቅና ዘለዓለማዊ የሆነውን ሰማያዊ ምሥጢር አቅርቦና አጕልቶ ለማስረዳት ምድራዊውን መግቦት በምሳሌነት በመጠቀም ታስተምራለች።

በዚህ ጽሑፍም መነሻችን ምድራዊው የእርሻ፣ የዘር፣ የወይን ተክል፣ የወይን ተክል ቦታ፣ በሬ፣ ልብስ፣ ይህን ሁሉ የሚከናወንበትና የሚጠበቅበት ሥርዓት፣ ወዘተ. ሲሆን ነገር ግን ሰማያዊውንና ዘለዓለማዊውን የእግዚአብሔርን ትምህርትና መግቦት ለማጉላትና ለማስረዳት በምድራዊው መነሻነት እንመለከታለን። ሙሉ ቃሉን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው እንመልከተው።

"ሥርዐቴን ጠብቁ፤ በበሬህ በባዕድ ቀንበር አትረስ፤ በወይን ቦታህ የተለያየ ዘር አትዝራ፤ ከሁለት ዓይነት ነገር የተሠራ ልብስ ኃፍረት ነውና አትልበስ።" ይላል። (ዘሌ.፲፱፥፲፱) እንዲሁ ይህ ገጸ ንባብ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል "ፍሬውንና የዘራኸውን ዘር ከወይን ፍሬ ጋር እንዳትለቅም በወይንህ ቦታ ላይ የተለያየ ዓይነት ተክል አትትከል። በአህያህና በበሬህ በአንድነት አትረስ። ከተልባ እግርና ከበግ ጠጕር በአንድነት የተሠራ ልብስ አትልበስ።" ተብሎ ተጽፎ እናገኘዋለን። (ዘዳ.፳፪፥፱) ይህንም ኃይለ ቃሉን እያነሣን እንመለከተዋለን።

***ሥርዐቴን ጠብቁ፦*** ሥርዐት ሠርዐ ሠራ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ሕግ፣ አሠራር፣ ደንብ ማለት ነው። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ በተሰኘ መዝገበ ቃላታቸው "ሥርዐት፣ ደንብ፣ አሠራር፣ ሕግ፣ ትእዛዝ፣ ዐዋጅ፣ ፍርድ፣ ልማድ፣ የሥራ መንገድ" ብለው ይፈቱታል። (፲፱፻፺፰፣ ገጽ፺፻፸፰) ደስታ ተክለ ወልድ በበኩላቸው ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በተሰኘ መዝገበ ቃላታቸው "ንጹሕ ውሳኔ፣ የሕግና የትእዛዝ መጠበቂያ ደንብ" በማለት ይፈቱታል። (ገጽ ፰፻፴)

ከላይ በተገለጸው መሠረት እግዚአብሔር በአምልኮቱ እንኖር ዘንድ ከጠላት ዲያብሎስ ሴራ ፣ ከአምልኮተ ጣዖት ተለይተን በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንተን እንኖር ዘንድ የአምልኮት ሥርዐት ሠርቶልናል። ይህን ሥርዐት እንድንጠብቅ ሥርዐቴን ጠብቁ በማለት በሊቀ ነቢያት ሙሴ አማካይነት ትእዛዙን አስተላልፏል። ይህ ሥርዓት በሃይማኖት የመኖራችን፣ በአምልኮተ እግዚአብሔር የመጽናታችን መገለጫ ነው። እኛ ሰዎች በነጻ ፈቃድ፣ የተፈጠርን ቢሆንም ነጻ ፈቃዳችንን ተጠቅመን የማይገባ ሥራ ስለ ሠራን ከክብሩ ወርደናል፤ ልጅነታችንን አጥተናል፤ ከጸጋ እግዚአብሔር ተራቁተናል። ስለዚህ ያጣነውን ሁሉ ሊመልስልን አምላክ መከራ ተቀበለ፤ በመስቀል ላይ ተሰቀለ፤ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ያጣነውን ሁሉ መለሰልን። ስለዚህ ይህን የተመለሰልን እና የተሰጠነውን ጸጋ ሁሉ ጠብቀን እንኖር ዘንድ የሃይማኖታችን መገለጫ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኛ ሥርዐተ አምልኮ በፈጣሪያችንና በአምላካችን በእግዚአብሔር ተሰጥቶናልና ይህን መጠበቅ ደግሞ ክርስቲያናዊ ግዴታ ስለሆነ "ሥርዐቴን ጠብቁ" በማለት አዘዘን።

**የወይን ቦታ፦** የወይን ቦታ ተብሎ የተገለጸው ለጊዜው ለምድራዊው ህልውና የሚያስፈልገው ሁሉ የሚተከልበት ቦታ ነው። ፍሬውን ለመልቀም እንዳይቸገር በአንድ ቦታ ላይ መተከል ያለበት አንድ ዓይነት ተክል መሆኑን ያስረዳል። ምክንያቱንም "ፍሬውንና የዘራኸውን ዘር ከወይን ፍሬ ጋር እንዳትለቅም በወይንህ ቦታ ላይ የተለያየ ዓይነት ተክል አትትከል።" በማለት አቀላቅሎ ቢተክል የሚደርስበትን ችግር ያስረዳል።

ሌላው የወይን ቦታ እያለ የገለጸው በብሉይ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉት የእስራኤልን ልቡና ሲሆን በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በአጠቃላይ የምእመናንን ልቡና ነው። ይህን አስመልክቶ ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ "አሁን የወይኔን ቦታ በተመለከተ የወዳጄን መዝሙር ለወዳጄ እዘምራለሁ። ለወዳጄ በፍሬያማው ቦታ ላይ የወይን ቦታ ነበረው አጥር አጠርሁ፤ በዙሪያውም ቈፈርሁ፤ ድንጋዮችንም ለቅሜ አወጣሁ፤ ምርጥ የሆነውንም ወይን ተከልሁ፤ በመካከሉም ግንብ ሠራሁ፤ ደግሞም የመጥመቂያ ጉድጓድ ማስሁለት፤ ወይንንም ያፈራ ዘንድ ጠበቅሁት፤ ዳሩ ግን እሾህን አፈራ።... የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ወይን ቦታ የእስራኤል ቤት ነው፤ ተወዳጁ አዲስ

ተክልም የይሁዳ ሰዎች ናቸው፤ ፍርድን ያደርጋል ብየ እጠብቅ ነበር፤ እነሆም ዐመፅን አደረገ፤ ጽድቅንም አይደለም፤ ጩኸትን እንጂ” በማለት አስረድቶናል። (ኢሳ.፭፥፩-፯)

እስራኤል ትንቢት የተነገረላቸው፣ ሱባኤ የተቈጠረላቸው፣ ተስፋ ድኅነት የተሰጣቸው ናቸው። ይህ ብቻ ሳይሆን በወቅቱ ነቢያት የተላኩላቸው፣ ጠባቂ የተሾመላቸው፣ ምግበ ሥጋው ያልተቋረጠባቸው፣ በተለይም ምግበ ነፍስ የሆነው ቃለ እግዚአብሔር እየተነገራቸው ዕለት ዕለት በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንተው እንዲኖሩ እግዚአብሔር አምላክ በልዩ እንክብካቤ የጠበቃቸው የወይን ቦታው ናቸው። ይሁን እንጂ እንደተደረገላቸው መልካም ነገር በሃይማኖት ሲጸኑ፣ መልካም ሥራ ሲሠሩ አልተገኙም፤ ከዚህ ይልቅ ጣዖት አምልከው ለጣዖት ሲሰግዱ፣ ለጣዖት የተሠዋውን መሥዋዕት እየበሉና እየጠጡ የማይገባ ሥራ ሲሠሩ ተገኝተዋል። ስለዚህ እኔ ለወይን ቦታየ ያላደረግሁለት ነገር ምን አለ? እያለ ይጠይቃል።

ስለዚህ በወይን ቦታህ የተለያየ ዘር አትዝራ ሲል የሕግ ማደሪያ በሆነ ልቦናህ ሕገ እግዚአብሔርንና ሕገ ጣዖትን አንድ አድርገህ አትያዝ ሲል ነው። ሁለቱ አንድ ላይ የማይተባበሩ ስለሆነ ነው። ይህ ማለት ግን ከአምልኮተ ጣዖት ተመልሳችሁ በአምልኮተ እግዚአብሔር ኑሩ፤ ልቡናችሁን የእግዚአብሔር ማደሪያ አድርጉት ማለት ነው እንጂ ምርጫ የግድ ነውና ከሕገ እግዚአብሔር ወጥታችሁ ወደ ሕገ ጣዖት ሂዱ ማለት አይደለም።

ምክንያቱም ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ በአምልኮ ጣዖት እና በአምልኮተ እግዚአብሔር መካከል እየተመላለሱ ለነበሩት ሕዝብ “እስከ መቼ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፤ በዓልም አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ” (፩ኛነገ.፲፰፥፳፩) በማለት የተናገረው በዓልን አምላክ ነው ለማለት አይደለም። የእግዚአብሔርን አምላክነት ጠንቅቆ ያውቃል። በዚህም ምክንያት ከንጉሥ ከንግሥት ተጣልቷል፤ ብዙ መከራም ተቀብሏል። ይሁን እንጂ በሁለት አሳብ እየተመላለሱ ያሉትን ሕዝብ አንዱን ማለትም አሳባቸውን እየከፈለ ካለው አምልኮተ ጣዖት ተመልሰው አምልኮተ እግዚአብሔርን ብቻ መምረጥ እንዳለባቸው ለማስረዳት ይህን ተናገረ።

ሁለቱ ግብራት ማለትም አምልኮተ እግዚአብሔርና አምልኮተ ጣዖት አብረው ሊሄዱ እንደማይችሉ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በላከው መልእክቱ “ተጠራጣሪዎች አትሁኑ፤ ወደማያምኑ ሰዎች አንድነትም አትሂዱ፤ ጽድቅን ከኃጢአት ጋር አንድ የሚያደርጋት ማን ነው? ብርሃንንስ ከጨለማ ጋር የሚቀላቅል ማን ነው? ክርስቶስን ከቤልሆር ጋር አንድ የሚያደርገው ማን ነው? ወይስ ምእመናንን ከመናፍቃን ጋር አንድ ወገን የሚያደርጋቸው ምን ነው? የእግዚአብሔርን ታቦስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው? የሕያው እግዚአብሔር ማደሪያዎች እኛ አይደለንምን? እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናገረ፤ እኔ በእነርሱ አድራለሁ፤ በመካከላቸውም እኖራለሁ፤ አምላካቸውም እሆናቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆኑኛል። ስለዚህም ከመካከላቸው ተለይታችሁ ውጡ፤ ከእነርሱ ተለዩ፤ ወደ ርኵሳን አትቅረቡ፤ እኔም እቀበላችኋለሁ። አባት እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ሴቶችና ወንዶች ልጆች ትሆኑኛላችሁ፤ ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር።” (፪ኛቆሮ.፮፥፲፬-፲፰) በማለት በአጽንኦት አስረድቷል። ስለዚህ ኃጢአትን ከጽድቅ ጋር፣ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከአምልኮተ ጣዖት ጋር፣ ሕገ እግዚአብሔርን ከሕገ ጣዖት ጋር እያደባለቃችሁ አትኑሩ። በአግባቡ አምልኮተ እግዚአብሔርን አጽንታችሁ ኑሩ በማለት አስረድቷል።

ከላይ በተጠቀሰው ምንባብ “በሬህንም በባዕድ ቀንበር አትጥመድ” የሚል እናገኛለን። በሬ ዕለት ዕለት የሚያርስበት ቀንበር ሲቀየርበት የሚጠምደውም ሰው ሲቀየር አመል ያወጣል ይባላል። ስለዚህ “የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ” የሚባለው በለመደው አግባብ ሲሆን የተሻለ ይሆናል። በዋናነት ግን በሬ የተባለው ልቡና ሲሆን የባዕድ ቀንበር ተብሎ የተገለጸው ከሕገ እግዚአብሔር ውጪ የሆነውን አምልኮተ ጣዖት ነው። በቅዱስ ወንጌል ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕገ ወንጌልን በቀንበር መስሎ አስተምሯል። “እናንተ ደካሞች ሸክማችሁም የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ ነኝና፤ ልቤም ትሑት ነውና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍትን ታገኛላችሁ። ቀንበሬ ልዝብ፣ ሸክሜም ቀላል ነውና” እንዲል። (ማቴ.፲፩፥፳፰-፴)

ይህን የወንጌል ቃል የተረጐሙ መምህራን “ቀንበር አላት ወንጌልን ቀንበር ሁለቱን በሮች አንድ እንደምታደርግ ወንጌልም ሕዝብና አሕዛብን አንድ ታደርጋለችና” ብለው ተርጉመውታል። ስለዚህ የእግዚአብሔር የቸርነቱ መገለጫ በሆነችውና ዘለዓለማዊውን መንግሥት እንድንወርስ በምታደርገው ሕገ እግዚአብሔር ጸንታችሁ ኑሩ እንጂ በባዕድ አምልኮ አትኑሩ ሲል “በሬህን በባዕድ ቀንበር አትጥመድ” ብሎ አዘዘ።

በሌላም በኩል በአህያህና በበሬህ በአንድነት አትረስ የሚል ገጸ ንባብ አለ። በዚህ ገጸ ንባብ አህያና በሬ ተብለው የተገለጹት ለጊዜው ሁለቱ በሙያ ስለሚለያዩ በአንድ ላይ ተጠምደው ማረስ ስለማያስችሉ ነው። አህያው ሊጫን በሬው ደግሞ ተጠምዶ ሊታረስበት ሁለቱም ግን ለሰው ልጅ አገልግሎት ተፈጥረዋል። ይህ ማለት ግን አህያውን ለእርሻ ቢያለማምዱት አይሆንም ማለት አይደለም። ሁለቱ አህያውና በሬው በአንድ ላይ ግን ተጠምደው እኩል ሊስቡ አይችሉምና ገበሬው ይቸገራል። በሬን ከበሬ ጋር ሊጠምዱ ይገባል እንጂ በሬን ከአህያ ጋር ቢጠምዱ ሥራው በታሰበው ልክ አይከናወንምና አንድ ላይ አትጥመድ ተብሏል።

በዋናነት ግን አህያና በሬ ተብለው የተገለጹት ካህነ ጣዖትና ካህነ ኦሪት ናቸው። ስለዚህ በአህያህና በበሬህ በአንድነት አትረስ ማለት በአንድ ቀንበር ጠምደህ አትረስባቸው ሲል ነው። ይህም ማለት ከካህነ ጣዖትና ከካህነ ኦሪት እማራለሁ አትበል ማለት

ነው:: ሁለቱም የየራሳቸው ትምህርትና ተልእኮ አላቸው:: ካህነ ኦሪቱ ሕገ ኦሪትን ማስጠበቅ፣ በሕገ ኦሪት መሠረት ሕዝቡን ማገልገል ነው:: ካህነ ጣዖቱ ደግሞ ሕዝቡ ጣዖቱን እንዲያመልኩ ለጣዖቱ ማድረግ ያለባቸውን እንዲያደርጉ ስለጣዖቱ ማስተማር ነው:: መዳረሻቸውም ይለያያል:: ካህነ ኦሪቱ ወደ እግዚአብሔር ያደርሳል ካህነ ጣዖቱ ግን ወደ ዲያብሎስ ያደርሳል:: ስለዚህ የተለያየ ተልእኮ፣ የተለያየ ትምህርትና የተለያየ መዳረሻ ይዘው መንዝ ስለማይችሉ በእንደዚህ ያለ ተግባር ተሠማርተው እግዚአብሔርን ማገልገል ስለማይችሉ ከሁለቱም ትምህርት እንማራለን አትበሉ ሲል ነው::

እንደዚህ ያለውን ተግባር መከተል እንደማይገባ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በቅዱስ ወንጌል በክፉና በመልካም ዛፍ መስሎ አስተምሯል:: “የበግ ለምድ ለብሰው ወደ እናንተ ከሚመጡ ከሐሰተኞች ተኵላዎች ተጠንቀቁ፤ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ናቸው:: ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ ከእሾህ ወይን ከአሜከላም በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬን ያፈራል፤ ክፉ ዛፍም ክፉ ፍሬን ያፈራል:: መልካምም ዛፍ ክፉ ፍሬን ማፍራት ክፉ ዛፍም መልካም ፍሬን ማፍራት አይችልም:: መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል:: እንግዲህ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ::” እንዲል:: (ማቴ.፯፥፲፭-፳)

እውነተኛ መምህራን ሳይሆኑ መስለው ሊያስተምሩ ቢፈልጉ ተጠንቀቁ፤ ከእነርሱ እውነተኛ ትምህርት አይገኝምና:: ለጊዜው መስለው ቢቀርቡ እንኳን ካስተዋላችኋቸው ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ:: ምክንያቱም መልካም ዛፍ መልካም ፍሬን ያፈራል፤ ክፉ ዛፍ ግን ክፉ ፍሬን ያፈራል:: እንዲሁ እውነተኛ መምህር እውነተኛ ትምህርትን ያስተምራል፤ ሐሰተኛ መምህር ግን ሐሰተኛ ትምህርትን ያስተምራል::

ዘር፡- የተለያየ ዘር ሲዘራ አንዱ የሌላው ጠላት ሊሆን ይችላል:: ለመሰብሰብ የሚደርሱበት ጊዜም የተለያየ ሊሆን ይችላል:: አንዱ ቀድሞ ቢደርስ ሊላው ቢዘገይ የደረሰውን ለመሰብሰብ ሲባል ያልደረሰው ሊጎዳ ይችላል:: በእርግጥ አልፎ አልፎ ተቀላቅለው የሚዘሩ ዘሮች ያሉ ቢሆኑም በአብዛኛው ግን በአንድ መሬት ላይ አንድ ዓይነት ዘር ብቻ ሲዘራ በተፈለገው ልክ ያማረ ይሆናል:: ስለዚህ በዚህ ሁሉ መቸገር አለና አንድ ዓይነት ዘር ብቻ መዘራት አለበት ተብሎ ተገልጿል::

ልብስ፡- ልብሱ በእርግጥ እንደየአካባቢው ባህል ሊታይ ይችላል:: ምክንያቱም ሆን ተብሎ ከተለያየ ቀለም ሊዘጋጅ ይችላል:: ይህ ግን የተለያየ ልብስ ተብሎ የተገለጸው ድህነትን የሚያመለክት ተብሎ የተገለጸ ነው:: በዋነኛነት ግን በሰሙ የተገለጸውን ሳይሆን በወርቅ የተገለጸውን እንመለከታለን::

ስለዚህ ዘርና ልብስ ተብሎ የተገለጸው ሥርዓተ አምልኮ ነው:: የተለያየ ዘር፣ የተለያየ ልብስ እየተባለ የተገለጸው አምልኮተ እግዚአብሔርና አምልኮተ ጣዖትን ቀላቅሎ መከተል ነው:: ሰው ጥንቱ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረው ስሙን ቀድሶ ክብሩን ወርሶ ሊኖር እንጂ ከአምልኮተ እግዚአብሔር ውጪ ሌላ ተግባር ሊኖረው አይደለም:: ነቢዩ ዮናስ በመርከብ ውስጥ ሳለ ማዕበል ሞገድ ተነሥቶ መርከቢቱን ሲያናውጣት ሕዝቡ ሥራህ ምንድነው ከወዴትስ መጣህ? ወዴትስ ትሄዳለህ ብለው በጠየቁት ጊዜ የመለሰላቸው ሥራየ ባሕሩንና የብሱን፣ የፈጠረውን እግዚአብሔርን አመልካለሁ ብሎ ነበር:: (ዮና.፩፥፱) ስለዚህ ሥራችሁ ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወጥቶ በአምልኮተ ጣዖት መኖር እንዳይሆን ሲል የተለያየ ዘር አትዝራ፣ የተለያየ ልብስ ፣ አትልበስ ብሎ አስረዳ::

በሌላ በኩል ዘር ቃለ እግዚአብሔር ተብሎ ተገልጿል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል ዘሪ ዘሩን እንደዘራ፣ ዘሩ በመንገድ ላይ፣ በጭንጫ፣ በእሾህና በመልካም መሬት ላይ እንደ ወደቀ፣ በመልካም መሬት ላይ ከወደቀው በቀር ሌላው ተገቢውን ፍሬ እንዳላፈራ ቢያፈራ እንኳን ለባለቤቱ እንዳልጠቀመው ከተናገረ በኋላ ዘሩን በቃለ እግዚአብሔር፣ የዘሩን ቦታ የምእመናን ልቡና፣ ዘሪውን ራሱ ጌታ ብሎ በምሳሌ አስተምሯል:: “እንግዲህ እናንተ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ:: የመንግሥተ ሰማያትን ቃል ሰምቶ ለማያስተውል ሁሉ ክፉው መጥቶ በልቡ የተዘራውን ቃል ይነጥቀዋል፤ በመንገድ የተዘራው ዘር ይህ ነው:: በጭንጫ ላይ የተዘራውም ቃሉን የሚሰማና ፈጥኖ በደስታ የሚቀበለው ነው:: ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ላይ ሥር የለውም፤ በቃሉም ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይክዳል:: በእሾኽ መካከል የተዘራውም ቃሉን ሰምቶ የዚህ ዓለም አሳብና የሀብት ማታለል ቃሉን አንቆት ያለ ፍሬ የሚቀረው ነው:: ነገር ግን በመልካም ምድር ላይ የተዘራው ይህ ቃሉን የሚሰማና የሚያስተውል ነው፤ እርሱም አንዱ መቶ፣ ሌላውም ስድሳ፣ ሌላውም ሠላሳ ፍሬ ይሰጣል::” በማለት ያስረዳውን ልብ ማለት ይገባል:: (ማቴ.፲፫፥፲፰-፳፫)

በአጠቃላይ በወይን ቦታህ ላይ የተለያየ ዘር አትዝራ ማለት የእግዚአብሔር ማደሪያ እንሆን ዘንድ ሥጋውን በቆረሰለት፣ ደሙንም ባፈሰሰለት ሰውነታችን መልካም የሆነውን አምልኮተ እግዚአብሔርን እንድናጸናበት መልካም ሥራ እንድንሠራበት የተላለፈ ጽኑ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው:: ሊቁ ቅዱስ ያሬድ በዝማሬ መዋሥዕቱ “አኮ በወርቅ ኃላፊ ዘተሳየጠነ በደሙ ክቡር ቤዘወነ ወለደነ በጥምቀቱ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤ በኃላፊው ወርቅ የገዛን አይደለም፤ በክቡር ደሙ ዋጀን እንጂ፤ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንም በጥምቀቱ ዳግመኛ ወለደን” በማለት እንደተናገረው አስቀድሞ በአርያአያው የፈጠረን፣ የፍጥረታት ሁሉ ገዥ ያደረገን፣ በኋላም የደም ዋጋ የከፈለልን ክቡር ፍጥረቱ ነንና የተከፈለልንን ዋጋ አክብረን፣ ልቡናችንን ከአምልኮተ ጣዖት ለይተን፣በአምልኮተ እግዚአብሔር አጽንተን፣ መልካም ሥራ ሠርተን የመንግሥቱ ወራሽ የስሙ ቀዳሽ እንድንሆን የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ሁሉ ምልጃ አይለየን አሜን::✣

# ደመናውንም ከላይ አዘዘ

(መዝ. ፸፯፥፳፫)

ቀሲስ ዘክርስቶስ ጸጋዬ

የክረምት መግቢያ ወቅት ከሰኔ ፳፮ እስከ ሐምሌ ቊርቆስ ሲሆን ምልአተ ባሕር ደግሞ ከሐምሌ ቊርቆስ እስከ ነሐሴ ፲ ድረስ ያለው ጊዜ ነው፡፡ በእዚህ ወቅት ደመና ምድርን የሚያለመልምበት፣ ዘር የሚዘራበት፣ የተዘራው የሚበቅልበት፣ በፀሐይ ሐሩር የደረቁ ዛፎች ሁሉ የሚያቆጠቁጡበት ወቅት ነው፡፡ በተለይ ከሐምሌ ቊርቆስ እስከ ሐምሌ ፳፱ ባለው ወቅት መባርቅት የሚበርቁበት፣ ባሕርና አፍላጋት የሚሞሉበት፣ ምድር ጠልን የምትጎናጸፍበት ወቅት ነው፡፡

በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዚህ ወቅት ዘርዕን፣ ደመናን፣ ዝናምን የሚያዘክሩ እና የመብረቅን፣ የነጎድጓድን፣ የባሕርን፣ የአፍላጋትን፣ የጠልን ጠባይዓት የሚያመለክቱ መዝሙራት ይዘመራሉ፤ ምንባባት ይነበባሉ፣ ስብከት ይሰበካል፡፡ ሊቁ ቅዱስ ያሬድም መብረቅን የሚመልሰው፣ ነጎድጓድን የሚያበረታው፣ መብረቅን ካልነበረበት በጋ ወደሚኖርበት ክረምት የሚያመጣውና ደመናን የሚፈጥርለት እግዚአብሔር መሆኑን በድጓው ያስረዳል፡፡

ደመና ስንል ከርጥብ ምድር የሚወጣ ጢስ፣ ላበት፣ ተሰብስቦ ከጠፈር በታች በኅዋ የሚታይ ጠፈርን የሚሸፍንና የሚጋርድ ማለት ነው( ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በገጽ ፫፻፶፪) ፡፡ ደመና መደመን መጥቆር፣ መጨለም፣ ደመና መምሰል፣ ደመና መልበስ፣ በጉም መታፈን፣ መሸፈን እየተባለ ሊገለጥም ይችላል፡፡ ይህን ዑደት በተለይ በክረምት ወቅት የምንመለከተው ነው፡፡

## የደመና ዑደት

የደመናን አወጣጥንና ከየት ወጥቶ ወደ የት እንደሚመለስ መጽሐፍ ቅዱስ "ከምድር ዳር ደመናትን ያወጣል፤ ለዝናም ጊዜም መብረቅን አደረገ፤ ነፋሳትንም ከመዛግብታቸው ያወጣል" በማለት ገልጦታል፡፡ እንዲሁም ነቢዩ መሴ የሥነ ፍጥረትን ነገር በተናገረበት በመጀመርያው ክፍል አዳም በምድር ላይ ሥራ መሥራት ከመጀመሩ በፊት ስለነበረው ሁኔታ ሲገልጥ "ምድር የሚሠራባት አልነበረም፣ ጉም ከምድር ይወጣ ነበረ፣ የምድርንም ፊት ሁሉ ታጠጣ ነበረ" በማለት ከርጥብ ምድር የሚወጣ ጢስ፣ ጉም፣ ከጠፈር በታች በኅዋ ላይ ታይቶ ጠፈርን እንደሚሸፍንና ከዚያም በኋላ የምድርንም ፊት ሁሉ እንደሚያጠጣ ገልጧል፡፡ ከዚያም የሰውን ልጅ የፈጠረበትን ሂደት "እግዚአብሔርም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፣ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ" በማለት ያጠቃልላል (ዘፍ. ፪፥፯)፡፡

ቅዱስ ዳዊትም በመዝሙሩ "ጸልሙ ማያት በውስተ ደመናት፣ ወእምብርሃነ ገጹ ኀለፉ ደመናት ቅድሜሁ፣ በረድ ወአፍሓመ እሳት፤ ውኃዎች በደመናዎች ውስጥ ጠቆሩ፤ በፊቱ ካለው ብርሃን የተነሣ ደመናትና በረዶ የእሳት ፍምም በፊቱ አለፉ" ይላል፡፡ በሌላ መዝሙሩም የደመና አወጣጥ እና አከናዋኙ ማን እንደሆነ እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ ማድረጉን ገልጦ "ያዐርግ ደመናተ እምአጽናፈ ምድር፣ ወገብረ መብረቀ ለጊዜ ዝናም፣ ዘያወፅኦሙ ለነፍሳት እመዛግብቲሆሙ፤ ከምድር ዳር ደመናትን ያወጣል በዝናብ ጊዜ መብረቅን አደረገ፤ ነፋሳትንም ከመዛግብቱ ያወጣል" (መዝ.፻፴፬፥፯) ብሏል፡፡

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተገለጠው ደመና ምሳሌነቱ የክብረ እግዚአብሔር፣ የመግቦተ እግዚአብሔር፣ የጥምቀት፣ የሥልጣነ እግዚአብሔር፣ የጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ እና የድንግል ማርያም ምሳሌዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ምሳሌዎች ከክብረ እግዚአብሔር መገለጫነት ጀምረን በቅደም ተከተል እናቀርባለን፡፡ የቅዱሳን ጌጥ እና ሽልማት የሆነው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምሥጢሩን ይግለጥልን፡፡

### ፩. የክብረ እግዚአብሔር መገለጫ

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አምላክ ለሕዝበ እስራኤል ክብሩን በደመና ይገልጥላቸው ነበር፡፡ ይህን አስመልክቶ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በሲና ተራራ የተፈጸመውን "የእግዚአብሔርም ክብር በሲና ተራራ ላይ ተቀመጠ፣ ደመናውም ስድስት ቀን ሸፈነው፤ በሰባተኛውም ቀን ከደመናው ውስጥ ሙሴን ጠራው፡፡ ሙሴም ወደ ደመናው ውስጥ ገባ፤ ወደ ተራራውም ወጣ፤ ሙሴም በተራራው ላይ አርባ ቀን፣ አርባ ሌሊት ቆየ፡፡ ሙሴም ወደ ድንኳኑ በገባ ጊዜ የደመና ዓምድ ይወርድ ነበር፣ በድንኳኑም ደጃፍ ይቆም ነበር፤ እግዚአብሔርም ሙሴን ይናገረው ነበር፡፡ ሕዝቡም ሁሉ የደመናው ዓምድ በድንኳኑ ደጃፍ ሲቆም ያየው ነበር፤ ሕዝቡም ሁሉ ተነሥቶ እያንዳንዱ በድንኳኑ ደጃፍ ይሰግድ ነበር" ብሏል (ዘጸ.፳፬፥፲፰፤ ፴፫፥፱-፲)፡፡ እግዚአብሔር አምላክ በደመና ክብሩን ይገልጽ እንደ ነበረና ሕዝቡም አምልኮቱን ይፈጽም እንደ ነበረ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ገልጦልናል፡፡

በመገናኛው ድንኳንም እግዚአብሔር ክብሩን ይገልጥ እንደ ነበርና የጉዟቸውን ሁኔታ ይወስንላቸው እንደ ነበር ሲገልጥ "እግዚአብሔርም በደመናው ውስጥ ወረደ፣ በዚያም ከእርሱ ጋር ቆመ፣ የእግዚአብሔርንም ስም አወጀ፡፡ ደምናውም የመገናኛውን ድንኳን ከደነ፣ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ፡፡ ደመናውም በላዩ ስለ ነበረ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ስለ ሞላ ሙሴ ወደ መገናኛው ድንኳን ይገባ ዘንድ አልቻለም፡፡ ደመናውም ከማደሪያው በተነሣ ጊዜ የእስራኤል ልጆች በመንገዳቸው ሁሉ ይጓዙ ነበር፡፡ ደመናው እስከሚነሣበት ቀን ድረስ አይጓዙም ነበር፡፡

በመንገዳቸውም ሁሉ በእስራኤል ቤት ሁሉ ፊት የእግዚአብሔር ደመና በማደሪያው ላይ በቀን ነበርና፣ እሳትም በሌሊት በዚያ ላይ ነበረና” (ዘፀ. ፵፬፥፳፤ ፺፥፴፬-፴፰)። ክብረ እግዚአብሔር ከግብፅ ባርነት ተላቀው በሊቀ ነቢያት ሙሴ መሪነት ለሚመሩት ማኅበር ሲገለጥ “ማኅበሩ በሙሴና በአሮን ላይ በተሰበሰቡ ጊዜ የመገናኛውን ድንኳን አዩ እነሆም፣ ደመናው ሸፈነው፣ የእግዚአብሔርም ክብር ተገለጠ” ይለናል (ዘኍ. ፲፩፥፳፫፤ ፲፪፥፫-፲)።

## ፪. የመግቦተ እግዚአብሔር መገለጫ

የእግዚአብሔር መግቦት የሚገለጥባቸው መንገዶች ብዙ ናቸው። “…ኢየሱስ ክርስቶስ ዘያዕቆብ ዐምደ ደመና፣ ምርሐኒ እግዚኦ ኀበ ዘይትፈቀድ ፍና፣ በዓመተ ርስዓን ወድካም ኢይርአይ ሙሰና፦ የያዕቆብ ደመና ምሰሶ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በእርግና፣ በድካም ዘመን ጥፋትን እንዳላይ አቤቱ የተወደደ ወደሚሆን ጎዳና ምራኝ” በማለት የመልክአ ኢየሱስ ደራሲ ኢየሱስ ክርስቶስን ተማጽኖታል። እስራኤላውያን ለ፬፻፲፰ ዓመት መከራን ከተቀበሉበት ከግብፅ ወጥተው ወደ ምድረ ርስት ሲጓዙ በሰባት ደመና ተጋርደው መውጣታቸው የእግዚአብሔር መግቦት መገለጫ ነው።

አንዱ በፊታቸው፣ አንዱ በኋላቸው፣ አንዱ በቀኛቸው፣ አንዱ በግራቸው፣ አንዱ ከላይ እንደ ጥላ ሆኖ የቀን ሐሩር፣ የሌሊት ቁር እንዳያገኛቸው እየከለለ፤ አንዱ ደመና ከሥር እንደ ጫማ ሆኖላቸው እሾህ፣ እንቅፋት እንዳያገኛቸው እያታደገ፣ ሰባተኛው ደመና የሦስት ቀን ጎዳና ቀድሞ እየሄደ ዛፉን እየነቀለ፣ ድንጋዩን እየፈነቀለ፣ ዝቅ ያለውን ከፍ፤ ከፍ ያለውን ዝቅ እያደረገ ይደለድልላቸው ነበር። ቀን ዐምደ ደመና ሆኖ ሲመራቸው የነበረው ሌሊት ደግሞ ዐምደ እሳት ሆኖ ሲያበራላቸው ያድር ነበር (ዘፀ. ፲፬፥፲፱-፳)። እንዲህ ያለው ምሥጢር የእግዚአብሔር መግቦት ከመመርመር በላይ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

የደመናው ምሰሶ በፈርዖን ባርነት ተይዘው የነበሩትን የያዕቆብ ልጆች እስራኤል ዘሥጋን ከጠላታቸው ከፈርዖንና ከሠራዊቱ እጅ ከልሎ፣ ከፊት መርቶ፣ ከኋላ ተከትሎ፣ በቀኝ፣ በግራ ጋርዶ ወደ ምድረ ርስታቸው ከነዓን እንዳደረሳቸው ሁሉ፤ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመስቀል ተሰቅሎ፣ በፈርዖንና በሠራዊቱ የተመሰሉ ዲያብሎስንና ሠራዊቱን ድል ነሥቶ ፭ሺህ ፭መቶ ዘመን በዲያብሎስ ባርነት የነበሩ ነፍሳትን “እለ ውስተ ሲኦል ጻዑ፤ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ፤ በሲኦል ያላችሁ ውጡ፤ በጨለማ ውስጥ ያላችሁ ተገለጡ” ብሎ ከሲኦል አውጥቶ ወደ ጥንተ ርስታቸው ወደ ገነት አግብቷቸዋል።

## ፫. የጥምቀት ምሳሌ

በብሉይ ኪዳን አባቶቻችን እስራኤል ዘሥጋን የመገበ፣ የጠበቀ፣ የተንከባከበና ወደ ምድረ ርስት ከነዓን በዓምደ ደመና እየመራ ያስገባቸው እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በመዋሐድ ሰው የሆነ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትን በ፴ ዓመቱ በእደ ዮሐንስ “ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል” በማለት በተግባር በመፈጸምና (ማቴ. ፫፥፲፭) በቃል ደግሞ “ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም” ብሎ ለኒቆዲሞስ በማስተማር ክርስቲያኖች ሁሉ ስንተገብረው እንድንኖር አድርጓል (ዮሐ. ፫፥፭)።

ቅዱስ ጳውሎስም “ወንድሞች ሆይ፣ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ፤ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ” በማለት ቀድሞ የእስራኤላውያን መሻገር ለጥምቀት ምሳሌ የነበረ መሆኑንና አሁን በአዲስ ኪዳን አማናዊ ምሥጢረ ጥምቀትን ወደ መንግሥተ ሰማያት መሻገርያ በር መሆኑን ሲያሳይ ጥምቀቱም በደመናና በባሕር (በመንፈስ ቅዱስና በውኃ) መሆኑን ገልጦአል (፩ኛ ቆሮ. ፲፥፩-፪)።

ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይህን ምሥጢር የምትፈጽመው ከክርስቶስ መጠመቅ ምሥጢር አንጻር የተገለጠ እውነት ተነሥታ ነው (ማቴ. ፫፥፲፫-፲፯)። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ በደመናና በባሕር ተጠመቁ እንዳለው በደመና የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ ማኅተሙ ሲሆን በማኅተሙ ላይ ያለው ደግሞ ሥዕለ ክርስቶስ ነው። በዚህ ምክንያት የጥምቀት ማኅተም በሜሮን አማካኝነት ወደ ተጠማቂው ሲሸጋገር ይኖራል።

## ፬. የሥልጣነ እግዚአብሔር መገለጫ

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን የመግለጥ ምሥጢርን በተመለከተ በማቴዎስ ወንጌል ላይ እንደ ተቀመጠው “እርሱም ገና ሲናገር፣ እነሆ፣ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፤ የጋረዳቸው ብሩህ ደመና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። እነሆም ከደመናው በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ” በማለት ሲገልጠው (ማቴ. ፲፯፥፭) ይህን ምሥጢር የማርቆስ ወንጌልም “ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው፣ ከደመናውም። የምወደው ልጄ ይህ ነው፣ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ” በማለት ያስነብበናል (ማር. ፱፥፳፯)። የሉቃስ ወንጌልም ይህንን ምሥጢር “ደመና መጣና ጋረዳቸው፤ ወደ ደመናውም ሲገቡ ሳሉ ፈሩ ከደመናውም። የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው፣ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ” በማለት አስረድቶናል(ሉቃ. ፱፥፴፬-፴፭)።

ከደመናው ውስጥ የወጣው ድምፅ ስለ እግዚአብሔር ወልድ ስለ ድንግል ማርያም ልጅ ስለ ልጁ የመሰከረው እግዚአብሔር አብ ሲሆን ብሩህ ደመናው ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ ደመና በዕርገተ ክርስቶስም ሆነ በምጽአቱ ተገልጦ እናገኘዋለን (ሐዋ. ፩፥፱) እና (ሉቃ. ፳፩፥፳፯) በዕርገቱ ጊዜም ደመና ሠወረችው ተብሎ የተጻፈው በገዛ ሥልጣኑ ማረጉን ለማስረዳት ነው።

### ፭. የጰራቅሊጦስ (የመንፈስ ቅዱስ) ምሳሌ

አባቶቻችንን የመራው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ የመልክአ ጰራቅሊጦስ ደራሲ ከገለጠባቸው የተለያዩ ምሳሌዎች መካከል አንዱ ዐምደ ደመና የሚል ሲሆን፤ ሌሎቹ ደግሞ ጰራቅሊጦስ መና ወማይ፤ የምድረ በዳ መጠጥ ውኃ፣ ጰራቅሊጦስ መና፣ የምድረ በዳ መና፣ ጰራቅሊጦስ ፀሓይ፤ የብርሃናት ንጉሥ እና ጰራቅሊጦስ ዜው፤ አፍን የሚያጣፍጥ ጨው የሚሉ ናቸው።

አርኬውም፣"ጰራቅሊጦስ ዓምደ ደመና ዘመራሕኮሙ ለአበው፤ ጰራቅሊጦሰ መና ወማየ ስቴ ዘበድው፤ ጰራቅሊጦስ ፀሐይ ንጉሠ ብርሃናት ሥርግው፤ አብርህ ልቡናየ በብርሃንከ ፍንው፤ ወልስሐተ አፉየ ቀሥም ጰራቅሊጦስ ዜው፤ አባቶችንን የመራሕ የደመና ዐምድ ጰራቅሊጦስ፤ በምድረ በዳ የተገኘህ የመጠጥ ውኃና መና ጰራቅሊጦስ፤ የተሾመ የብርሃናት ንጉሥ ጰራቅሊጦስ፤ ከአብ ዘንድ በተላክ ብርሃንህ ልቡናየን አብራው፤ አንተ ጨው ጰራቅሊጦስ አልጫ የሆነ አፌንም አጣፍጠው" የሚል ነው።

የደመና ዐምድ፤ ጰራቅሊጦስ ዓምደ ደመና ዘመራሕኮሙ በማለት የብሉይ ኪዳን አባቶቻችን የመራቸውን በመጥቀስ ዓምደ ደመና፤ የደመና ዐምድ በማለት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ይገልጠዋል። ይህ ማለት ግን ለመንፈስ ቅዱስ እንዲህ ነው፤ ይህን ያህላል፤ ይህን ይመስላል ተብሎ የሚወሰን፣ የሚዳሰስና የሚገለጥ አካል አለው ማለት አይደለም። መግቦቱ በሚገለጥበት፣ እርሱ በፈቀደ ልገለጥ ብሎ በተገለጠበት የሰው ልጆች ለመረዳት እንዲቻል አባቶች እንዲህ ያለውን አገላለጥ ተጠቅመዋል።

### ፮፤ የድንግል ማርያም ምሳሌ

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን ወደ እዚህ ምድር መጥቶ ሊቀበል ስላለው መከራ አምልቶ፣ አስፍቶ የጻፈ ነቢዩ ኢሳይያስ በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝቶ ቅድስተ ድንግል ማርያም የባሕርይ አምላክ አማኑኤልን ይዛ ወደ ግብፅ የመሰደዷን ነገርም አስቀድሞ ተገልጾለት "እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብፅ ይመጣል፣ የግብፅም ጣዖታት በፊቱ ይርዳሉ" (ኢሳ. ፲፱፥፩) በማለት ተናግሯል። ከገነት የተሰደድነውን እኛን ወደ ቀደመ ርስታችን ሊመልሰን እንደመጣ ለማጠየቅና፣ ጠላታችን ዲያብሎስን ከሰዎች ልብ አውጥቶ ለመስደድ፣ ክብር ይግባውና ወልደ እግዚአብሔር ልመናዋ ፈጥኖ በሚሰማላት "ደመና መፍጠኒት" በተባለች በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ጀርባ ታዝሎ ወደ ግብፅ የመሰደዱን ነገር አስቀድሞ ገልጦታል።

በቅዱስ ወንጌል እንደ ተጻፈ ንጉሥ ሄሮድስ ክርስቶስን ለመግደል በፈለገ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ለአረጋዊው ዮሴፍ በሕልሙ ተገልጾለት "ተንሥእ ወንሣእ ሕፃነ ወእሞ ወጕየይ ውስተ ብሔረ ግብፅ፤ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ" ባለው ጊዜ ይህ ኢሳይያስ የተናገረው ትንቢት ሊፈጸም ምልጃዋ ፈጥኖ የሚደርስ "ደመና መፍጠኒት" በተባለች በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ጀርባ ታዝሎ ወደ ግብፅ በሄደ ጊዜ በግብፅ ጣዖታት ሁሉ እየተሰባበሩ ሲወድቁ፣ በእነርሱ አድረው ሰዎችን ያስቱ የነበሩ አጋንንት ሁሉ ሸሽተዋል፤ በመሆኑም እመቤታችን "ደመና መፍጠኒት" ተብላ ተጠራለች።

አስቀድመን የዘረዘርናቸው ጉዳዮች ሁሉ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔር የሆኑትን የሚገልጡ ናቸው። ልዑል ባሕርይ እግዚአብሔር ስለ ልዕልናው በደመና ይመሰላል። ሁሉ የሚታዘዝለት አምላክ ፍጥረታትን እያዘዘ አንዱን የአንዱ አገልጋይ፣ መጋቢ፣ አስተዳዳሪ አድርጎ በፍጥረቱ ለፍጥረቱ እየመገበ፣ በፍጥረቱ ሲመሰገን ይኖራል። ይህንን ጉዳይ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት "ደመናውንም ከላይ አዘዘ፣ የሰማይንም ደጆች ከፈተ፤ ይበሉም ዘንድ መናን አዘነመላቸው፤ የሰማይንም እንጀራ ሰጣቸው" (መዝ. ፸፯÷፳፫-፳፬) በማለት ገልጦታል። አምላካችን እግዚአብሔር በቸርነቱ ፍጥረቱን ሁሉ ለዘመናት ሲመግብ የኖረው፣ ዛሬም ፍጥረታትን የሚመግበው ስጦታው የማያልቅ፣ መግቦቱ የማይቋረጥ በመሆኑ ነው።

አምላካችን እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ደመናውን እያዘዘ ይመግብ እንደ ነበረ ዛሬም በጥምቀቱ ልጅነትን አድሎ፣ በሥጋውና በደሙ የእርሱ አካል አድርጎ፣ በቸርነቱና በመግቦቱ ምግበ ሥጋውን፣ ምግበ ነፍሱን አዘጋጅቶ፣ የእናት አማላጅ ድንግል ማርያምን "እነኋት እናትህ" (ዮሐ. ፲፱፥፳፯) በማለት ተጥቶናል። የጭንቅ ቀን ደራሽ የመዳን ተስፋ ሰጥቶ፣ ብንበድለው እንኳን የአባት ስጦታ ንስሓን አድሎን በየዕለቱ ይመግበናል። ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ እንካችሁ ብሉ ጠጡ ብሎናል።

### ማጠቃለያ

መግቦቱ ዕለት ዕለት የማይቋረጥበት አምላክ የእውነትን ቃል የመዳናችንን ወንጌል ሰምተን፣ በክርስቶስ አምነን በተስፋው መንፈስ የርስታችን መያዣ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ የታተምን፣ አዲሱን ሰው በጥምቀት የለበስን፣ የድንግል ማርያም ልጆች ኦርቶዶክሳውያን ስለሆንን፡፡ ለቤዛም ቀን የታተምንበትን ዘወትር በቀኞችን ሆኖ እንዳንታወክ የሚደግፈንን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ ላለማስመረር፣ እንደ ደመና ዙሪያችንን የከበቡንን በቅዱሱ መንፈስ የሚመሩትን ቅዱሳንን ላለማሳዘን መራራነትንና ንዴትን፣ ቁጣንም ጩኸትንም፣ መሳደብንም ሁሉ ከእኛ ዘንድ በማስወገድ፤ እርስ በእርሳችን ቸሮችና ርኅሩኆች ሆነን ይቅር ልንባባልና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልጆች መሆናችንን በቀሪው ዘመናችን ልናረጋግጥ ይገባናል። ንስሓ ገብተን ሥጋ ወደሙን ተቀብለን የመንግሥቱ ወራሾች የስሙ ቀዳሾች ለመሆን እንድንበቃ የአብና የወልድ ሕይወታቸው የቅዱሳን ጌጥና ሽልማት ዐምደ ደመና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ረድኤት የፈጣኗ ደመና የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን!!✥

# ሰላም እንዲሰፍን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ድርሻችንን እንወጣ

ዲ/ን አሻግሬ አምጤ

በአገራችን ላይ እየወረደ ያለው የመከራ ዝናብ የሚቆምበት ጊዜ እንደ ሰማይ እየራቀ መምጣቱን ለመረዳት እየተፈጸመ ያለውን እኵይ ድርጊት መመልከት ይበቃል፡፡ የኢትዮጵያ ጉዳይ ይገደኛል ያለ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚወስደው የመፍትሔ አሳብ የተለያየ ነው፡፡ ሁሉም በየፊናው ይጠቅማል ያለውን ይሞክራል፡፡ አንዳንዱ የሚወስደው መፍትሔ ሰላም የሚያሰፍን ሳይሆን አገርን ለበለጠ ጥፋት የሚዳርግ መሆኑን የተረዱ ወገኖች ምክረ አሳብ ቢያቀርቡለትም የሚናገር እንጂ የሚሰማ የለም፡፡ አንዳንዶች ተቆርቋሪ መስለው የተጎጂዎችን ቁስል እየነካኩ በቁስል ላይ ቁስል በመጨመር እንጀራቸውን ለመጋገር እንቅልፍ አጥተዋል፡፡ የሚሰማቸው ያጡ ጥቂት ንጹሓን ደግሞ ዘላቂ ሰላም የሚመጣበትን አሳብ ያቀርባሉ፡፡ አንዳንዱ ደግሞ በአገር ላይ መከራ ከነደደ መርጦ ያቃጥል ይመስል ሌሎችን ለማጥፋት ያግዘኛል ያለውን እሳት አቀጣጥሎ ቤንዚን ለመጨመር ይጣደፋል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት አገር በመከራ በተወጠረችበት ወቅት የሚያነዱት እሳት አቀጣጣዮችን እንደማይፈጃቸው ማስተማመኛ ዋስትና አለመኖሩን ተረድቶ አስተማማኝ ሰላም እንዲመጣ መሥራት ከኢትዮጵያውያን ሁሉ ይጠበቃል፡፡

በኢትዮጵያውያን ላይ እየተፈጸመ ያለው አሰቃቂ ግድያ ያሳሰባት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው መግለጫ ስትሰጥ፣ የተጎዱትን ስትደግፍ፣ ለመንግሥት የመፍትሔ አሳብ ስታቀርብ ቆይታለች፡፡ የሚገርመው እንዲህ ያለ መከራ እየወረደ እና ሰው በጅምላ ተገድሎ በጅምላ እየተቀበረ እያየን ኀዘን የማይሰማን መሆናችን እና ምክር ላለመቀበል "ከእኛ በላይ ላሳር" ማለታችን ነው፡፡ መከራው ይወርዳል፣ ሰዎች በማንነታቸው ይገደላሉ ጩኸት እንጂ መፍትሔው እንደ ሰማይ ርቆናል፡፡ በጥላቻ የተመረዙ አንዳንድ ባለሥልጣናት መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ አንዱን ደግፈው ሌላውን በመግፋት፣ ለአንዱ መግደያ አቀብለው ሌላውን ለማስገደል ዕረፍት አጥተዋል፡፡ ልዩነቱ እንዲሰፋ፣ አለመግባባቱ እንዲከር እየፈጸሙት ያለው እኵይ ድርጊት የሰሚን ጆሮ ይሰቀጥጣል፡፡

ለጥፋት የተሰለፉ ባለሥልጣናት ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ባለመደረጉ ሰው በጅምላ ሲጨፈጨፍ እንኳ ጩኸት እና ልቅሶው የሟቹ ማንነት እየታየ ሆኗል፡፡ ይህ ጉዳይ የት እንደሚያደርስ የሚያውቁት ጥፋቱን ፈጻሚዎች፣ ከጥፋቱ እንጠቀማለን ብለው ያሰቡ አካላት እና በመንግሥት ሥልጣን ተቀምጠው ለአጥፊዎች ሽፋን የሚሰጡት ወገኖች ናቸው፡፡ ሥልጣን የያዘ ሰው የሥልጣን ዘመኑ እንዲረዝም መልካም ሥራ ይሠራል እንጂ በራሱ ላይ ጥፋት የሚያውጀው የዘመናችን ባለሥልጣን ድርጊት የሚያስገርምም ምን ተልእኮ ቢኖረው ይሆን ብሎ ለመጠየቅ የሚያስገድድም ነው፡፡

በዘመናችን ነቢዩ ኤርምያስ "የመቅደሱ ድንጋዮች በጐዳና ሁሉ ራስ ተበተኑ" (ሰ. ኤር.፬÷፩) በማለት የተናገረው ትንቢት ብቻ ሳይሆን በመቅደሱ አምልኳቸውን የሚፈጽሙ ክርስቲያኖች፣ ከጭፍጨፋ ይታደገናል ብለው የተጠጉት መስጊድ ከሞት አልታደጋቸው ያሉ ሙስሊም ወገኖቻችን እና የሌላ እምነት ተከታይ ወገኖቻችን አስከሬን በየጎዳናው እየወደቀ፣ በእየጥሻው እየተገኘ፣ የሟች ሬሳ ሜዳ ውሎ ማደር በመለመዱ የሰው ልጅ በጅምላ መቀበርም ብርቅ እየሆነ መምጣት ጀምሯል፡፡ እንዲህ ያለው ዘግናኝ ድርጊት የሰውን ልጅ አንጀት ማራራት ተስኖት የሰዎች ኀዘን ለሌሎች እንጀራ መጋገሪያ፣ የአንዱ ኀዘን ለሌላው ፌሽታ ከሆነ ዓመታት ተቈጠሩ፡፡

እንዲህ ያለው ቃላት የማይገልጡት እኩይ ድርጊት ያሳሰባቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ በወለጋና በጋምቤላ የተፈጸመውን አሰቃቂ የጅምላ ጭፍጨፋ አስመልክተው ሰኔ ፲፯ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ባስተላለፉት መልእክት "ስሜትን በሚወርር፣ ልብን በሚያሳዝን፣ ጉልበትን በሚሰብር ኀዘን ውስጥ ላሉት ወገኖቻችን፤ ትናንት ባለ ብዙ ቤተሰብ ዛሬ ሌጣ ለሆኑት፣ የክብር ሞትና መቃብር ለተነፈጉት፣ ሰው ሆነው በሰው ለተገፉት፣ ኢትዮጵያዊ ሆነው በኢትዮጵያውያን ለተሠውት፣ አገር እያላቸው እንደ ባዕድ ለተቈጠሩት ለደከሙበት ምድር በወርቅ ፈንታ ሰይፍ ለተከፈሉት ልጆቻችን እግዚአብሔር ያጽናችሁ፣ የሞቱትንም ደመ አቤልን ያከበረ አምላክ ደማቸውን እንዲመራመር እንለምናለን" ብለዋል፡፡ እንዲህ ያለው አባታዊ መልእክት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለሰው ልጅ ሁሉ የሚገዳት እንጂ ቋንቋ ዓይታ፣ ዘር መርጣ የማታዝን ለመሆኗ ማሳያ ነው፡፡ ቅዱስነታቸው በመልእክታቸው እንደ ገለጡት ከዚህ በላይ ልብን የሚሰብር፣ ስሜትን የሚወርር ኀዘን አገራችንን ገጥሟት አያውቅም፡፡ የሰውን ዘር የሚተኩ እናቶች፣ አድገው ለአገር ተስፋ የሚሆኑ ሕፃናት የጥቃቱ ዒላማ መሆናቸው ደግሞ ኀዘናችንን የበለጠ መራር አድርጎታል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተጠናከረ መልኩ በተለይም ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በተደጋጋሚ ሲፈጸም የነበረው የኦርቶዶክሳውያን ጭፍጨፋ አሳስቧት ስታስጠነቅቅ የቆየችው እንዲህ ዓይነቱ ጅምላ ፍጅት እንዳይፈጸም ነበር፡፡ በእንግዳ ተቀባይነታችን እና "በአንተ ትብስ አንተ ትብስ" መባባላችን ዓለም ያውቀን የነበርን ኢትዮጵያውያን ወልዳ የተኛች አራስ ከማንምርበት የጭካኔ ዳርቻ ላይ ደረስን፡፡

በየትኛውም ሃይማኖት እና በብዙ ኢትዮጵያውያን ጎሣዎች ባህል ሴትንና ልጅን መግደል ቀርቶ መገላመጥ ጸያፍ ነበር። በዘመናችን ዋናዎቹ ተጠቂዎች ሴትና አዳጊ ሕፃናት መሆናቸው አገራችንን ያለ ተተኪ ለማስቀረት እየተሠራ ያለ ድብቅ አጀንዳ መኖሩን እንድንመረምር ያደርገናል።

ኦርቶዶክሳውያንን ብቻ ዒላማ አድርጎ ይፈጸም የነበረው ጥቃት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሌሎች እምነት ተከታዮችን ወደማጥቃት ተሸጋግሯል። እንዲህ ዓይነት ጥቃቶች በቶሎ መፍትሔ ካልተበጀላቸው በአገራችን ላይ ከዚህም የከፋ አደጋ ሊደርስ እንደሚችል ለመረዳት ነቢይነትን አይጠይቅም። መንግሥት ለተከሠቱ ችግሮች መፍትሔ እንደሚሰጥ፣ አጥፊዎችንም ለሕግ እንደሚያቀርብ ደጋግሞ ቢገልጥም ተግባራዊ ስላልተደረገ ከሁለት ዓመት በፊት የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎ በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ አንዱ መርማሪ ሌላው መስካሪ እየሆኑ ኦርቶዶክሳውያን በእስር እንዲማቅቁ እንዳደረጓቸው እማኞች የገለጡት መልኩን ቀይሮ እና አድማሱን አስፍቶ የኢትጵያውያንን ሁሉ በር ወደ ማንኳኳት ተሸጋገረ። አጥፊዎች ወደ ሕግ አለመቅረባቸው እና አጥቂው ቀርቶ ተጠቂው ለተጨማሪ አደጋ መዳረጉ ለአጥፊዎች የልብ ልብ እየሰጠ በጥፋት ላይ ጥፋት እንዲፈጽሙ ሲያደርግ ተጠቂዎችም ራሳቸውን ለመከላከል በሚያደርጉት ሙከራ ወደ እርስ በርስ ፍጅት እንዳንገባ የችግሩን ውስብስብነት ደጋግሞ ማጤን አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው ብለን እናምናለን።

አጥፊዎችን ለሕግ አለማቅረብ በአንድ በኩል ከአጥፊዎች ጋር መተባበር ሲሆን በሌላ በኩል ንጹሓን ተደራራቢ ግፍ እንዲፈጸምባቸው መተባበር ነው። እንዲህ ያለው እኩይ ድርጊት የአገራችንንም አሁን በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ገጽታም ስለሚያጠለሽ ስምን የሚያድስ፣ ተጎጂዎችንም የሚክስ ተግባር መፈጸም ከመንግሥት ይጠበቃል። ጥቃቱ እና ግድያው በዚሁ ከቀጠለ ንጹሓን ወጥተው ለመግባት እየተሳቀቁ መኖር ሲሰለቻቸው የአጥፊዎችን የጥፋት መንገድ እንዲከተሉ በር መክፈት በመሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። ኢትዮጵያውያንም በለው ፍለጠው በማለት ትውልድ የሚያጨራርስ ተግባር ከመፈጸም ወጥተን ትውልድ የሚያሻግር ተግባር ለመፈጸም የሚጠበቅብንን መሥራት ይኖርብናል። አገርን ማልማት እና ሰላምን ማስፈን ጊዜ ከመውሰድ በተጨማሪ በጣም ያደክማል እንጂ አገርን ማፍረስ እማ ደቂቃም ይበቃል። ንጹሓንን አጥፍቶ ከሚገኝ ስኬት እና ደስታ ይልቅ አማናዊ ሰላምን ለማስፈን የሚከፈል መሥዋዕትነት የሚያስገኘው ዋጋ የሚያስገኘውን ውስጣዊ ሰላም ቃላት አይገልጡትም። የኑሮ ውድነቱ ጣራ መንካት አእምሮውን ያዞረውን ኢትዮጵያዊ ለአራት ዓመት ያለማቋረጥ የቀጠለው የእርስ በርስ ፍጅት ተጨምሮበት በጨለማ ላይ ጥላ እንደ መደረብ ነው።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የጸጥታ እና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል ሰኔ ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በሰጠው መግለጫ "ሽብርተኞችን በሁሉም አካባቢ የመቈጣጠር እና ሕግ ማስከበር ሥራ እየሠራ" መሆኑን ገልጧል። ይህ በተግባር ተተርጕሞ መታየት ከቻለ አገራችን ሰላም ውላ ለማደር ኢትዮጵያውያንም ወደ ቀደመ መተባበራቸው ለመመለስ ጊዜ አይፈጅባቸውም። በእርግጥ በዚህ ወቅት አገራችን እሳት እየነደደባትም እንደ ሌሎች ፈጽማ ያልተበታተነችው ቀደምት አባቶቻችን እና የሃይማኖት ተቋማት አማኞቻቸውን በሥነ ምግባር ሲያንጹ በመኖራቸው ነው። አሁን አሁን ግን ሌላውን አጥፍተን ለመኖር የምናደርገው መፍጨርጨር ሁላችንንም ለማጥፋት ወደ ሚገፋ መከራ እየመራን ነው። ሽብርተኞችን በሁሉም አካባቢ የመቈጣጠር ተግባር ከተፈጸመ ጅምላ ጭፍጨፋው ለምን ቀጠለ የሚል ጥያቄ ስለሚያስነሣ የተነገረው በተግባር መገለጥ ይገባዋል።

ቅዱስነታቸው በኀዘን መግለጫ መልእክታቸው "ብዙ መልካም ቃላት በሚነገሩበት፣ የጥበብ ድምፆች በሚያስተጋቡበት፣ መሠረተ ፈርሶ ለጉልላት ጌጥ በምንጨነቅበት በዚህ ዘመን፣ 'እንዴት ካለው ጊዜ ደረስን ማለት መመጻደቅ ባይሆን ኖሮ የሚባልበት ወቅት ሁኖ አግኝተነዋል። ትናንት ገንዘብን የሚቀሙ እንዴት የሰውን ልፋት ይወስዳሉ ተብለው በተወገዙበት ምድር ሕይወትን የሚቀሙ፣ የሰው ዘር ቅነሳ የሚያደርጉ ግፈኞች ሲንጎማለሉ ማየት ያሳዝናል። ንጹሓን ወገኖቻችን እግዚአብሔር በሰጣቸው ማንነት ብቻ ሲሞቱ ስናይ የዘቅታችንና የመውደቃችን ልክ ማጣት ጎልቶ ይታያል" በማለት የገለጡትን አስበን ሁላችንም ወደ ሰላማዊ ሕይወት መመለስ ይኖርብናል። ይህ ብቻ ሳይሆንም እኛ ስናጠፋ ምክንያት ያለን ሌላው ሲያጠፋ አገር ለማፍረስ አስመስለን የምንነዛውን ፕሮፓጋንዳ ትተን ለሰላም መስፈን ሁላችንም የሚጠበቅብንን መሥራት ይኖርብናል። ተግባራዊ ሥራ መሥራት እንጂ ምክንያት መደርደር ለአገራችንም፣ ለሕዝባችንም ዋስትና ስለማይሆን ጣት መጠቋቆሙን በመተው የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማከናወን እየተመካከርን የሚበጀውን መሥራት ነው።

ቅዱስነታቸው "ወገኖቻችን እግዚአብሔር በሰጣቸው ማንነት፣ ለምን እንዲህ ተፈጠራችሁ ተብለው የሞቱ ናቸውና ሰማዕታት እንላቸዋለን። ገዳዮችም ቀጥተኛ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች ናቸው" በማለት የገለጡት ትኩረት የሚሻ ነጥብ ነው። መንግሥት በሌሎች አገራት የሚገኙ ስደተኞችን ወደ አገራቸው መልሶ እያቋቋማቸው መሆኑን እያየን ነው። በአገር ውስጥ ለሚፈናቀሉትም ድጋፍ ሊያደርግላቸው ትክክለኛው ሰላም ሰፍኖ ኢትዮጵያውያን የሰው እጅ ከማየት ተላቀው ሠርተው እንዲበሉ ማገዝ ይኖርበታል። የሃይማኖት ተቋማት የሚያግዙትን ጉዳይ ለይቶ በመስጠትም በቤተሰብ ሞት ያዘኑት እንዲጽናኑ፣ የተሰደዱት እንዲመለሱ፣ የተበተኑት እንዲሰበሰቡ ማድረግ ይገባዋል። በዚህ ወቅት ጣታችንን ወደ ሌላ መቀሰሩን ትተን መፍትሔ ፍለጋ መድከም ይኖርብናል። ምክንያት አዳምንና ሔዋንን ወደ ምድረ ፋይድ ከመውረድ እንዳላዳናቸው ምክንያት መደርደርም በታሪክ ተወቃሽ በአምላካችን ፊት ተጠያቂ ከመሆን አያድነንም።

### ችግሩን ለማስቆም ከመንግሥት የሚጠበቀው ተግባር

ከመንግሥት የሚጠበቀው የመጀመሪያው ተልእኮ "ሀገራዊ

ሰላም የሚገኘው በሰዎችና በሰዎች መካከል ኅብረት ሲኖር በመሆኑ መንግሥት በዜጎች መካከል ለጥላቻ፣ ለአለመግባባትና ለመለያየት ምክንያት የሚሆን በሰላምና በትዕግሥት በመቻቻልም ጭምር ለመኖር የማያስችሉ ድርጊቶችን ጊዜ ሳይሰጥ ከኅብረተሰቡ መካከል ነቅሶ ማስወገድ ይኖርበታል። ከዚሁ ጋር የዜጎች ሰላምና አንድነት የሚጠበቅበትን ሥራ ባለማቋረጥ ማከናወን የሚገባው መሆኑን ልናሳስብ እንወዳለን። በቀጣይም በየትኛውም የአገራችን ክፍሎች እንዲህ ዓይነት የጥፋት ድርጊት እንዳይደገም አስፈላጊው የዜጎች ጥበቃ እንዲደረግ አጥብቀን እናስገነዝባለን” በማለት ቅዱስ ሲኖዶስ ሰኔ ፲፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም የገለጠውን ተግባራዊ ማድረግ ነው።

የመንግሥት ባለ ሥልጣናት በጅምላ ጭፍጨፋ የተጎዱ ወገኖቻችንን ችግሩ ከተፈጸመበት አካባቢዎች ድረስ ሔደው ወገኖቻችን በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ መጎብኘት የመጀመሪያው ተግባራቸው ሊሆን ይገባል። ባለ ሥልጣናት የወገኖቻቸውን ጉዳት ለማየት ሲሔዱ ተሰሚነት ያላቸውን የሃይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ወገኖቻችንን ሊረዱ የሚችሉ ባለ ሀብቶችን ይዘው ቢሔዱ ተግባራዊ ሥራ መሥራት ይችላሉ። የደረሰውን ጉዳት በዓይን ከማየት በተጨማሪ የተጎዱትንም ማጽናናታቸው በመከራ ላይ ለሚገኙ ወገኖቻችን ተስፋቸውን ያለመልመዋል።

የመንግሥት ባለሥልጣናት እና የልዩ ልዩ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ሄደው ወገኖቻቸውን ማየታቸው የችግሩን ጥልቀት ተመልክተው መፈጸም የሚገባቸውን ለመለየትም ያግዛቸዋል። የተጎዱትን በገንዘብ፣ በቊሳቊስ፣ በምግብ እህል መደገፍ የሚቻለው ባለሥልጣናት አካባቢውን አይተው ምቹ ሁኔታ መፍጠር ሲችሉ ነው። የጎደለውን ከሞላው ለመለየት፣ አካባቢው አስተማማኝ ሰላሙ መመለስ አለመመለሱን ለማረጋገጥ በሪፖርት ከመስማት ሄዶ ማየት ፍቱን መድኃኒት ነው። የተጎዱትን ሕመማችሁ ሕመማችን፣ ጉዳታችሁ ጉዳታችን በመሆኑ ልናያችሁ መጣን ቢሏቸው የደረሰባቸውን ረስተው አዲስ ሕይወት ለመጀመር ይነሣሣሉ። ባለሥልጣናት እና የሃይማኖት አባቶች ሄደው ማጽናናታቸው የተጎዱትን ወገኖቻችንን ሥነ ልቡናዊ ስብራት ይጠግናል።

ከቦታው ተገኝተው ችግሩን ማየታቸው ተጎጅዎች የሚያስብልን ወገን አለ ብለው ተስፋቸው እንዲለመልም ያደርጋል። “ችግራችሁን አይተናል መንግሥት ይህን ያደርግላችኋል” ቢሏቸው የአብዛኛውን ማኅበረሰብ ሥነ ልቡና ሲያክም በጣም የተጎዱትም “ይህን ክረምት እንዴት ልናሳልፈው ነው? ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን?” ብለው ለተጨማሪ ጭንቀት እንዳይዳረጉ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በጭፍጨፋውም ሆነ በሌላ ምክንያት ቀያቸውን ለቀው የተሰደዱትን፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ለችግር የተጋለጡትን ወገኖች የቋንቋም ሆነ የመልክአ ምድር ወሰን ሳናደርግ መርዳት ከኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚጠበቅ ተግባር እና ኃላፊነት ነው። ይህም በቅዱስ ወንጌል “እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን እንግዲህ በምን ይጣፍጣል? እንግዲህ የሚጠቅመው የለም። ሰዎች አውጥተው ይጥሉታል። በእግራቸውም ይረግጡታል እንጂ። እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ ላይ የተሠራች ከተማ መሰወር አይቻላትም” ተብሎ የተነገረውን እና ብራብ አብልታችሁኛል፣ ብጠማ አጠጥታችሁኛል የተባለውን አምላካዊ ቃል በተግባር መፈጸም ማለት ነው። ራሳቸውን ከአደጋ ለማትረፍ የሚሰደዱትን ወገኖቻችንን መርዳት የሚያስገኘው ዋጋም አስቀድሜ ከጠቀስኩት ቢበልጥ እንጂ አያንስም።

ክርስቲያኖች ብቻ ሳንሆን ኢትጵያውያን ሁሉ አልጫውን ዓለም ማጣፈጥ፣ ጨለማውን ዓለም ማብራት የምንችለው ለወገኖቻችን መልካም ስናደርግ፣ የተጎዱትንም ስንረዳ ነው። በዚህ ወቅት መልካም ማድረግ ሰብአዊ ብቻ ሳይሆን አገራዊ ግዴታችን ጭምር ነው። ገብር ሐካይ መሆን እና ራስ ደኅና ብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ተባርዮን የማያስቀር አምላክ መከራውን ወደ ቸልተኞች ያዞረው እንደሆነ የሚደርስላቸው አያገኙም። የክርስቲያኖች ብርሃንነትና የምድር ጨው መሆን የሚገለጠው ሠርተው ራሳቸውን ከመቻል አልፈው ለሌላቸው ወገኖቻቸው ሰጥተው ችግራቸውን ማቃለል ሲችሉ፣ ሕይወታቸው እንድትቀጥል ምክንያት ሲሆኑ ነው። ገንዘብ፣ ዕውቀት፣ ጥበብም ሆነ ለተቸገሩ ሰዎች የሚያስፈልጋቸው ሌላ ነገር ያላቸው ሰዎች ለሌላቸው መስጠት ሲችሉ ከአምላካቸው በረከት ከማግኘት በተጨማሪ መልካም በማድረጋቸው ውስጣዊ ሰላምን ያገኛሉ።

በዚህ የመከራ ዘመን ሀገር ለቀው ለተሰደዱ፣ በችግር አሽክላ ታስረው ለሚሠቃዩ፣ ረኃብና ኀዘን ተጨምሮባቸው ለሚሠቃዩ ወገኖቻችን ያልደረስን መቼ ልንደርስላቸው ነው? የትሩፋት ተግባር ለመፈጸም የተነሡ ሰዎች ለራሳችን ይቅርብን ብለው ወገናቸውን ሲያስቀድሙ እኛ ደግሞ ቢያንስ ካለን በማካፈል ለወገን አለኝታነታችንን ማረጋገጥ ከኢትዮጵያውያን ሁሉ ይጠበቃል። ቅዱስ ፓትርያርኩ “የሃይማኖት አባቶችም የምናስተምረው ሕዝብ አልቆ ማንን ልናስተምር መሆኑን ደግመን ማሰብ ያስፈልገናል። አገራችን ኢትዮጵያ የሚያስከብሯትን መሪዎች አሁንም እየተጣራች ነውና መንግሥትና ሕዝብ ግፍን በተግባር ማውገዝ ያስፈልጋቸዋል” በማለት የተናገሩትን በተግባር እንግለጠው።

በዚህ ዘመን ለመከራ የተዳረጉ ወገኖቻችን ሥነ ልቡና ተስተካክሎ የተሻለ ሕይወት እንዲመሩ ባለሥልጣናት፣ የሕክምና ባለሞያዎች፣ የሥነ ልቡና ሰዎች፣ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ተመርጠው የሚላኩ መምህራነ ወንጌልና ካህናት በመተባበር መሥራት ይገባቸዋል። እነዚህ አካላት ችግር ወደ ተከሠተባቸው ቦታዎች በመሄድ ለመከራ ከተጋለጡት ጋር አብረው ውለው እያደሩ አንዱ የጀመረውን ሌላው ከፍጻሜ እያደረሰ የቈሰለውን የማኅበረሰባችንን ሥነ ልቡና አክመው ማስተካከል ይችላሉ።

ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው “ቀን ያልፍልናል፣ ሕፃናት ልጆቻችንን አሳድገንና አስተምረን ለአገርና ለወገን መከታ ይሆናሉ በሚል ራእይ ማልደው እየተነሡ፣ አምሽተው እየገቡ ኑሯቸውን በረኃብ፣ በጥም፣ በራቁትነትና በሕመም እያሳለፉ የነበሩ ወገኖቻችን ይህም በዛባችሁ ተብለው አሰቃቂ ግፍና

ጭካኔ በተሞላበት ግድያ ሕይወታቸው እንዲያልፍ መደረጉ መላውን ዓለም አሳዝኗል፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነት አስከፊ ድርጊት ልማትን፣ ዕድገትና ብልጽግናን ለምትመኝ በዚህም ጎዳና ዳዴ እያለች ላለች ሀገር ቀርቶ ለሠለጠኑትና ላደጉትም አገራት የማይበጅ አሳፋሪ ድርጊት ነው፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን ድንበር ተሻግሮ የመጣ ወራሪ ጠላት በሌለበት የግል ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል በተደረገ የእርስ በርስ ግጭት መሆኑ እንደ አገር ሁላችንንም ሊያሳፍረን፣ ሊደገምም የማይገባ ድርጊት ነው፡፡ ሰላም በዓለም ላይ ለሚኖሩ የሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን ለእንስሳቱና ለአራዊቱ፣ ለምድሩም ሆነ ለሰማዩ አስፈላጊ በመሆኑ ከእንዲህ ዓይነት የጥፋት ተልእኮ መጠበቅ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ሰው ሁሉ በዚህ ዓለም ሲኖር ሠራተኛው ሠርቶ ለመበልጸግ፣ ነጋዴው ነግዶ ለማትረፍ፣ በሽተኛው ድኖ በጤና ለመኖር፣ ተማሪው ተምሮ ለማወቅ በአጠቃላይ ዜጎች ማልደው ለመውጣትም ሆነ አምሽተው ለመግባት በምድራችን ሰላም ሲገኝ፣ እርስ በርስ መተማመን ሲኖር በመሆኑ መላው ኢትዮጵያውያን ዜጎቻችን ለሰላምና ለአንድነት ተባብሮና ተከባብሮ ለመኖር እጅ ለእጅ ተያይዘን የምንነሣበት ጊዜ አሁን ነው" ብሏል፡፡

መፍትሔው ቅዱስ ሲኖዶስ እንደ ገለጠው እጅ ለእጅ ተያይዞ ችግርን መሻገር እንጂ አንዱ ሌላውን አጥፍቶ ለመኖር መሞከር አይደለም፡፡ አንዱ ሌላውን አጥፍቶ ለመኖር መሞከር አገራችንን ለባዕድ ወራሪ አሳልፎ መስጠት መሆኑን መረዳትም ታላቅነት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ከመላ ኢትዮጵያውያን የሚጠበቀውም በፍቅርና በመተሳሰብ ያለንን ተካፍለን እየበላን ለሥራ መነሣት የሚገባን መሆኑን መረዳት ይኖርብናል፡፡ በዚህ ዘመን ከሰላም የበለጠ አስፈላጊ ነገር የለም፡፡ ሁላችንም ውለን የምንገባው፣ ተኝተን የምንነሣው፣ ሠርተን የምንበላው ሰላም እና መተማመን ሲኖር ብቻ ነው፡፡✥

ከገጽ ፳፰ የዞረ

# ከዓይን ጋር የተገባ. . .

"ሀገር ጥዬ ስለመጥፋት ነው የማስበው" አልኳቸው የሞት ሞቴን፡፡ "ለምን ብለህ?" አሉኝ፡፡"ኃጢአቴ ተገልጧል፤ ሁሉም ወራዳ ይለኛል፡፡ ከእንግዲህ እዚህ ሀገር መኖር አልችልም" አልኳቸው፡፡ "ከእሷና ከእኔ በስተቀር ያወቀ የለም"፡፡ "አባቴ እንድጽናና ብለው እንዳይሆን?"፡፡ "ለዚያ ብዬ አይደለም"፡፡ "እንደዚያ ሆኜ ስታየኝ በድንጋጤ እንዴት አልጮኸችም?"፡፡ "እኔንም የገረመኝ እሱ ነው"፡፡ "ግን ለምንድነው እንደዚያ የሆንኩት?"፡፡ "መንፈስ ቅዱስ እንድትቀርባት አልፈቀደልህም"፡፡ አባ ዘግየት ብለው አከሉበት፡፡ "እናታችን እንዳንላት ልጅ ናት፡፡ ልጃችን እንዳንላት ሥራዋ የትላልቅ እናቶች ነው፡፡ የእሷ ነገር ይገርመኛል"፡፡

እኔንም እየገረመኝ ነበር፡፡ በዚህ ዕድሜ ከዚህ የጸጋ ደረጃ ላይ ትደርሳለች ብዬ በፍጹም አላሰብኩም፡፡ እንዲሁ በኀፍረት እንዳቀረቀርኩ ነበር ቤቴ የደረስኩት፡፡ ከዚያን ዕለት ጀምሮ ስለጽድቅና ኩነኔ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ምንም እንኳን ዕድገቴ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ቢሆንም የሥነ ምግባር ድሀ፣ ገብረ ሀካይ ነበርኩ፡፡ አልጋዬን ተመለከትኩት፡፡ እዚህ አልጋ ላይ ብዙ ልጃ ገረዶች ከክብር አንሰዋል፡፡ አንሶላና ፍራሼ ደማቸውን ጠጥቷል፡፡ እዚህ አልጋ ላይ የአባ ጠበል ያልደረሰበት እርኩስ መንፈስ እንዳለበት ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ከእንግዲህ እንደማልተኛበት ባውቅም መነኩሴውን አምጥቼ ቤቴን አስረጨኹት፡፡ በእስካሁኑ ኑሮዬ በሕያዋን ምድር እግዚአብሔርን ማየት እንደማልችል ግልጽ ሆኖልኝ ነበር፡፡ ገብረ ሀካይ ነኝ፡፡ ብዙ ልጃ ገረዶችን ከክብር ያሳነስኩ፣ የአምኖን ወልደ ዳዊት ልጅ፡፡ ለብዙ ሕፃናት መጨንገፍ፣ ከውርጃ ጋር ተያይዞ ለብዙ አዳጊ ሴቶች የጤና መታወክና ሞት ምክንያት ነኝ፡፡ የብዙ ልጆችን የትምህርት ዕድል የገደልኩ፣ ተስፋቸውን ያጨለምኩኝ እኩይ!

ከዚያን ዕለት ጀምሮ እንደ በግ እረኛው እንደ አባ ዕብሎይ፣ "ሰባ ጊዜ ሰባት በደልኩ፡፡ የማይበድል ባርያ የማይምር ጌታ የለም፡፡ ጌታዬ ሆይ ማረኝ" እያልኩ ሌሊቱን በሙሉ ሳለቅስና ስሰግድ አድራለሁ፡፡ ነፍሴ ከፊቴ እሳት ላይ ወድቃ ስትቃጠል እያየሁ አለቅሳለሁ፡፡ ነፍሴ በትሎች ተከባ እንደ ኢዮብ ስትጨነቅ እያየሁ አነባለሁ፡፡ ማደሪያዬ እንደ እረኛ ገሳ ተነቅላ ከእኔ ዘንድ እንደ ተወገደች፣ በሕያዋን ምድር እግዚአብሔርን ማየት እንደማልችል፣ እግዚአብሔርን ተስፋ ከሚያደርጉት፣ ካልተዳደፉት ንጹሐን፣ ሕሩያን ከሆኑት ሕዝብ ጋር መመሳሰስ እንደማልችል እያሰብኩ በኀዘን እኖራለሁ፡፡ መምህራን "ዐሥርቱን ትዕዛዛተ ኦሪትና ስድስቱን ቃላተ ወንጌል" እንድጠብቅ አስተምረውኝ ነበር፡፡ ሕጉን ገንዘብ ብታደርገው ገንዘብ ይሆንሃል፣ ብትተወው ይተውሃል ቢሉኝም አልሰማኋቸውም ነበር፡፡ ሰማይ ስሚ፣ ምድርም መስክሪ ብለው ተውኝ፡፡ አሁን ጡት ባላወጣች ታናሽ እኅታቸው እንዳፈሩት ወንድሞቿ በራሴ አፈርኩ፡፡

"እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ በቀንበርህ ተጠምደው በመስክህ ከሚታዩ፣ ከተባረኩ በጎችህ ጋር አቁመኝ፡፡ በረከት ከሚገኝበት ቦታ ለወጣሁት ለእኔ፣ አለባበሴ ለጎሰቆለው ለእኔ፣ ለተዋረደችው ነፍሴ ራራላት፡፡ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ ወደ ልጅሽ ሰርግ እንድ ገባ፣ ከወዳጅሽ ማዕድ እንድቀመጥ አድርጊኝ፡፡ በኃጢአት ማዕበል ለታወከችው ነፍሴ መረጋጋትን ስጫት፡፡ ነፍሴን በጠላት እጅ አትተያት" የዘወትር ተማጽኖዬ ሆነ፡፡

ጥሪት ስለመቋጠርና ቤት ስለመሥራት አላስብም፡፡ ከደመወዜ ከዕለት ጉርስና ከዓመት ልብስ የሚተርፈውን የድሆችን ጎዶሎ እሞላበታለሁ፡፡ ሞትን ከቀመስኩባት ከዚያች ቀን ጀምሮ ግድ ካልሆነብኝ በስተቀር ጭስ እንደ ሸተተው ንብ ከሰው እየሸሸሁ የደገኞቹን ባሕታውያን ኑሮ እኖር ጀመር፡፡ በቀሪ ዘመኔ ቆንጆ እንዳልመለከት ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፡፡✥

# የተዘነጋውን የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ እንደ ገና ማጠናከር

ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ

*ክፍል ሁለት*

የተከበራችሁ አንባብያን ባለፈው ወር ዕትማችን የማኅበራዊ አገለግሎት ምንነትና ጥቅሙን በአጭሩ ማስነበባችን ይታወሳል፡፡ የመጨረሻ ክፍል በሆነው በዚህ ጽሑፍ ደግሞ ከማኅበራዊ አገለግሎታችን ጋር ተያይዘው ያሉ ችግሮችን አስመልክተን እናቀርባለን፡፡

### በማኅበራዊ አልግሎት መፈታት የሚገባቸው ችግሮች

የቤተ ክርስያን አንዱ መሠረታዊ ተልኮዋ ሐዋርያዊ አገልግሎትን አጠናክሮ መቀጠል ቢሆንም ማኅበራዊ አገለግሎት መፈጸም ለሰው ልጅ ሁሉ ደራሽ መሆኗን፣ አስተምህሮዋን ላልሰሙት አሰምታ የሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኙ የምታደርግበት የክርስቲያኖች ምግባርና በጎ ተግባር የሚገለጥባት ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደም የክርስትና አስተምህሮ መገለጫ መሆኑን የምታሳውቅበት ነው፡፡ ሐዋርያትም ሆነ ከእነርሱ ተከትለው ዓለምን ዞረው ያስተማሩ በየመዘናቱ የተነሡ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን አማናዊው ወንጌል ለዓለም እንዲደርስ ያደረጉት በጎ ምግባራቸውን ዓይተው የተራራ ላይ መብራት የምድር ጨው እንዲሆኑ በሃይማኖት ኮትኩታ፣ በምግባር አንጻ የምታሠማራቸው መሆኗን በመግለጥ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ አገልግሎት ስትፈጽም ልዩ ልዩ ችግሮች ቢገጥሚትም ለችግሩ እጅ ሳትሰጥ ለጥፋት የተሰለፈውንም በእምነት ስትማርከው የኖረችው እውነትን በመያዟ ነው፡፡ በዘመናችን የተከሠተው አገራዊ ቀውስ ቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ አገልግሎቷን አጠናክራ ለመስጠት ዕንቅፋት ቢሆንባትም በአገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ለተቸገሩ ወገኖቻችን ሁሉ ያለምንም ምድራዊ መስፈርት ድጋፍ በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ የተከሠተው ማኅበራዊ ቀውስ አገልግሎቷን የተሟላ እና የተሳካ ባያደርገውም ሙከራዋ የብዙዎችን ሕይወት እየታደገ ነው፡፡ ማኅበራዊ አገልግሎቷ ክፍተት የሚታይበት ቢሆንም ክፍተቱን እየደፈኑ፣ የጎደለውን እየሞሉ፣ የተበተነውን መሰብሰብ፣ የራቀውን ማቅረብ ዘመኑ የሚጠይቀው የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት አንድ አካል ነው፡፡

ባለፉት አራት ዓመታት ብቻ በብዙ በሺ የሚቈጠሩ ክርስቲያኖች ቀያቸውን ለቀው፣ ንብረታቸውን አጥተው፣ ቤተ ሰባቸው ተበትኖ ተፈናቅለዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ክርስቲያን ያልሆኑ ወገኖቻችንም የስደቱ፣ የጥቃቱ፣ የጅምላ ግድያው ሰለባ በመሆናቸው እንደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያሉትን ማኅበራዊ አገልግሎት የሚፈጽሙ በጎ አድራጊዎች ተግባር የሚፈለገውን ያህል እንዳይንቀሳቀሱ እያደረጋቸው ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የችግሩ ውስብስብነት ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ ጉዳት ለደረሰባቸው ሁሉ መድረስ አልተቻለም፡፡ እንዲህ ያለው ውስብስብ ችግር ከሥሩ የሚነቀልበትን ተግባር ማከናወን እንጂ ወገኖቻችን ከተፈናቀሉ በኋላ ለመደገፍ መሞከር ውጤት አለማስገኘቱን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

ወገኖቻችን ለፍተው ያጠራቀሙት ንብረት በደቂቃ ውስጥ አመድ ይሆናል፡፡ ጥረው ግረው ያፈሩት ሀብታቸው የእሳት እራት እየሆነ ከረጅነት የሰው እጅ አይቶ ወደ ማደር እየተሸጋገሩ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ለተቸገሩ ቀደው ያለብሱ፣ ቆርሰው ያጎርሱ የነበሩ ደጋግ ኦርቶዶክሳውያን ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የጥቃት አድራሾች ሰለባ መሆናቸው የአገርን ገጽታ ከማጥፋቱም ባሻገር ለቤተ ክርስቲያንም፣ ለመንግሥትም፣ ለረድኤት ድርጅቶችም ሸክሙን አክብደባቸዋል፡፡ ችግሩ በዚህ ከቀጠለ ላንቋቋመው ስለምንችል የሚገባው የችግሩን ምንጭ ማድረቅ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ቀዳሚው ሚና የመንግሥት ቢሆንም ከሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ግዴታ እና ኃላፊነት መኖሩን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ ቀውስ የሚያስከትሉ እኩይ ድርጊቶች እንዲወገዱ አጥብቃ ልትሠራ ይገባል የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ ምክንያቱም ችግሩ የሚያስከትለው መዘዝ ለአገርም፣ ለቤተ ክርስቲያንም ስለሚተርፍ ነው፡፡ ሰኔ ወር ፳፻፲፪ ዓ.ም በመላው ኦሮምያ ሊባል በሚችል መልኩ የደረሰው የሰው ሕይወት መጥፋት እና የንብረት ውድመት ደማቅ የነበሩትን የሻሸመኔ እና የዝዋይ ከተሞችን እንዴት እንዳወደማቸው የሚታወቅ ነው፡፡ የፈራረሱትን የከተሞችን የንግድ ተቋማት መልሶ ለመገንባት የወጣው ገንዘብ ለሌላ ዓላማ ቢውል የአገር ኢኮኖሚ ያሳድግ ነበር፡፡ ወደፊትም የሚገባው እንዲህ ያለው ጥፋት እንዳይደገም መሥራት፣ ከደረሰም በቶሎ ለማስቆም መሞከር ነው፡፡

### ፩. የሕዝብ መፈናቀል ያስከተላቸው ማኅበራዊ ቀውሶች

ከጥቅምት ፲፪ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ፳፻፲፪ ዓ.ም በዶዶላ፣ በሻሸመኔ፣ በሐረር፣ በጭሮ፣ በአዳሚ ቱሉ፣ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በምሥራቅና ምዕራብ አርሲ ሀገረ ስብከት ሥር በሚገኙ ቦታዎች በሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን ላይ ተከታታይ ጥቃት ተፈጽሟል፡፡ በዚህ ጥቃት የወደመው የኦርቶዶክሳውያን ንብረት ተጠብቆ ቢሆን ኖሮ አገራችንን በሰው ኃይል፣በምጣኔ ሀብት፣ በመሠረተ ልማት እና በሌሎችም ዘርፎች የበለጸጉ አገሮችን እጅ ከማየት ይታደጋት ነበር፡፡ በኦርቶዶክሳውያን ላይ ብቻ በተፈጸመው ጥቃት ወደ ፫ ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት መውደሙን ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ የሌሎች ቤተ እምነት ወገኖቻችን ንብረት ውድመት ሲታከልበት ደግሞ አገራችንም ሆነች ሕዝባችን ወገን በወገኑ ላይ በሚፈጽመው ጥቃት ብቻ ምን ያህል ሀብት ንብረታቸውን እያጡ እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡

አስቀድሞ በተጠቀሱት አካባቢዎች በተፈጸሙ ተከታታይ ጥቃቶች በሺህ የሚቈጠሩ ወገኖቻችን በሞት ሰማዕትነት ተቀብለዋል፡፡ በስደት እና በረኃብ ሰማዕትነት እየተቀበሉ ያሉትን ወገኖቻችንን ቍጥር ከጨመርነው ከሚሊዮንም ያልፋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሚፈጸመው ጥቃት ምክንያት መከራውን መቋቋም የተሳናቸው ወገኖቻችን ወልደው ከብደው፣ ወጥተው ወርደው ሀብት ንብረት

አፍርተው፣ ከብረው የኖሩበትን ቀያቸውን ለቀው፣ ቤተ ሰባቸውን በትነው ወደማያውቁት አካባቢ እየተሰደዱ ነው፡፡ እንዲህ ያለው ድርጊት ማኅበራዊ ቀውስ የሚፈጥረው ጥቃቱ በተፈጸመበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን ተፈናቅለው ሄደው በሚያርፉበት አካባቢ ጭምር ነው፡፡

እንዲህ ዓይነት የአገርን ገጽታ የሚያበላሽ፣ ኢትዮጵያውያን እንታወቅበት የነበረውን መተሳሰብ እና የእንግዳ ተቀባይነት በጎ ዕሴት የሚያጠለሽ መጥፎ ተግባር ማቆም የምንችለው ኢትዮጵያውያን ሁሉ ድርጊቱን ከመቃወም አልፈን ከአጥፊዎች ጋር ላለመተባበር እና የእነርሱ የጥፋት ተባባሪ ላለመሆን ስንወስን ነው፡፡ መወሰን ብቻውን በቂ ባለመሆኑ ውሳኔያችንን በተግባር መግለጥም ዋናው ተግባራችን ሊሆን ይገባል፡፡ በአገራችን እና በሕዝባችን ላይ የመከራ ዶፍ ሲወርድ ጉዳዩን የአንድ ሰሞን መነጋገሪያ አድርጎ ከማለፍ የዘለለ ዘላቂነት ያለው ችግር ፈችና የማያዳግም መፍትሔ መስጠት ካልቻልን ሥራችን የሚደርሰውን መከራ እያወራን፣ የሞቱ እና የተሰደዱ ወገኖቻችንን ጉዳት እየተናገርን መቅረታችን ነው፡፡ ለሕይወታችው ዋስትና የሚሆን ነገር ካልፈጸምን ማውራታችን ፋይዳ እንደሌለው መረዳት ይኖርብናል፡፡ ወሬያችን ፋይዳ የሚኖረው የችግሩን ጥልቀት ተረድተን ወደ ሥራ እንድንገባ መቀስቀስ ከቻለ ብቻ ነው፡፡

የችግሩን ምንጭ በአግባቡ ተረድተን በማያዳግም ሁኔታ የምንፈታበትን ስልት መንደፍ ቀዳሚው ተግባር ነው፡፡ ለችግር የተጋለጡ ወገኖቻችን ከገጠማቸው አሰቃቂ ሕይወት የሚወጡበትን መንገድ፣ በመከራ የቆሰሉት ወገኖቻችን ከቁስላቸው የሚያገግሙበትን ተግባር መፈጸም ለነገ የማይባል የሁሉም ኢትዮጵያውያን ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡ ወገናችን በመከራ እየተሰቃየ እያየን ምን አገባኝ ብለን እጃችንን አጣጥፈን የምንቀመጥ ከሆነ ችግሩ በእኛ ላይ ቢከሠት የሚደርስልን አናገኝም፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ለተቸገሩ ወገኖቻቸው የማይራሩ ተብለን የዓለም መዘባበቻም እንሆናለን፡፡ በተጠቀሱት አካባቢዎች ብቻ ሳይሆን በሰሜን ኢትዮጵያ በተከሠተው ጦርነት ለመከራ የተዳረጉት ወገኖቻችን ብዛት ይህን ያህል ነው ለማለት ከማንችልበት ደረጃ ደርሰናል፡፡ ጦርነቱ ክርስቲያኖችን ብቻ ሳይሆን ጥንታውያን ገዳማትን፣ ጉባኤ ቤቶችን፣ አብያተ ክርስቲያናትን፣ እንዲሁም የሌሎች እምነት ተከታዮችን እና ቤተ እምነታቸውንም ለጉዳት ዳርጓል፡፡ በጦርነቱ የደረሰው ጥፋት እንዲህ ነው ብሎ መግለጥ ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

ጦርነቱ የሕዝብ እልቂት፣ መፈናቀልና ስደትን አስከትሏል፡፡ ላለፉት አራት ዓመታት በየአካባቢው ለደረሰው ጥቃት እና ጥፋት አጥጋቢ የሆነ መፍትሔ ሳይሰጥ በመታለፉ በዚህ ዓመት ደግሞ በወለጋ፣ በምዕራብ ሸዋ፣ በሰሜን ሸዋ (ሰላሌ) ሀገረ ስብከት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አሸባሪ ብሎ በፈረጃቸው አካላት ካህናት፣ ዲያቆናት፣ ሕዝበ ክርስቲያን እና የሌሎች እምነት ተከታይ ወገኖቻችን በየዕለቱ መከራ እየተቀበሉ ነው፡፡ ወልደው የተኙ እናቶች፣ የነገ አገር ተረካቢ የሚሆኑ ሕፃናት በማንነታቸው ተመርጠው እየሞቱ ነው፡፡ ሸሽተው ማምለጥ የማይችሉ ሕፃናት፣ አረጋውያንና እናቶች በቃላት ሊገልጡት የማይቻለውን የሰቆቃ ኑሮ እንዲኖሩ እየተገደዱ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ከዐሥር ሺህ የሚበልጡ ወገኖቻችን ከወለጋና ከምዕራብ ሸዋ ተፈናቅለው በደብረ ብርሃን ከተማ ልዩ ልዩ መጠለያ ጣቢያዎች ተጠልለው ይገኛሉ፡፡ ከተፈናቃዮች መካከል ከ፱፻፺ በላይ የሚሆኑት ካህናት እና የካህናት ቤተሰቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ወገኖቻችን ከሰይፍ አምልጠው፣ ከጥይት ተርፈው ቢወጡም በቂ ድጋፍ ሳያገኙ ከእነ ቤተሰቦቻቸው በባዶ አዳራሽ ረኃብ እያሰቃያቸው ነው፡፡ የሚገርመው የችግሩን ምንጭ ተረድቶ አስተማማኝ ሰላም እንዲመጣ፣ የተሰደዱትም ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ አለመደረጉ ነው፡፡ እንዲያውም የተሰደዱት እና የተፈናቀሉት ያነሱ ይመስል አሁንም ጅምላ ግድያው ባለመቆሙ የተፈናቃዮች ቁጥር ዕለት ዕለት እየጨመረ የረድኤት ድርጅቶችም ማስተናገድ ከሚችሉት በላይ ሸክም ሆኖባቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያውያን አንድ አሳብ ሆነን መፍትሔ መፈለግ፤ የተሰደዱት ወደ ቀያቸው የሚመለሱበትን፣ ሌሎችም የማይሳደዱበትን እና ለተጨማሪ መከራ የማይዳረጉበትን ተግባር መፈጸም ካልቻልን ችግሩ አይወገድም፡፡

ጦርነቱ ባስከተለው መፈናቀል በዋግኽምራ እና አካባቢው ከ፺ ሺህ በላይ ተፈናቃዮች በተመሳሳይ ሕይወት እየተሰቃዩ እንደሚገኙ ይነገራል፡፡ ይህ ሁሉ የሚያስገነዝበው የችግሩን ሥር መስደድ ነው፡፡ ችግሩ ሥር ከሰደደ ደግሞ በቀላሉ ሊነቀል ስለማይችል ከችግሩ ጋር ከመታገል ይልቅ ምንጩን ፈልጎ ማግኘት ቀዳሚው ተግባራችን ሊሆን ይገባል፡፡ የችግሩን ምንጭ ከተረዳን በኋላ ደግሞ ሥራ ተከፋፍለን፣ እና ኃላፊነት ወስደን ሥሩን ለመንቀል መረባረብ ይኖርብናል፡፡ አሁን የተያዘው ምክንያት ፍለጋ እንጂ መፍትሔ ፍለጋ ባለመሆኑ ምክንያት ፍለጋው መፍትሔ ለመስጠት ካልሆነ ጠቀሜታ የለውም፡፡

እነዚህ ከላይ በጥቂቱ ያነሣናቸው ችግሮች ለማሳያ የተቀመጡ እንጂ የችግሩ ስፋትና ጥልቀት እጅግ የከፋ ነው፡፡ ሐዋርያት “እምነ ርኃብ ይኄይስ ኩናት ከርኃብ ጦር ይሻላል” በማለት መናገራቸው ቢታወቅም የተፈናቀሉ ወገኖቻችን ከጦርም፣ ከርኃብም የሚታደጋቸው ጠፍቶ በመከራ ላይ መከራ እየተደራረበባቸው ነው፡፡

ክረምት ከበጋ በድንኳን ውስጥ እንደ መኖር ያለ የከፋ ሕይወት አምሳያ የለውም፡፡ ትናንት በእናት በአባታቸው እቅፍ በፍስሐና በሐሴት ይቦርቁ የነበሩ፣ በቀል የማያውቁ ሕፃናት ዛሬ ከእናቶቻቸው ጡት መድረቅ የተነሣ የላመ፣ የጣመ አጥተው ወተትና ዳቦ ሲማጸኑ ከማየትስ በላይ መኖርን የሚያስጠላ ምን ክሥተት ይኖር ይሆን?

በወገናቸው ላይ አስጨናቂ መከራ በሚያደርሱ አካላት ላይ መንግሥት የማያዳግም ርምጃ መውሰድ፣ ሕዝቡም ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ይህ ሁሉ ችግር የደረሰው በበቂ ሁኔታ ዝግጁ ሆኖ፣ ለማኅበራዊ ቀውሶች የሥጋት ቅድመ ትንተና ሠርቶ ተግባራዊ ምላሽ የሚሰጥ በተገቢ ሁኔታ የተደራጀ አካል ባለመኖሩ ነው፡፡ ችግሩ እየተወሳሰበ እንደ ሄደ ለመረዳት የሚፈልግ አካል ከጅጅጋ በሰሜን ኢትዮጵያ እስከ ተካሄደው ጦርነት የደረሰውን በሚገባ መመርምር ይችላል፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም የደረሰውን ችግር በዘላቂነትና ስልታዊ በሆነ አግባብ

የሚፈታ አደረጃጀት መፍጠር እና አሠራር መዘርጋት ያለባት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ መፍትሔ ሰጭ አመራር ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

**ትናንት በእናት በአባታቸው እቅፍ በፍስሐና በሐሴት ይቦርቁ የነበሩ፣ በቀል የማያውቁ ሕፃናት ዛሬ ከእናቶቻቸው ጡት መድረቅ የተነሣ የላመ፣ የጣመ አጥተው ወተትና ዳቦ ሲማጸኑ ከማየትስ በላይ መኖርን የሚያስጠላ ምን ክሥተት ይኖር ይሆን?**

### ፪. ትኩረት ያልተሰጠው የትምህርት ዘርፍ ማኅበራዊ አገልግሎት

በመደበኛው የማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፍም ስንመለከት ያለንበት ቦታና ሁኔታ እጅጉን አሳሳቢ ነው፡፡ በትምህርት ተቋማት የሚታየው የሥነ ምግባር ድርቀትና ተቃርኖ ተገቢውን ትምህርት በተገቢው ቦታ ለወጣቶችና ለአዳጊዎች ካለማድረስ የመነጨ ነው፡፡ ዛሬ ላይ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ሳይቀር እንደተራ ነገር የምናየው ሥር የሰደደ ሱሰኝነት፣ ዝሙት፣ ራስን መጥላትና ተስፋ መቁረጥን መሠረት ያደረገ የሕይወት ምሬት የተፈጠረው ሰውን በተገቢ ሁኔታ በቃለ እግዚአብሔር ካለማነጻችን የተነሣ መሆኑን ማመን ግዴታችን ነው፡፡ ነቢዩ ሆሴዕ "ሕዝቤ እውቀት ከማጣት የተነሣ ጠፍቷል" በማለት የተናገረው ሕይወት፣ መድኃኒት የሚገኝበት አማናዊ ትምህርት ማጣት ሕዝብ እንደሚያጠፋ ከእኛ በላይ ምስክር ሊገኝ አይችልም(ሆሴ.፬÷፮)፡፡

### ፫. ሊታሰብበት የሚገባው የጤና አገልግሎት ዘርፍ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደዌ ሥጋን በተአምራት ደዌ ነፍስን በትምህርት እየፈወሰ ማስተማሩ ጤና ለሰው ልጆች ድኅነት ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ማሳያ ነው፡፡ ከመቶ ሃያው ቤተሰብ መካከልም ከአርድዕት ወገን ባለመድኃኒት እንደ ነበር የታወቀ ነው፡፡

በዚህ ዘርፍ ከተካኑ ደቀ መዛሙርት መካከል ሐዋርያው ቅዱስ ሉቃስ አንዱ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን በሀገር በቀል ሕክምና የዳበረና የካበተ ልምድ ቢኖራትም እንኳን ዛሬ ባይተዋር የሆነች ይመስላል፡፡ የመድኃኒት ቅመማ ጥበብ የተከተበባቸው የብራና መጻሕፍትን በድቃቂ ሳንቲም ሸጠው የራሳችንን መጻሕፍት እና ዕፀዋት ወስደው መድኃኒት ቀምመው የሚመጸውቱንን ምዕራባውያን የሚናፍቅ ትውልድ ተፈጥሯል፡፡ በዚህ ወቅት ቤተ ክርስቲያናችን በታችኛው መዋቅርና የአገልግሎት እርከን የሚገኙ አገልጋዮችና ምእመናን ቀርቶ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትን እንኳ የምታሳክምበት የእኔ የምትለው የተደራጀ የጤና ተቋም የላትም፡፡ በእርግጥ በዚህ ዓመት የግንቦት ርክበ ካህናት የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ላይ ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የተወሰነው ውሳኔ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡

አፈጻጸሙ የመግለጫ ግብዓት ብቻ ሆኖ እንዳይቀር የሁላችንንም ርብርብ ይጠይቃል፡፡ በተለይ ደግሞ የጤና ባለሙያዎች ሙያቸውን መሥዋዕት ለማድረግ ያልተቋረጠ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ እነዚህ ሁሉ የማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፎች ችግሮቻችን በዘላቂነት እንዲፈቱ በግልም በቡድንም፣ እንደ ተቋምም ያላሠለሰ ጥረት ማድረግ ተገቢ መሆኑን መግለጥ እንወዳለን፡፡ ለጠቀስናቸውና ላልጠቀስናቸው ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ወሳኙ ጉዳይ ተባብሮ መሥራት ነው፡፡ ለችግሩ የራስን ድርሻ ለመወጣት ከምንችልባቸው ተግባራት አንዱ ከማኅበረ ቅዱሳን ሙያና ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ ጋር ተባብሮ እና ተደጋግፎ መሥራት መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን፡፡ በዚህ ጽሑፍ በዚህ አስጨናቂ ጊዜ የችግሩ ፈጣሪ እገሌ ነው በማለት ጣታችንን ወደ ሌሎች ከመጠቆም ይልቅ ወገንን ከመከራ የሚታደግ ተግባር መፈጸም የሚገባ መሆኑን ማስገንዘብ እንፈልጋለን፡፡✤

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡*

# ከወላይታ ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት እስከ ጦመ ግራር

**የመጨረሻ ክፍል**

**ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን**

የተከበራችሁ አንባብያን "ከወላይታ ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት እስከ ጦመ ግራር" በሚል ርእስ ተከታታይ ጽሑፍ ስናስነብባችሁ መቆየታችን ይታወቃል። የመጨረሻውን ያቀረብነው በሚከተለው መልክ ነው።

ጦመ ግራር አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ልዩ ልዩ ገቢረ ተአምራት ሲያደርጉበት የኖረ ቅዱስ ቦታ ነው። የወላይታው ንጉሥ ሞተለሚ አሽከሮቹን ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ወስደው ገደል እንዲጥሏቸው ያደረገበት ቦታ በመሆኑ በጻድቁ ተባርኳል። ወታደሮቹ በቀፎ ውስጥ አድርገው ተሸክመው ወስደው ከገደሉ አፋፍ ቀርበው ሲጥሏቸው መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ከገደል አውጥቶ ከንጉሡ ፊት ያቆማቸው ነበር። ተአምር መሆኑን ያልተረዳው ንጉሥም በጣም እየተበሳጨ ሌሎችን አሽከሮች በመላክ እንዲጥሏቸው ያደርግ ነበር።

በተፈጸመው ተደጋጋሚ ድርጊት የተበሳጨው ሞተለሚ አሽከሮቹ ያታለሉት እየመሰለው እነርሱን ጨምሮ ለመቅጣት ቢሞክር ወታደሮቹ እኛስ በዚህ ጻድቅ ሰው አምላክ አምነናል በማለት ብስጭቱ እንዲጨምር ያደርጉት ነበር። ቅጣቱ ውጤት ከማስገኘት ይልቅ ወደ ክርስትና የሚገቡ ሰዎች ቊጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ በመሔዱ ንጉሡ ምን እንደሚያደርግ ግራ ተጋባ። በሌላ በኩል ደግሞ ጥቅማቸው የተነካባቸው ማርያን የሚባሉ የጣዖት ካህናት ተክለ ሃይማኖትን በመግደል ተቀባይነታቸውን ለመመለስ ሞክረው ነበር። ነገር ግን ያሰቡት አልተሳካም። ሞተለሚ የማርያን ካህናት የመከሩትን ቢያደርግም የአካባቢውን ነዋሪዎች ወደ ክርስትና ከመግባት፣ ገደል እንዲጣሉ የተፈረደባቸው ሊጥሏቸው የሔዱት ሳይመለሱ ቀድመው ከንጉሡ ፊት እንዲደርሱ ከማድረግ ማገድ አልቻሉም። ድርጊቱ ንጉሡን ይበልጥ ስላበሳጨው ሰውን ሁሉ ወደ ክርስትና እያስገቡ ያስቸገሩትን አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ለመግደል ቢሞክርም አልተሳካለትም።

አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ገደል ጥሎ መግደል አልቻለው ሲል በረጅም ዛፍ ላይ ለመስቀል ቢያስብም ሊሰቅል የወጣው ሰው ከዛፍ ላይ ወድቆ ሲሞት ጻድቁን ግን ዛፏ ዘንበል ብላ መሬት ላይ አስቀምጣቸዋለች። መጨረሻም በጦር ወግቶ ሊገድላቸው ፈለገ። ግን አልተቻለውም። ከዚህ ሁሉ በኋላ ንጉሡ ክርስትና ተነሥቶ ፍስሓ ጽዮን ተብሎ በመሰየም አካባቢው የክርስትና ማእከል ለመሆን በቃ። የማርያን አገልጋይ ካህናተ ጣዖት በእሳት ተቃጥለው፣ በጦር ተወግተው ሞቱ። በክርስቶስ እናምናለን ያሉት ደግሞ አምነው ተጠምቀው የሥላሴ ልጅነትን አገኙ።

ቦታው ጠፍ ሆኖ ከኖረ በኋላ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ኃለ ሥላሴ ቦታውን በጎበኙበት ወቅት የቦታውን ታሪካዊነት ያስረዷቸው በዘመኑ መንኰሰው በአውራጃው ያገለግሉ የነበሩት አባ መልአኩ ነበሩ። ወዲያው መቃኞ ተሠርቶ ጽላት እንዲገባ ቀስ ብሎም ዋናው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ ንጉሠ ነገሥቱ አሳብ አቅርበው እንደ ነበር ይነገራል። አሁን ያለው ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ አገልግሎት መስጠት የጀመረው ግን በ፳፻፰ ዓ.ም መሆኑን በቦታው በተገኘንበት ወቅት አረጋግጠናል።

በአንድ ወቅት አንድ እናት ወንድ ልጅ አርግዛ ሳለ በዚሁ በጦመ ግራር በገዳሙ በኩል ባለው ገደል ወድቃ ምንም ጉዳት ሳይደርስባት ጻድቁ በጥበቃቸው ተራድተዋት ድናለች። ከዚህም በተጨማሪ በቦታው ውኃ ባለመኖሩ ከሩቅ ቦታ በአህያ እየተጫነ ነው የሚመጣው። የገዳማውያንን የውኃ ችግር ለማቃለል በማሰብ በአንድ ወቅት ጉድጓድ ተቆፍሮ ነበር። ጉድጓዱ ከመቆፈሩ በፊት ባለሙያዎች በቦታው በቂ የከርሰ ምድር ውኃ መኖሩን መርምረው አረጋግጠው ነበር። ውኃ በቅርብ መገኘት እንደሚችል ተናግረው ቁፋሮ ቢጀመርም በቀላሉ ውኃ ማግኘት አልተቻለም።

ውኃው ባይገኝም ተቆፍሮ የነበረው ጉድጓድ አልተደፈነም ነበር። አስቀድሞ ገደል ገብታ እንደነበር የተገለጠችው ሴት ምንም ጉዳት ሳይደርስባት እንደተረፈች ሁሉ ልጇ ደግሞ ምሽት ላይ ከአባቱ ጋር እየሄደ ሳለ አባቱ ሳያየው ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ስለነበር ልጁ ቢፈለግ አልተገኘም። በኋላም ከጉድጓድ ውስጥ መውደቁ ታወቀ። ጉድጓዱ በጣም ጥልቀት የነበረው ቢሆንም ልጁ ግን ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስበት ከጉድጓዱ ውስጥ ለመውጣት ችሏል። ልጁ በዚህ ሰዓት በዘመናዊው ትምህርት የዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ መሆኑን ጥቅምት ወር በቦታው በተገኘን ጊዜ መነኰሳቱ ነግረውናል። በመንፈሳዊውም ግብረ ዲቁና ተምሮ ቤተ ክርስቲያኑን በማገልገል ላይ መሆኑን ለመረዳት ችለናል።

በወላይታ ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖትና በጦመ ግራር ምዕራፈ ቅዱሳን አቡነ ተክለ ሃይማኖት የአንድነት ገዳም የሚኖሩት መነኰሳት ከደብረ ሊባኖስ በጣም ይበዙ እንደ ነበር



*የጦመ ግራር ምዕራፈ ቅዱሳን አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንድነት ገዳም*

መነኰሳቱ ይናገራሉ። ለጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሰማይ የወረደላቸው መስቀል ከቦታው ወደ ደብረ ሊባኖስ ከተወሰደ በኋላ ብዙ ነገሮች እየቀነሱ መምጣታቸውንም ይገልጣሉ። የመነኰሳቱ ቊጥር መቀነስ፣ እንደ አጠቃላይ በአካባቢውም የምእመናን ቊጥር መቀነስና የሌላ እምነት ተከታዮች ቊጥር እየጨመረ፣ የቦታው ዕውቅናም እየተቀዛቀዘ መምጣት ከመስቀሉ ወደ ደብረ ሊባኖስ መሄድ በኋላ እንደ ሆነ የጥንት አባቶችና ታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ።

ቦታው ከጠቀስናቸው በላይ ድንቅ ድንቅ ተአምራት የተደረገበት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስደቱ ጊዜ እና ሌሎችም ቅዱሳን የባረኩት ነው። በኅዳር ወር ድርሳነ ዑራኤል ተጽፎ እንደምናነበው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐይቅ እስጢፋኖስ ወደ ጦመ ግራር አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሔዶ ባርኮታል ይባላል። ከሐይቅ ተነሥተው ሲሄዱ ሲሉ ጌታችን መድኃኒታችን ለእናቱ ለድንግል ማርያም ከከንባታ እስከ ዳውሮ ያሉ ተራራዎችን በሙሉ የቃል ኪዳን ተራሮች አድርጌልሻለሁ ብሏታል። በዚህ ጊዜ ቅድስት ድንግል ማርያም እንደ ዋልድባ፣ እንደ ሐይቅ እስጢፋኖስና እንደ ሌሎችም ቅዱሳት መካናት ያንንም ቦታ ለእኔ ከሰጠኸኝ ማየት አለብኝ አለችው። ጌታችንም የእናቱን ጥያቄ ተቀብሎ በእግራችን ሳይሆን በደመና ሄደን እናየዋለን ብሏት በደመና ተጭነው ሄደው ቦታውን አሳይቶ እየዞረ ባርኮታል።

ወደ ቦታው በሄዱ ጊዜ በዚህ ቦታ ወደ ፊት ሊሆን የሚችለውን ስትጠይቀው በንጽሕናው፣ በቅድስናው፣ በድንግልናው እንደ ኤልያስ ንጹሕ፣ ባሕታዊ፣ ደግና ታላቅ የብዙዎች አባት ወደዚህ ቦታ ይመጣል፤ ብዙ ተአምራትንም ያደርጋል፤ በርካታ አሕዛብ በትምህርቱ አምነው የእኔ ተከታዮች ይሆናሉ፤ ቤተ ክርስቲያንም ትሰፋለች ብሎ ነግሯታል። ትምህርታቸውን ጨርሰው ሥራ አጥተው የተቀመጡ ከቦታው ሄደው ጻድቁን አቡነ ተክለ ሃይማኖትን በፅንባና በጸሎት ሲማጸኑ ገና ከቦታው ሳይወጡ በስልክ ተደውሎላቸው ሥራ ተገኝቶላችኋልና እንደ ጨረሳችሁ ተመለሱ እየተባሉ ይጠራሉ። እነርሱም ሄደው ሥራቸውን እንደ ጀመሩ ወደ ገዳሙ ተመልሰው ምስክርነት ይሰጣሉ። እንደ ምሳሌ እነዚህን አነሣን እንጂ ሌላም የቤተሰብም ሆነ የግል ጉዳዩ አስጨንቋቸው ወደ ቦታው ሄደው ጻድቁን ሲማጸኑ በፍጥነት ጸሎታቸው ተሰምቶላቸው፣ ችግራቸው ተወግዶላቸው ውስጣቸው ከኀዘን ወደ ደስታ ተለውጦላቸው የሚሄዱ ብዙ ናቸው።

## በጫካው መኖራቸው ስለሚነገረው ስውራን

በጫካው ውስጥ ስውራን እንዳሉ ይታወቃል። ስውራን የሚባሉት ለሰው የማይታዩ ቅዱሳን ናቸው። ቊጥራቸውንም የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ከምልክቶቹ በመነሣት መናገር ይቻላል። አንዳንድ ጊዜ ድምፃቸው ይሰማል፤ ለአንዳንድ ልበ ንጹሖች ጥርት ያለ የቅዳሴ ድምፅ ይሰማቸዋል፤ መልካም መዓዛ ያላው የዕጣን ሽታ ከጫካው ውስጥ ይወጣል፤ ለአንዳንድ ንጹሓን ነጭ ለብሰው አካባቢውን ሲያጥኑ ከሩቅ ታይተዋል። ሰዎቹ ለመረዳት ፈልገው ሲቀርቡ ይሰወሯቸዋል።

ሌሊት ላይ ብርሃን ሲበራ ይታያል። እነዚህና ሌሎችም በርካታ ምልክቶች ስለሚታዩ ስውራን መኖራቸው የሚያጠራጥር አይደለም። በዚህ ዓመት ጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ጠዋት ጻድቁ ከተወረወሩበት ፏፏቴ ውስጥ በሚገኘው ጫካ ውስጥ እየተዘዋወሩ አካባቢውን ሲያጥኑ መነኰሳት ብቻ ሳይሆኑ በአካባቢው የነበሩ የሌሎች እምነት ተከታዮችም እንዳዩዋቸው መነኰሳቱ ነግረውናል። ተራራው ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተጠቀሱት እና ድንቅ ድንቅ ተአምራት እንደ ተደረገባቸው ምሥጢረ ሥጋዌው እንደ ተገለጠበት እንደ ደብረ ሲና (ዘፀ.፫፣ ፩-፯)፣ ብርሃነ መለኮቱን እንደ ገለጠበት እንደ ደብረ ታቦር (ማቴ.፲፯÷፩-፲፫)፣ ነገረ ምጽአቱን እንደ ገለጠበት እንደ ደብረ ዘይት (ማቴ.፳፬÷፩-፲፬) በርካታ ድንቅ ድንቅ ተአምራት የተገለጡበት ልዩ ተራራ ነው።

## በገዳሙ የተጋረጠው ችግር

**ረኃብ፦** አሁን አሁን እንደ ጥንቱ ችግሩን ተቋቁመው የሚኖሩ መነኰሳት ባለመኖራቸው ገዳሙ ዕድገቱ ብዙ የሚባል አይደለም። መነኰሳቱ በረኃብ ይፈተናሉ። የአየር ንብረቱም ምቹ የሚባል አይደለም፤ የእርሻ ቦታው በጣም ጠባብ በመሆኑ መነኰሳት ለመኖር አይመርጡትም። በመምህርነት ተመድበው የሚሄዱ መርጌቶችም ለተወሰነ ጊዜ እንዳዩት አልተመቸንም ብለው ጥለው እንደሚሄዱ ለመረዳት ችለናል። አልፎ አልፎ ከከተማ መነኰሳቱን ለመጠየቅ የሚሄዱ ሰዎችን እጅ አይቶ መኖር የሚያስቀቅ በመሆኑ በማንኛውም ቦታ የሚኖሩ ክርስቲያኖች

ፕሮጀክት ቀርጸው ከሀገረ ስብከቱ ጋር በመወያየት ለመሥራት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት አለባቸው። ይህን ማድረግ ከተቻለ አካባቢው የክርስተና ማዕከል ወደ መሆን ይመለሳል።

**የምእመናን ቊጥር መቀነስ፡-** አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ በመሆኑ በገዳማውያን ላይ ልዩ ልዩ ችግሮች ያደርሱባቸዋል። አጸደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ተተክሎ የነበረ መስቀል ነቅለው ወደ ገደል ጥለውባቸዋል። መስቀሉን የወረወረው ሰው ተከስሶ ፍርድ ቤት ቢቀርብም ሥልጣን ላይ የሚገኙት በሙሉ ፕሮቴስታንቶች በመሆናቸው መፍትሔ ማግኘት አልተቻለም። በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ በመሆኑ ለገዳማውያን ፈተና ነው። በአካባቢው የሚኖሩ አንዳንድ ኦርቶዶክሶች የመንግሥት ሥልጣን ቢይዙ እንኳ ጫና ስለሚደርስባቸው የሚኖሩት ፈርተው ነው።

**የዕውቀት ክፍተት፡-** በአካባቢው የሚኖሩት ምእመናን ከቍጥራቸው ማነስ በተጨማሪ ሃይማኖታቸውን በሚገባ ያልተረዱ መሆናቸው ሌላው ችግር ነው። ስለሃይማኖታቸው፣ ስለቤተ ክርስቲያናቸው ታሪክ፣ ሥርዓትና ትውፊት የሚያስተምራቸው መምህር አያገኙም። ይህ ሁሉ በሌለበት በሃይማኖት መገኘታቸው ራሱ እንደ ተአምር የሚቈጠር ነው። ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ሲጠየቁ እንዲህ ነው ብለው ከማስረዳት ይልቅ የእናት የአባቶቻችንን እምነት አንለቅም በሚል ብቻ ይዘውት የሚኖሩት ብዙዎች ቢሆኑም ለፕሮቴስታንቱ ጫና በቀላሉ እጅ የሰጡትም ቍጥር ቀላል አይደለም። ብዙዎቹ ወደ ፕሮቴስታንት እምነት ለመቀየራቸው አንዱና ዋናው ምክንያትም ሃይማኖታቸውን እንዲያጸኑ የሚያስተምር ሰው አለመኖሩ ነው።

**የጠበል ቤት አለመኖር፡-** አስቀድሞ እንደ ተገለጠው ጠበሉ ድንቅ ድንቅ ተአምራት ቢያደርግም የጠበል ቤት ስለሌለው በቅርብ አካባቢ የሚኖሩ ምእመናን እየተመላለሱ ይጠመቁበታል እንጂ ከሩቅ መጥቶ በብዙ ደጅ ጽናት ሊገኝ የሚችለውን የእግዚአብሔርን ምሕረት፣ ቸርነትና ፈውስ ማግኘት የሚችለው ክርስቲያን ቍጥር አነስተኛ ነው። በተለይም በክረምት ወቀት መንገዱ እጅግ አስቸጋሪ ስለሆነ ወደ ቦታው የሚሄደው ሰው ቍጥር ይቀንሳል። እንኳን ታመው ለሚሄዱ ለጤነኞችም መንገዱ ፈታኝ ነው። ስለዚህ ቦታው እንዳለው ጸጋና በረከት ሰው ሄዶ ጠበል ተጠምቆ ለመዳን አያበረታታም።

## ከባለድርሻ አካላት የሚጠበቀው ተግባር

**ከሀገረ ስብከት፡-** ለቤተ ክርስቲያን ድርሻ የሌለው አካል ባይኖርም ሀገረ ስብከቱ አሁን ያለውን መነቃቃት አጠናክሮ ቢቀጥል በአካባቢው ያሉትን ክርስቲያኖች በእምነት ከማጽናት በተጨማሪ ሌሎችንም ለማምጣት ይቻላል። አስቀድሞ እንደ ተገለጠው ሀገረ ስብከቱ ሰፋ ያለ መሬት ተቀብሎ ፕሮጀክቶችን አስቀርጾ ሥራ ላይ ማግባቱ መልካም ነው። ፕሮጀክቱን እስከ ታች በማውረድ በጀት መድቦ የአብነት መምህራንን እና ሰባክያንን ቢቀጥር ችግሮች እየቀነሱ ይሄዳሉ።

**ገዳማውያን፡-** ገዳማውያን ለመኖር የሚያስፈልጋቸው ነገር በመጠኑም ቢሆን መሟላት እንዳለበት የሚታመን ቢሆንም የጥንት ገዳማውያን ምንም ዓይነት ምቾት ሳያምራቸው መከራውን ተቋቁመው ቤተ ክርስቲያንንና ገዳማዊ ሕይወትን እንዳስረከቡን ቀደምቶቻችን የዚህ ዘመን መነኰሳትም ምቾትን ከመፈለግና ከአንዱ ገዳም ወደ ሌላው ገዳም ከመዞር አንድ ቦታ ጸንተው በመቀመጥ አጽንኦ በአትን፣ መንፈሳዊ ተጋድሎን ገንዘብ ቢያደርጉና አርአያነትንም ቢያጸኑ ሌሎች ገዳማውያንም ወደ ቦታው ገብተው ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ተግባራትን ያከናውናሉ።

**ምእመናን፡-** መደረግ ያለበትን ሁሉ ከሌላ አካል ሳይጠብቁ ገዳማትን፣ ቤተ ክርስቲያንን፣ የአብነት ትምህርት ቤቶችን መጠበቅ፣ ያልተቋቋመውንም ማቋቋም ይኖርባቸዋል። ይህን የሚያደርጉት ሃይማኖታቸውን በመጠበቅ፣ ዐሥራታቸውን በማውጣት፣ ለቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ልጅ በመስጠት፣ ተተኪ የማፍራት ድርሻቸውን በመወጣት ጭምር ነው።

**ማኅበራት፡-** በዚህ ቤተ ክርስቲያን የተሳተፉትና መልካም ሥራ የሠሩ ማኅበራት የፈጸሙት አርአያነት ያለው ተግባር የሚያስመሰግን ነው። ሌሎች ማኅበራትም እንዲሁ ተሰብስበው እየተወያዩ መልካም ሥራ ሠርተው የጽቅድ አብነት መሆን ይገባቸዋል። ሌሎችም መልካም የሚሠሩትን አሠረ ፍኖት እየተከተሉ ጠያቂ የሌላቸውን የገጠር አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት መጠየቅ፣ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን የሚረከብ ትውልድ ማፍራት ይኖርባቸዋል።

የሚደርሰውን ችግር መቋቋምና የተሻለ ሕይወት መኖር የሚታሰበው ሀገር ሰላም ስትሆን ነው። ሀገር ሰላም ባልሆነበት ይህን ሁሉ ችግር እንኳንስ መቋቋም ማውራትም አይቻልም። እግዚአብሔር በምሕረት ዐይኑ ተመልክቶ ለክፉዎችም ልቦና ሰጥቷቸው፣ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ይቅርታ ተባብሎ በሰላም እንድንኖር ሁላችንም ከመጸለይ በተጨማሪ ሰላማዊ ሰው ለመሆን ወስነን ተግባራዊ ማድረግ አለብን። ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት በቅዳሴዋ "ጸግዋ ሰላመ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ፣ ለታእካ ወለሠራዊታ፣ ወለመኳንንታ፣ወለሕዝባ፡- ለሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ለአንድነቷ፣ ለሠራዊቷ፣ ለመኳንንቷ፣ ለሕዝቧም ሰላምን ስጣት" (ሥርዓተ ቅዳሴ) እያለች ብትጸልይም ይህ ሰላም የሚያስፈልገው ለሁሉ እስከ ሆነ ድረስ ሁሉም ሰላም ያስፈልገኛል ብሎ የየድርሻውን መወጣት አለበት። መንግሥትም በሚዲያ እንደሚነግረን ሁሉ በተግባርም ተገቢውን ሥራ መሥራት አለበት። እግዚአብሔር ለሀገራችን ሰላምን ለሕዝባችን ፍቅርን አንድነትን ያድልልን አሜን።✥

# ሊመጣ ካለው ፈተና ለማምለጥ የእኅት አብያተ ክርስቲያናት አንድነት የሚኖረው ሚና

**ዲ/ን ማለደ ዋሲሁን**

ኢኪዩሜንዝም የሚለው ቃል የዓለም ክርስቲያኖችን አንድነት፣ ኅብረት፣ ጉባኤ፣ ትብብር የሚመለከት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን ስትጀምር ዓለም አቀፋዊት ሆና ነው፡፡ “ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” (ማቴ. ፳፰፥፲፱) በሚለው ትእዛዝ መሠረት ተልእኮ የተቀበለች ናት፡፡

በሂደት ግን የፖለቲካና የብሔርተኞች ሥጋዊ ፍላጎት ቤተ ክርስቲያን አካባቢያዊ አስተዳደር እንድታቋቁም ግድ ብሏታል፡፡ በየሀገሩ ራሱን የቻለ አስተዳደር መመሥረት ሲጀመር ግንኙነቱ እንዲላላ ምክንያት ሆኗል፡፡ ያም ሆኖ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ንጉሥ፣ የሁሉ መድኃኒት የመሆኑ ነገር የእምነት መሠረት በመሆኑ፣ በእምነት የሚመሳሰሉ ራሳቸውን የቻሉ መንበረ ፓትርያርኮች እንደ ገና ዓለም አቀፍ ጉባኤ /ኢኪዩሜንዝም መሠረታዊ ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ መሆኑን ለመጠበቅ ሞክረዋል፡፡

ኢኪዩሜንዝም በባሕርዩ ዓለማቀፋዊ ተግባር ነው፡፡ ዘር፣ ቀለም፣ ባህል ሳይለይ ሁሉን የማቀፍ አገልግሎት ነው፡፡ በዚህ ዓለም ተጋድሎ ላይ ያለች ቤተክርስቲያን ሉዓላዊ ጉባኤ ነው፡፡ ምድር ላይ ያለችው የእግዚአብሔር መንግሥት ጉባኤ ማለት ነው፡፡ ለዓለም ሁሉ መድኃኒት የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ የአገልግሎት አደራ የሰጣት ቤተክርስቲያን ተጠሪ የሆነ ጉባኤ ነው፡፡

በቀደመው የክርስትና ዘመን የነበሩ ሦስቱ ኦርቶዶክሳውያን ጉባኤዎች ማለትም ጉባኤ ኒቅያ፣ ቁስጥንጥንያ እና ኤፌሶን ቀዳማዊ ለቤተክርስቲያን ኢኪዩሜኒዝም ታሪክ ተጠቃሽ ሁነቶች ነበሩ፡፡ በእነዚህ ጉባኤያት ቤተ ክርስቲያንን ሊያጠፉ ከውስጥ ከተነሡ የመናፍቃን ቅሰጣዎች አሐቲ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዋን ለመጠበቅ ጉባኤዎች በማዘጋጀት በውስጧ ተሰግስገው የነበሩትን ኑፋቄያቸውን ለይታ በማውጣት አስቀድማ በማስተማር እንዲመለሱ አድርጋለች፡፡ አንመለስም ያሉትን ደግሞ አውግዛ ለይታለች፡፡ ይህ ድርጊትም ሐዋርያዊ አግልግሎቷ ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ በየጊዜው የሚከሠቱ ፈተናዎች ቤተ ክርስቲያን ወደ ልዩ ልዩ እምነት መሰል ተቋም እንድትከፋፈል ምክንያት ሆነ፡፡ ከእነዚህ ጉባኤያት በኋላ የተፈጠሩ መከፋፈሎች፣ በርካታ ውጣ ውረዶች አብያተ ክርስቲያናት አንድ እንዳይሆኑ /እንዳይሰባሰቡ/ አድርገዋል፡፡

በተለይም የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት በመለካውያን እና በእስልምና መስፋፋት መካካል ከፍተኛ መከራ በማስተናገዳቸው በየራሳቸው ሕመማቸውን ከመሸከም ባለፈ ተገናኝቶ ኅብረት ለመፍጠር የሚያስችል ዕድል አላገኙም፡፡ ተገኘ ቢባል እንኳን፣ በሁለትዮሽ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ፣ አልፎ አልፎ በሚከሠቱ ልዩ ልዩ ሁነቶች አንዱ ከሌላው ጋር የሚገጥመው ትብብር ካልሆነ በስተቀር ሁሉን አቀፍ ጉባኤ የማድረግ ዕድል ሳያገኙ ለዘመናት ተሻግረዋል፡፡

አብያተ ክርስቲያናቱ በጋራ ለመራመድ ያደረጉት ጥረት በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተዳከመ ቢሆንም የግብጽ፣ የኢትዮጵያ እና የኤርትራ አብያተ ክርስቲያናት ከራሳቸው ታሪክ አንጻር እንደ አንድ የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡ የሶርያ እና የሕንድ ማላንካራ አብያተ ክርስቲያናትም ከራሳቸው ታሪክ አንጻር ትስስራቸው የጠበቀ ነበር፡፡ የአርማንያ ደግሞ የተለየ መልክ ነበረው፡፡ እነዚህ ወገኖች ግን ለጋራ አንድነት ያደረጓቸው መነሣሣቶች የዘመናዊ ታሪክ ክስተት እንጂ በየጊዜው ተጠናክሮ የመጣ አልነበረም፡፡ መሠረቱ የተጣለ ሆኖ ሳለ በዘመናት መካከል ግን ትስስሩን ሳይጠብቅ ቆይቷል፡፡ አብያተ ክርስቲያኑ የገጠማቸውን ፈተና በተናጠል ለመወጣት ቢጥሩም ጠንካራ የግንኙነት ሰንሰለት ስለአልነበራቸው ፈተናው ብዙ ችግር አድርሶባቸዋል፡፡

በኋላ ግን የመሰባሰብ ዕድል የተገኘበት፣ በዘመናዊው የታሪክ ዘመን በጋራ የማገልገል ፍንጭ መታየት የጀመረው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተደረገው የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ነበር፡፡ ይህ ታሪካዊ ጉባኤ ግን በተጀመረበት መንገድ ሳይጠናከር አሁንም ድረስ ከሁለትዮሽ ትብብር በዘለለ በሚፈለገው ልክ የተደራጀ እንቅስቃሴ እያደረገ አለመሆኑን መረዳት ይገባል፡፡

### የተወደደ ጊዜ

አሁን ግን ለኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት የተወደደ ጊዜ ነው፡፡ የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት አንድነት አስፈላጊ የሚሆንባቸው አስገዳጅ ሁኔታዎች መጥተዋል፡፡ ዓለም አቀፋዊ ቅርጽ የያዙ፣ በዓለም አቀፍ ኃይሎች የሚመሩ ብርቱ ፈተናዎችም እየመጡ ናቸው፡፡ ኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት እነዚህ ዓለም አቀፍ ፈተናዎች የሁሉም የጋራ ፈተናዎች መሆናቸውን የሚረዱበት የተወደደ ጊዜ አሁን ነው፡፡ ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ውስጣዊ፣ ሌሎች ደግሞ ውጫዊ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ጥልቀትና ስፋታቸው ይለያይ እንጂ ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ግን ፈተናዎች ናቸው፡፡

ውስጣዊ ፈተናዎቹን ለማንሣት እንሞክር፡፡ በቅድሚያ መንጋው የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል በበቂ ሁኔታ እያገኘ አይደለም፡፡ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ፍቅሩ፣ አስፈላጊነቱ ላይ ያለው እምነት

ከፍ ያለ ቢመስልም በሕይወት የማይገለጽበት ሁኔታ ሰፍቷል፡፡ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት መንጋው ልባዊና መዋቅራዊ ሆኖ በመንገዱ አልተሰለፈላቸውም፤ መንጋው በዓለማዊ ወከባዎች ውስጥ እየተዋጠ ወደ አብያተ ክርስቲያናት የሚሔደው ቁጥሩ እየቀነሰ ነው፡፡ አካላዊ መገኘቱ በዲጂታል ቅርጽ መልኩን ለውጦ ቴሌግራም ግሩፕ፣ ፌስቡክ ጓደኝነት ወዘተ ብቻ ወደ መገናኘት እየተቀየረ ነው፡፡ በአብያተ ክርስቲያናት መሰብሰብ ወደ ዲጂታል መሰባሰብ ከጊዜ ጊዜ እየተለወጠ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የምሥጢራት ተሳትፎና ሌሎች መሠረታዊ የክርስትና ሕይወት ተሳትፎዎችን ያዳክማል፡፡ እርስ በእርስ የሚለያዩ ዝንባሌዎች በዝተዋል፡፡

የአብያተ ክርስቲያናቱ ሰዎች የሚሄዱበት አጥቢያ ዘር፣ ቋንቋ፣ ጎጥ፣ ጾታ፣ የመዝሙር ዓይነት፣ የፖለቲካ ዝንባሌ፣ የፖለቲካ መደብ ... ወዘተ እየመረጡ የመታደም ዝንባሌዎች እያደጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች የአብያተ ክርስቲያናትን ውስጣዊ ጥንካሬ እያናጉ ነው፡፡ ምእመናን በራሳቸው መስፈርት ከሚስማማቸው አጥቢያ ጋር መጓዝ ይመርጣሉ፤ አንዱ አጥቢያ ከሌላው የተለየ ዓይነት ይሆናል፡፡ ሃይማኖታዊነትን በመላበስ መንፈሳዊነትን መግፋት ሌላ ፈተና ያስከትላል፡፡ ተገንጥሎ ሌላ አስተዳደር የመፍጠር ዝንሌዎች ማደጋቸው ይታያል፡፡ በአገልጋዮች ዘንድ ሲሞናዊነት እና ምንደኝነት መባባሱ፣ ለዚህ ዘመን ፈተናዎች በሚሰጡ ምላሾችም መለያየት አለመደማመጡ ቀጥሏል፡፡ ማኅበራዊ ብዙኀን መገናኛው ችግሮችን በማባባስና አዳዲስ ችግሮችን በመውለድ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡ ዘረኝነት እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወገንተኝነት ተጽዕኖም እንዲሁ አሳድሯል፡፡ ከማስታረቅ፣ ከማስተባባር፣ ከማቀራረብ ይልቅ በካህናቱ በኩል ወገንተኝነት የመታየት ችግር አለ፡፡

ከፍተኛ የግበረገባዊ ሕይወት መዳከም፣ የግብረ ሰዶማዊነት መስፋፋት፣ የጋብቻ ፍቺ መስፋፋት፣ የሰውን ፈቃደ ሥጋ የሚያነሣሡ ፊልሞች ሥርጭት ማደግ፣ ኃጢአትን ጽድቅ የማድረግ፣ የነገረ ሃይማኖት የሕይወት ትምህርቶችን የመገልበጥ፣ የመከለስ፣ የማደፍረስ፣ የመከለስ ጥረቶች ተጠናክረዋል፡፡ የሃይማኖት ነፃነት በሚል ሰበብ አመካኝቶ ከሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ የራሴን ቤተ ክርስቲያን እመሠርታለሁ ማለት ከግንዱ መቆረጥ መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ ለምእመናን ጥያቄዎችና ልዩ ልዩ ችግሮች ምላስ የመስጠት፣ ሥርዓት የመሥራት ባህል በሲኖዶሶች መዘንጋቱ ሌላው ችግርን ያወሳሰበ ነገር ነው፡፡ በውስጥ ያሉ ጽንፈኛ አመለካከቶች ለአብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት ምክርና ተግሣጽ በር እየዘጉ መምጣታቸው፡፡ ዕውቀትን የማቅለል፣ ዕውቀትን ከልኩም በላይ ወስዶ ፀጉር የመሰንጠቅ ፍላጎቶች ማደግ፣ በቤተ ክርስቲያ አስተዳዳሪዎች/መሪዎችና በምእመናን መካከል አለመተማመን፣ ምእመናን ከክርስቶሳዊ ትምህርት ይልቅ የባህልና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ማስበለጣቸው ...ወዘተ ለአብያተ ክርስቲያናቱ እንደየሚኖሩበት ዐውድ የከበቧቸው ፈተናዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ውስጣዊ ፈተናዎች ከውጪ ከሚመጡባቸው

**ሃይማኖታዊነትን በመላበስ መንፈሳዊነትን መግፋት ሌላ ፈተና ያስከትላል። ተገንጥሎ ሌላ አስተዳደር የመፍጠር ዝንሌዎች ማደጋቸው ይታያል። በአገልጋዮች ዘንድ ሲሞናዊነት እና ምንደኝነት መባባሱ፣ ለዚህ ዘመን ፈተናዎች በሚሰጡ ምላሾችም መለያየት አለመደማመጡ ቀጥሏል። ማኅበራዊ ብዙኀን መገናኛው ችግሮችን በማባባስና አዳዲስ ችግሮችን በመውለድ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው።**

ፈተናዎች ጋር እየተናበቡ እያሠቃዩአቸው ነው፡፡ ውጫዊ ከሆኑት ፈተናዎችም የአክራሪ እስልምና ጫና፣ ኢአማኒነት የመስፋፋት ዘመቻ፣ ዓለምን በኢኮኖሚ የመቆጣጠር የኃያላን ፍትጊያ የሚያስከትለው ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጫና፣ አካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ የፖለቲካ ኃይሎች አሰላለፍና ማኅበረሰቦችን በፈለጉት ባህልና መርሕ የማሳደር ፍላጎት መጨመር፣ የፖለቲከኞች የሃይማኖት ወገንተኝነት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራና ምርምሮች የሚፈጥሩት ማደናበር ወዘተ ለሁሉም ኦሪንታል አብያተ ክርስቲያናት የጋራ ፈተና ነው፡፡

ሰይጣን እነዚህን እና ያልተዘረዘሩ ሌሎች ፈተናዎች ሁሉ በማዝነብ ክርስትናን ከምድር ላይ ለማጥፋትና /የክርስቶስን ጠላት/ሐሳዊ መሲሕን የማንገሥ ዘመቻውን ቀጥሏል፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስን የሚያስክድ፣ አገልግሎታቸውንም የሚያፍን ሥርዓታዊ/መዋቅራዊ ተግዳሮት ገጥሟቸዋል፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር ረድኤት ለአገልግሎታቸው ዕድሜ መራዘም፣ ለመንጋው ተሰብስቦ መቆየት ዋስትና ማግኘት የሚችሉት በአንድነት መቆም እና ኢኪዩሜንዝምን ማጠናከር ሲችሉ ነው፡፡

**መከናወን የሚገባቸው ተግባራት**

**ሀ. መሰብሰብ፡-**

የኦሪንታል አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች መገናኘት፣ መሪዎች ሲሾሙ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ብቻ ተገናኝቶ መለያየት፣ ታላላቅ በዓላትን ተባብሮ ለማክበር የመሪዎች መገባበዝ ብቻ ችግሩን አይፈታውም፡፡ መሠረታዊ በሆነ መንገድ ልባዊ ፍቅር የሞላበት መሰብሰብ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ክርስቶሳዊ ፍቅር ሊኖራቸው ያስፈልጋል አንዱ አንዱን በክርስቲያናዊ ወንድማማችነት ሊፈልግ ይገባል፡፡

**በገጠማቸው ተግዳሮት ላይ መግባባት፡-** ከላይ የዘረዘርናቸው ዓይነት ፈተናዎች ይነስም ይብዛ ኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት የሚጋፈጧቸው ፈተናዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ችግሮቹን እንዴት እንቅረፍ፣ ፈተናዎቹን እንዴት እንለፍ ብሎ ለመተለም በችግሮቹ ስፋትና ዓይነት ላይ መወያየት መግባባት፣ አንዱ የሌላውን ሕመም ማወቅ ያስፈልገዋል፡፡ ከዚያም የጋራ መፍትሔዎች በማስቀመጥ አገልግሎታቸውን ወጥ ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡ መሰብሰብና አንድ ሆኖ ማገልገል የእግዚአብሔርንም ረድኤት ያቀርባል፡፡ ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት በአመዛኙ አናሳ ሆነው በየሀገሮቻቸው የሚኖሩ ስለሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ መተባበሩ ለጥቃት እና ጉዳት ሰለባ የሚሆኑበትን ዕድል ይቀንሳል፡፡

**ለ.ጸሎትና ነገረ ሃይማኖታዊ ውይይቶች፡-**

ነገረ ሃይማኖታዊ ውይይቶች ከዚህ በፊትም ተደርገው እንደሆነ መጠናከር፣ አሁን ደግሞ ከመቼውም ጊዜ በላይ መጠናከር አለባቸው፡፡ በርካታ ሊቃውንትን በዓለማቀፋዊ የኦሪየንታል አብያተክርስቲያናት ነገረ ሃይማኖታዊ ውይይቶች ላይ ለማሳተፍ አብተክርስቲያናት መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ የሊቃውንቱን አቅም እነዚህን ዓለም አቀፍ መድረኮች የሚመጥኑ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ውይይት ብቻ ሳይሆን በጋራ መጸለይ እግዚአብሔርን የሚያስደስትና የመንፈስ ቅዱስን ረድኤት የሚያቀርብ ነው፡፡ የቀደመቺዪቱን አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ኃይል ያላብሳል፤ ፍቅርን ያበዛል፡፡ ምእመናንንም በመላው ዓለም በዚሁ መንፈስ እንዲተያዩና እንዲተባበሩ ያደርጋል፡፡ አንዱ ሌላውን እንዲያውቅና በአገልግሎቱ ደጋፊ አቀላጣፊ በመሆን ፍሬ ለማፍራት ያበቃል፡፡

**ለኢትዮጵያ በተለይ፡-** የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በርካታ ቊጥር ያለው ምእመን ይኑራት እንጂ ምእመናኑ በኢአማንያን የተከበቡ፣ ደሴት ሆነው በፈተና ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተለይም በዚህ ዘመን ለገጠማት ፈተና የአኃት አብያተ ክርስቲያናትን ጸሎትና ድጋፍ ትፈልጋለች፡፡

ምዕራባውያን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ደጎንነት ግድ እንደ ሌላቸው በግልጽ አሳይተዋል፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት ብቻ እንኳን የተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናትን እና የተገደሉ ምእመናንን የተመለከቱ ጉዳዮች ሰሚ እንዲኖራቸው አልፈለጉም፤ እንዲያውም የመከራው ምንጭ የመሆናቸው ምልክት እየታየ ነው፡፡ ባለፉት አርባ ዓመታት የመናፍቃን ቤተ እምነቶች ‹‹ተለይተው በመንግሥት ይመዘገባሉ›› ብለው በየዓመቱ ሪፖርት እያወጡ መንግሥትን የሚገሥጹ ሀገራት ለኦርቶዶክሳውያን ሞት ግን ብዕራቸው አልጻፈም፡፡ አንደበታቸውም አልተናገረም፡፡

አክራሪ እስልምናም የተገኙ የፖለቲካ አለመረጋጋቶችን ሁሉ እንደ ዕድል እየተጠቀመ ክርስትናውን የሚደፍቅበትን ሥልጣንና መዓርግ ለመያዝ እየተጣጣረ ነው፡፡ መናፍቃን “ጊዜው የእኛ ነው” እያሉ ነው፡፡ በእስልምናና በክርስትና መካከል ዳኛ ሆነው ለመታየት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ፖለቲካና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ሁሉ ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖትን ለማዳከም፣ የነበረውን ክብር ለማዋረድ፣ ለመከፋፈልና መንጋውን ለመበተን ይጠቀሙባቸዋል፡፡ አክራሪ ብሔርተኝነት ለቤተ ክርስቲያንም ፈተና ሆኗል፡፡ በኢትዮጵያ ያለው ጦርነትና ግጭት በኦርቶዶክሳውያን መካከል ቂምና ቁርሾ እንዲፈጠር፣ መለያየት እንዲነግሥ እያደረገ ነው፡፡ ሉሎችም በርካታ ፈተናዎች ተደቅነዋል ስለዚህም የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ትብብርና አንድነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን መከራዎች በማቅለል በኩል ሚና ይኖራቸዋል፡፡

በአጠቃላይ የአኃት አብያተ ክርስቲያናት የኢኩሜኒዝም መጠናከር እያንዳንዳቸው አብያተ ክርስቲያናት የሚያጋጥማቸውን ፈተና ለመቋቋም ይጠቅማል፡፡ ሁለተኛም አገልግሎታቸውን ዓለማቀፋዊ አድርጎ የበለጠ ለማሳደግ ይረዳል፡፡ የአብያተ ክርስቲያናት የአስተዳዳር አካላት አንዱ ከሌላው የሚማርበት ዕድል ያገኛል፡፡ ነገረ ሃይማኖታዊ መሠረቶቻቸውን በብርቱ የሊቃወንት ትብብር ያጸናሉ፡፡ የጋራ ቀኖናዊ ጉዳዮች ላይ ይመክራሉ፡፡ የእግዚአብሔርንም በረከት ወደ መንጋው ያቀርባሉ፡፡ ስለዚህ የነገዋ ቤተ ክርስቲያን በዚህ መንገድ የፈጠነ ርምጃ ውስጥ ልትገባ ይገባል፡፡✥

# ከዓይን ጋር የተገባ ቃል ኪዳን

አስፋው ለገሠ

ቤቴን ሳጸዳ መጋረጃውን ወደ ላይ ሰብስቤ እንዳሰርኩት ስለነበር ለጸሎት የለየኂትን ጠባብ ክፍል ሲመለከት ቆይቶ "እንዲህ ዓይነት ሰው አትመስለኝም" ነበር አለኝ። "አልነበርኩም" አልኩት ከማንም የተሰወረ፣ ሰውሬ የምኖረውን ምሥጢሬን ሊያውቅብኝ በመሆኑ ቅር ተሰኝቼ።

"ከመቼ ወዲህ ነው?" አለኝ።

ላስታውሰው ወደ ማልፈልገው ጉዳይ ጥያቄዎቹ እንዳይመሩኝ እየፈራሁ "ትንሽ ቆየ" አልኩት።

"በምን ምክንያት ነው?"

"ባታውቀው ይሻልሃል!"

"ንገረኝ ግድ የለም"

"ስለማይጠቅምህ አልነግርህም"

"ይጠቅመኝ ይሆናል"

"የሚያሳፍር ነገር አለው"

"እኔን እስከጠቀመኝ ድረስ ግድ የለህም አፈር!" በማለት ግድ ካልነገርከኝ አለ።

መቼም ልረሳው የማይገባኝን አንድ ክሥተት እንዲያስታውሰኝ ብዬ በአነስተኛ ካርቶን ላይ አፈር ጨምሬ፣ ከአፈሩ በላይ ክፍት የሬሳ ሳጥን፣ ከሳጥኑ ውስጥ የሚንቀለቀል እሳት፣ እሳቱ ላይ እርቃኑን የተጋደመ የአስከሬን ምስል ሥዬ ለጸሎት ከምቆምበት ቦታ አስቀምጫለሁ። ግድግዳ ላይ ከሚገኘው ሥዕለ አድኅኖ ዝቅ ብሎ፣ አንገቱን ደፍቶ ወለል ላይ ተቀምጦ የሚቆዝም ሥዕል፣ ከሥዕሉ ግርጌ "ነፍሴ ሆይ በልጅቱና በካህኑ ፊት የደረሰብሽን ኀፍረት አትርሺ!" የሚል ጽሑፍ አለ።

አነስተኛ የገጠር ከተማ ሰዓቱ ለዓይን ያዝ ያደርግ ነበር። ተስፋነሽን ከቦኖ ውኃ ልትቀዳ ወረፋ ስትጠብቅ አየኂት። "ደረቅ!" አልኳት በልቤ።

መንገድ ለመንገድ ስለእሷ እያሰብኩ አልፌያት ከቤቴ ገባሁ። ካስቸገሩኝ ጥቂት ሴቶች ተስፋነሽ አንዷ ናት። ረዝማ ያልተንቀዋለለች ቁጤማ፣ ፈገግታ የማይለያት ፈንዲሻ፣ ይህ ቀራት የማትባል ቆንጆ ናት። ጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስታወሻ ጽፌ የሁሉም ትኩረት ያንን መገልበጥ ላይ ሲሆን ጽፌ ያዘጋጀሁትን ደብዳቤ ቀስ ብዬ ደብተሯ ውስጥ እከትላታለሁ። ምላሽ አትሰጠኝም። አንድ ቀን ሰንበት ትምህርት ቤት ቆይታ ከጓደኞቿ ተለይታ ወደ ቤቷ ስትመለስ ጠብቄ አነጋገርኳት።

"ለደብዳቤዬ መልስ ለምንድነው የማትሰጭኝ?" አልኳት በመለማመጥ።

"ዝምታዬ መልስ እንደሚሆን አስቤ ነው"

"በጽሑፍ ምላሽ መስጠት ነበረብሽ"

"እንደዚያ ዓይነት ጥያቄ ከብዙ ልጆች ስለሚቀርብልኝ ለእነዚያ ሁሉ ጽፌ አልችልም። እንዲያዉም በጥያቄዎቹ በመሰላቸት ማንበብ ሁሉ ትቻለሁ"።

"ታዲያ ምን እያደረግሻቸው ነው?"

"የከሰል ማቀጣጠያ"

"በጣም ተጨንቀንና ተጠበን የጻፍነውን ደብዳቤ ታቃጥያለሽ?!" አልኳት በድርጊቷ ተደንቄ።

"አስቀምጬው ምን ይሠራልኛል?"

"አጥፍተሻል። አስቀምጠሻቸው ቢሆን ፈታ ማለት ስትፈልጊ ታነቢያቸው ነበር። ደብዳቤዎቹ ለአንቺ የተደረሱ ውብ ድርሰቶች፣ ግጥሞችና ሥነ ቃሎች ስለሚሆኑ ዘና ያደርጉሽ ነበር" አልኳት በቁም ነገር።

"ነው ብለህ ነው?" አለችኝ።

"ተስፉ" አልኳት በማባበል ዓይን ዓይኗን እያየሁ።

"አቤት ጋሼ"

"ለምን አንደሰትም?"

"ደስታዬ ትእዛዘ እግዚአብሔርን ከመስማት ነው"

"ይህን ዓለም አታስቢውም?"

"አላስበውም አላልኩም"

"ታዲያ?"

"አሁን ጊዜው አይደለም"

"ለአቅመ ሔዋን ደርሰሻል እኮ" አልኳት ቀሚሷን የወጠሩትን ጡቶቿን እያየሁ።

"ይቅርታ ጋሼ አልችልም" አለችኝ።

እያሰለስኩ ተለማመጥኳት።

"አብረን መታየታችን ለስምህ ጥሩ አይሆንም። ለእኔም ቢሆን ከወላጆቼ ጆሮ ከደረሰ ችግር ይፈጥርብኛል" በማለት ልታገኘኝ እንደማትፈልግ ነገረችኝ።

“ለምን እኔ አላስተምርሽም?”

“ወላጆቼ ስላሉልኝ የአንተ እርዳታ አያስፈልገኝም፡፡ እርዳታህን ውለታ መክፈል ሳትሻ ለአቅመ ደካሞች ብታደርገው እጅግ በጣም ታተርፍበታለህ”፡፡

ተለይቻት እራት ወደ ምበላበት ሆቴል ስሄድ በብስለቷ እየተገረምኩ ነበር፡፡ በማግሥቱ “ተስፉ ደጅ ጥናት ሊገድለኝ ነው” አልኳት፡፡

አሁንም ከቤተ ክርስቲያን እየተመለሰች ነበር፡፡ ቆመን ለማውራት አመቺ ስላልነበረ ተከራይታ ወደ ምትኖርበት ቤት አብረን ዘለቅን፡፡

“አልሰማ ብለኸኝ እንጂ ነግሬህ ነበር፡፡ ለአንድ ቀን እንኳ ካለተስፋ ውዬ ማደር አልፈልግም” ትሕትና ያልተለያት ቢሆንም የምትጠቀማቸው ቃላት ጠንካራ ናቸው፡፡ ባቀረብኩላት የፍቅር ግብዣ ደስተኛ አይደለችም፡፡ ሆኖም በዚያን ሁሉ ጊዜ “ጋሼ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ አልችልም!” ከምትለኝ በስተቀር አንድም ክፉ ቃል ወጥቷት አያውቅም፡፡ ምናልባት መንፈሳዊነቷ ተጽዕኖ አድርጎባት ወይም መምህሯ ስለሆንኩ አክብራኝ ይሆናል፡፡ ማክበርስ የምታከብረኝ አይመስለኝም፡፡ በማርክ እንዳልጎዳት ይሆናል እንጂ፡፡

እቤቷ ደርሰን ነበር፡፡ ጉዳዬን መቋጨት ስለነበረብኝ ግባ ብላ እስክትጋብዘኝ ሳልጠብቅ ቀልጠፍ ብዬ ገባሁ፡፡ ከሰል አቀጣጥላ በበራድ ሻይ አፈላችልኝ፡፡ አምባሻ እንድ በላ ብታቀርብልኝ እንደማያስፈልገኝ ገልጬ ሻይ ብቻ ጠጣሁ፡፡ “ይኸው ነው አቋምሽ? ምንም ዕድል አትሰጭኝም?” አልኳት ሻይ ከጠጣሁ በኋላ፡፡

“በትክክል” አለችኝ ቁርጠኝነት በሚደመጥበት አኳኋን፡፡ “ተስፉ ብዙ ጊዜ ደጅ አስጠናሽኝ” አልኳት፡፡ “ደጅ ላስጠናህ ብዬ አይደለም፡፡ ስለማልችል ነው”፡፡ “ምንም አላሳዝንሽም?”፡፡ “በጣም ነው የምታሳዝነኝ፡፡ የማዝንልህ ግን ሌላ ነገር ቀረብህ ብዬ ሳይሆን ስለዘሙት ፍቅር፣ ስለጊዜያዊ ደስታ ብለህ እግዚአብሔርን የሚያክል አምላክና መንግሥተ ሰማያትን የምታክል የተድላ ደስታ ስፍራ ልታጣ በመሆንህ ነው”፡፡ ፈጽሞ ይህን ቃል ከእሷ አልጠብቅም ነበር፡፡

ምንድነው እንደዚህ አድርጎ ካለ ዕድሜያቸው የሚያበስላቸው?! የምመልስላት ቸግሮኝ ዝም ብዬ ዓይን ዓይኗን አያታለሁ፡፡ እሷ በስብከቷ ገፋችበት፡፡ “የእሳት ልጅ አመድ ነው፡፡ ለምን ጭክን ብለህ ንስሓ ገብተህ ይህንን ነገር አትተወውም?” አለችኝ በአጽንዖት፡፡ “አይሆንልኝም” “ይሆንልሃል፡፡ ለምን ራስህን ታሳንፋለህ?”፡፡ “ያልጀመርኩት መስሎሽ ይሆናል”፡፡ በዓለም ውስጥ ሆናችሁ ንጽሕናችሁን ጠብቃችሁ በድንግልና ኑሩ ብለው ሲያስተምሩ አልሰማሁም፡፡ አግብተህ መወሰን ትችላለህ፡፡ መተዳደሪያ በቂ ደመወዝ አለህ፡፡ ለምን አታገባም?”፡፡ “አንቺን ያሰብኩት ለማግባት ነው”፡፡

ተስፉነሽ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ሁለት የትምህርት ዓይነቶችን አስተምራታለሁ፡፡ የዚያን ጊዜ በሁለት የትምህርት ዓይነት የወደቀ ተማሪ አማካይ ውጤቱ ከሰማንያ በላይ እንኳ ቢሆን ወደ አሥረኛ ክፍል መዛወር አይችልም፡፡ “አጠናቋል” ይባልና የመደበኛውን ክፍለ ጊዜ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዕድሉን እስከ መጨረሻው ያጣል፡፡ ይኼ ለእኔ ጠቀሞኛል፡፡ ማባበልና ማማለል ያቃቱኝን ልጃገረዶች ለፈቃዴ አስገዛበታለሁ፡፡ ተስፉነሽ ግን ድርቅ አለችብኝ፡፡ ይባስ ብላም ጓደኛዋን ሰብካ አስከዳችኝ፡፡

ተስፉነሽ አንደኛ ሴሚስተር ላይ እኔ በማስተምራት ሁለቱም ትምህርቶች የማለፊያ ውጤት አላገኘችም፡፡ ሆን ብዬ ነው የጣልኳት፡፡ በዚህ ሴሚስተር ጥሩ የሠራች ቢሆንም እንደ ልማዴ ሰበብ ፈጥሬ ውጤቷን አበላሽሁባት፡፡ በመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ላይ ብዙም አላሳሰባትም ነበር፡፡ አሁን ግን መውደቋ ቁርጥ መሆኑን ስታውቅ፣ የምትጓጓለትን ትምህርት መቀጠል እንደማትችል ስታረጋግጥ አብዝታ ተለማመጠችኝ፡፡ “እሺ በይኝና” አልኳት እኔም በተራዬ ኮራ ጀነን ብዬ፡፡ “አዝናለሁ፣ አልችልም፡፡” ፊቷን አክፍታ፡፡ “ለምንድነው የማትችዪው?”፡፡ “ኃጢአት ነው!!”፡፡ “ከእኛ በላይ ፉጨት ትርፉ አፍን ማሞጥሞጥ!!” አልኳት በድርቅናዋ ተበሳጭቼ፡፡“አልገባኝም”፡፡ “መንፈሳዊ ሕይወትን ብዙዎች ይጀምሩታል እንጂ አይዘልቁትም፡፡ እኔም ብሆን ዲያቆን ነበርኩ”፡፡ “ሽክሜ ቀሊል፣ ቀንበሬ ልዝብ ነው ይላል እግዚአብሔር...”፡፡ “ስለዚህ...”፡፡ “በጾምና በጸሎት ከተጋህ፣ እርዳታውን አብዝተህ የምትሻ ከሆነ የማትሻገረው ወንዝና የማታልፈው መሰናክል አይኖርም”፡፡ “ምን ዓይነት መርዝ መምህር ነው ይህንን ያስተማራት?! እንዴት አድርጎ ቢያስተምራትስ ነው? እንዲህ አድርጎ የሠረጻት?!” ስል አሰብኩ፡፡

“በቃ ይኸው ነው አቋምሽ?”፡፡ “ልረዳህ ባለመቻሌ አዝናለሁ”፡፡ “ዩኒቨርሲቲ ገብተሽ የመማር ዕድልሽን እየዘጋሺው መሆኑን አውቀሻል?”፡፡“ይኼ ለእኔ የተጻፈ ፈተና ከሆነ ሰማዕትነት ነው፤ በአኰቴት እቀበለዋለሁ” አለችኝ፡፡ ባልደግፈውም አቋሟን ሳላደንቅላት አልቀረሁም፡፡ ይህቺን ከምታክል ልጅ እንዲህ ዓይነት ብስለትና ጽናት አልጠብቅም ነበር፡፡ “ምን ተማምና ነው እንዲህ ልበ ሙሉ የሆነችው?” በሚል በወላጆቿ ዙሪያ አጠናሁ፡፡ ወላጆቿ በዝቅተኛ የሥራ ደረጃ ላይ ያሉ በጣም ጥቂት የሚከፈላቸው የድሀ ድሀ ናቸው፡፡ አባቷ ካህን ሲሆኑ ጊዜና ቦታ ስላልገጠማቸው ብቻ ክህነታቸውን ደብቀው የሚኖሩ ደግ ሰው መሆናቸውን ደረስኩበት፡፡ ተስፉነሽ ስለመንፈሳዊነትና አጠቃላይ ቅድስና ሕይወት ሰንበት ትምህርት ቤት የተማረችው ብቻ ሳይሆን ከሕፃንነቷ ጀምረው ወላጆቿ በተለይም ካህን አባቷ ያሳደሩባት ተጽዕኖ እንደ ሆነ ተረዳሁ፡፡

ምንም እንኳን ፍላጎቴ ለዘላቂ ትዳር ባይሆንም የምን ጊዜም ምርጫዬ እንደ እሷ ዓይነት ውብና ያልተነካካች ልጅ ነው። የተማሪዎችን የውጤት ማስተላለፊያ ወረቀት ይዤለሁ፡፡ የሁሉንም ተማሪዎች ውጤት የሞላሁ ሲሆን ምናልባት ትለዝብ እንደ ሆነ ብዬ የተስፉነሽን ክፍቱን ትቼዋለሁ፡፡ ዛሬ ምሽት የመጨረሻ ዕድሌን ለመሞከር አስቤያለሁ፡፡ መኖሪያ ቤቴ ቤቷን አልፎ ነው፡፡ ክፍቱን ነበር፡፡ አካባቢውን ቃኘሁ፡፡ ማንም አልነበረም፡፡

በቀጥታ ወደ ቤቷ አመራሁ፡፡ ውስጥ ሰው አልነበረም፡፡ ዱካ ወንበር ላይ ተቀምጬ እጠብቃት ጀመር፡፡ ቤቷን ቃኘሁት፡፡ ሰፊ ቢሆንም አልጸዳም፡፡ አንድ ኮርነር ላይ አዲስ የእንጨት በር ግድግዳውን ተደግፎ ቆሟል፡፡ እስኪገጠም ድረስ ዝናብ እንዳይመታው ብለው ይሆናል አስገብተው ያቆሙት፡፡

የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ያደረግኩትን አንድ ነገር አስታወሰኝ፡፡ ብዙአየሁ የምትባል ልጅ እንዲሁ እንደ ተስፋነሽ አስቸግራኝ ነበር፡፡ ከጓደኛዋ ጋር ተመካክሬ አከራዮቿ በማይኖሩበት አንድ ቅዳሜ ቀን ልጅቱ ጓደኛዋ ዘንድ እንድትመጣ አደረግኩ፡፡ ሲጫዋወቱ ቆይተው ጓደኛዋ፣ "ጠብቂኝ ሱቅ ደርሼ መጣሁ" አለችና ወጣች፡፡ እኔ በዚያች ቅጽበት ከተደበቅኩበት ቦታ ወጣሁ፡፡ ብዙአየሁ እኔን ስታይ ልትወጣ ተፍ ብላ ተነሳች፡፡ በሩን ለመክፈት ያደረገቺው ጥረት ዋጋ አልነበረውም፡፡ ጓደኛዋ በሩን ከውጭ ቀርቅራባታለች፡፡ በመስኮት ዘላ ለመውጣት ብላ አልጋው ላይ ስትወጣ ደርሼ አነቅኳት፡፡ ብዙ ታገለችኝ፡፡ ሆኖም ከእሷ ይልቅ እኔ ጠንካራ ስለነበርኩ አሸነፍኳት፡፡

የተስፋነሽ ሰውነት ራበኝ፡፡ እንደው ልሞክረው ብዬ እንጂ ብዙም ተስፋ አላደረግኩም፡፡ ልጅቷ አሳብ ግትር ናት፡፡ በብዙአየሁ ያደረግኩትን በተስፋነሽ እንድ ደግመው የሚገፋፋኝ መንፈስ መጣብኝ፡፡ አንድ ስሕተት ብሠራ ለክብሬ እንደማይመጥነኝ አውቃላሁ፡፡ ሆኖም "ካልተዋረዱ እንትን አይገኝም" የሚለው የቆየ ብሂል በአእምሮዬ እየተመላለሰ አስቸገረኝ፡፡

ጥቂት ጊዜ ከራሴ ጋር ስሞግት ቆይቼ ግድግዳውን ተደግፎ ከቆመው ከበሩ ሥር ተደበቅኩ፡፡ የምትተኛበት ሰዓት ረዘመብኝ፡፡ በጊዜ እራቷን አልሠራችም ኖሯል፡፡ ስትንደፋደፍ አመሸች፡፡ እኔን ረኃብ በጥፍራም ጣቶቹ ሆዴን እያመሰኝ እሷ ራቷን በላች፡፡ እንብላ ማለት ባህላችን ነበር፡፡ ሳልጋበዝ የተገኘሁኝ እንግዳ ሆኜ ብቻዋን ጥርግ አድርጋ በላች፡፡ እራቷን ከበላች በኋላ ረጅም ጸሎት ጸለየች፡፡ አልፎ አልፎ አንዳንዶቹን ድምፅ እያሰማች ነበር የምትጸልየው "…ክርስቲያን አድርጊኝ፣ ክርስቲያን ልሁን፣ በክርስቲያን ሥርዓት ጸንቼ ልኑር፡፡… እግዚአብሔር አምላክ ሆይ አንተ የምትከብርበትን ሕይወት እንድኖር እርዳኝ፡፡ አቤቱ ቅዱስ ፈቃድህን መፈጸም እፈልጋለሁ፡፡ ልቦናዬ ትእዛዛትህን ወደ መጠበቅ እንዲያዘነብል አድርግልኝ፡፡ አቤቱ ከፈተና አድነኝ …."፡፡

ይህ ያልሰመረላት፣ ቅድመ እግዚአብሔር ያልደረሰ፣ ጸላኤ ሠናይ ከደመና በታች ያስቀረው ጸሎት እንደ ሆነ እያሰብኩ የምትተኛበትን ደቂቃ፣ የግቢው ሰው ሁሉ ተኝቶ የሚያንኮራፋበትን ሰዓት መጠበቅ ጀመርኩ፡፡ "የማያዛልቅ ጸሎት ትርፉ ቅስፈት" አልኩና ጸሎቷ ከዓላማዬ እንዳያስለውጠኝ ጆሮዎቼን ጠቀጠቅኳቸው፡፡ ሰዓቱ እንደ ማቱሳላ ዕድሜ ረዘመብኝ፡፡ እንቅwልፍ ለምኜ ብለው አንዳንድ አባቶች እንደሚያደርጉት እሷ ራሷ ቆማ የምታድር ቢሆንስ? አሳሰበኝ፡፡ የቄስ ልጅ መሆን ጣጣ ነው፡፡ ተስፋነሽ ረጅም ጸሎት ከጸለየች በኋላ ወደመኝታዋ ሄደች፡፡ ተመስገን ተኛችልኝ፡፡

የሌሊት ልብሷን ልትለብስ ቀን የለበሰቺውን ስታወልቅ ከልብስ የተራቆተ እጅግ በጣም ውብ የሆነውን ተክለ ሰውነቷን አይቼ ቋመጥኩላት፡፡ ይህን ለስላሳ ሰውነት ምናልባትም ከአሁን በፊት የማንም እጆች ደርሰውበት አያውቁም ይሆናል፡፡ ሁለመናዋን በዓይኖቼ ዳሰስኩ፡፡ እፎይ ሥራዬን አቀለለችልኝ፡፡ የሌሊት ልብሷ ስስ ቀሚስ ነው፡፡ ተጠቅልላ ተኛች፡፡ ከአተነፋፈሷ ወዲያው እንቅልፍ እንደወሰዳት ተገነዘብኩ፡፡ ደክሟት ይሆን? "ጀማሪ ክርስቲያን ከጳጳስ ይበልጣል" አሉ፡፡ ጥቂት ተኝታ ደግሞ ለሌት ጸሎት ትነሣ ይሆናል፡፡ መፍጠን ሊኖርብኝ ነው፡፡ የግቢው ሰው በሙሉ መተኛቱን ለማረጋገጥ በበሩና በመስኮቱ ጭላንጭል አጮለቅኩ፡፡ ከአጥር ግቢው ውጭ ከሚያበራው በሩ ላይ ከተሰቀለው አምፖል በስተቀር የተቀሩት መብራቶች በሙሉ ጠፍተዋል፡፡ የሰዓቱን መድረስ እየነገሩኝ ነበር፡፡ ጊዜ አላጠፋሁም፡፡ ልብሴን አወላልቄ ወለሉ ላይ አስቀመጥኩ፡፡ ኡ… ኡ… ድረሱልኝ ማለት እንዳትችል አስቀድሜ አስቤበት ጨርቅ አዘጋጅቻለሁ፡፡ አፏን መጠቅጠቂያ፡፡

ተንቀሳቃሽ ስልኬን አብርቼ ለአፍታ መልከት አደረግኳት፡፡ አልተከናነበችም፡፡ የንጉሥ ሰለሞን ዘር ነን እንደሚሉት አንዳንድ ሰዎች ዓይኖቿ ገርበብ አሉ እንጂ እንዳንቀላፉ ሰው ዓይኖች አልተጨፈኑም፡፡ ዓይኖቿ ትላልቅ ስለሆኑ ይሆን? ወይስ የንጉሥ ሰለሞን ዘር ኖሮባት? ጎንደሬ ስለሆነችና ቤተ እስራኤሎች በጎንደር ይኖሩ ስለነበረ ምናልባት፡፡ ሞባይሌን ልብሴ ላይ ወርውሬ ላዩዋ ላይ ልከመር እርቃኔን ወደ አልጋዋ አመራሁ፡፡ ከአልጋዋ ለመድረስ ጥቂት እርምጃዎች ሲቀሩኝ አንዳች ዓይነት መርዝ በሠራ አካላቴ ተሰራጨ፡፡በአንድ አፍታ ሰውነቴን ልፍስፍስ፣ ድክምክም አደረገኝ፡፡ ጠዋት ስነቃ ወለሉ ላይ ቁጭ ብያለሁ፡፡ እርቃኔን ነው ያለሁት፡፡ የነፍስ አባቷ ቆመው ጸሎተ ማርያም እየጸለዩ እያጠመቁኝ ነበር፡፡

"ምንድነው እየተደረገ ያለው? እዚህ ምን ልሠራ መጣሁ?" ስል ራሴን ጠየቅኩ፡፡ ተስፋነሽ አንድ ጥግ ላይ የጸሎት መጽሐፍ ይዛ በለሆሳስ ስታነብ አየኋት፡፡ አሁን የሆነውን ነገር አንድ በአንድ ማስታወስ ጀመርኩ፡፡ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ስትነሣ በአፍጢሜ ተደፍቼ ብታገኘኝ እንዲያጠምቁኝ ብላ ካህኑን ጠርታቸው ነው፡፡ እንዲያ ሆኜ ስታየኝ በድንጋጤ አልጮኸችም ይሆን? ጮኻ ከሆነ የጎረቤት ሰዎች ምን ገጠማት ብለው መምጣታቸው አይቀሬ ነው፡፡ "ወይኔ ጉዴ!! ገመናዬን የጎረቤት ሰው ሁሉ አውቋል፡፡ እንዴት ብዬ ነው ከእንግዲህ እዚህ አገር የምኖረው? እንዴት ብዬ ነው ተማሪዎች ፊት ቆሜ የማስተምረው?!" ስል አሰብኩ፡፡

የሥነ ምግባርና ሥነ-ዜጋ መምህር መሆኔን ሳስበው የበለጠ ኀፍረት ተሰማኝ፡፡ እኔ ራሴ በተግባር ያልኖርኩትን ትምህርት አስተምራለሁ፡፡ እኔን ብሎ መምህር፡፡ ካህኑ ጠበል አጥምቀው፣ መላ ሰውነቴን በመስቀል ከዳሰሱ በኋላ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያምንና አቡነ ዘበሰማያትን ደገሙልኝ፡፡ እፍረትና ጸጸት እየተፈራረቁ ቀጥቅጠው ራሴን ቀና ማድረግ እንዳልችል አድርገውኛል፡፡ ካህኑ ወደ መኖሪያ ቤታቸው ወስደው መከሩኝ፡፡

ወደ ገጽ ፳፮ ዞሯል

# ነገረ መንፈስ ቅዱስ

***ክፍል ሁለት***

**ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን**

የተከበራችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ማቅረባችን ይታወቃል፡፡ የመጨረሻውን ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

***ሐመር፡- መንፈስ ቅዱስ ማለት የአብ ፍቅር ነው እንጂ ራሱን የቻለ አካል ያለው የባሕርይ አምላክ አይደለም የሚሉ አሉና የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት፣ የባሕርይ አምላክነት የሚያስረዳ በቅዱሳት መጻሕፍት አስረጅነት ተንተን አድርገው ቢገልጹልን?***

***መጋቤ ሐዲስ ኤፍሬም፡-*** *መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ነው፡፡*

*መንፈስ ቅዱስ የአብ ፍቅር ሳይሆን እንደ አብ እንደ ወልድ ፍጹም አካል ያለው የባሕርይ አምላክ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅር የሚኖር ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራል" (፩ዮሐ.፬፥፲፮) ተብሎ እንደ ተገለጠው እግዚአብሔር ማለት ደግሞ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ማለት ነውና፣ እግዚአብሔር አብ ፍቅር ነው፤ እግዚአብሔር ወልድ ፍቅር ነው፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፍቅር ነው፡፡ ይህ ማለት ግን አንዱ አካል ያለው አንዱ ደግሞ አካል የሌለው ማለት ግን አይደለም፡፡ አብም፣ ወልድም፣ መንፈስ ቅዱስም አካል አላቸው፡፡ ሦስቱም የባሕርይ አምላክ ናቸው፡፡ ግን ሦስት አካል፣ አንድ አምላክ ተብሎ ይገለጻል እንጂ አንዱ አካል ያለው ሌላው ደግሞ አካል የሌለው ዝርው ማለት አይደለም፡፡*

*ቅዱስ ያሬድም "ሃይማኖት እንተ እምኀበ አብ ተፈጥረት ኀበ ወልድ ታበጽሕ ኀበ መንፈስ ቅዱስ ትትፌጸም፤ ሃይማኖት አብን አባት ፣ ወልድን ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስን ሠራፂ ብሎ በማመን ትፈጸማለች ጸንታ ትኖራለች" (ድጓ) ይላል፡፡ መንፈስ ቅዱስ አካል የሌለው ፍቅር ሳይሆን አካላዊ የሆነ የባሕርይ አምላክ ነው፡፡ እነርሱ እንደሚሉት የአብ ፍቅር ቢሆን ኑሮ  በአንድ ገጸ ንባብ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ተብሎ ባልተጻፈም ነበር፡፡*

*አካላዊ ለመሆኑ ማስረጃችን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት እና የባሕርይ አምላክነት ምስክር አንዱ ከአብ ከወልድ ጋር በመንፈስ ቅዱስ ስም እንድንጠመቅ መታዘዛችን ነው፡፡ ምክንያቱም "አንተ" ከተባለ አካል ያለው መሆኑ ግልጥ ነው፡፡ አንተ ብለን የምንጠራቸው ነገር ግን አካላቸው ምን አይነት እንደሆነ የማናውቀው ብዙ ፍጡራን አሉ፡፡ ግን አካል የላቸውም ብለን አንናገርም ምክንያቱም "አንተ ፣ እሱ" ብለን ከጠራናቸው አካል ያላቸው መሆኑ የተረዳ ስለሆነ ነው፡፡*

*ጌታችን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር "እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ጰራቅሊጦስ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ እናንተም ትመሰክራላችሁ ከጥንት ጀምሮ ከእኔ ጋር ኑሯልና" ብሏል፡፡ (የሐ.፲፭፥፳፮) እንዲሁም "ያ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ግን ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" በማለት ተናግሯል፡፡ ፲፮፥፲፫) ይህ ሁሉ አካላዊ መሆኑን በአጭሩ ያስረዳል፡፡ "ከጥንት ጀምሮ ከእኔ ጋር ኖሯልና" የሚለውን ወስደን ስንመረምር አብ አካላዊ ነው፤ ወልድም አካላዊ ነው፣ ከአብና ከወልድ ጋር በአንዲት ሥልጣን፣ በአንዲት አገዛዝ፣ በአንዲት ባሕርይ ዘመን ሳይቆጠርለት የኖረው መንፈስ ቅዱስም አካላዊ ነው፡፡*

***መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክ ነው፡-*** *ይህን የሚያስረዳን መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ ተብሎ መገለጹ ነው፡፡ ታላቁ አባት ኢዮብ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ" ሲል ምስክርነቱን ገልጧል፡፡ (ኢዮ. ፴፫፥፬) አምላክ ከአልሆነ እንዴት ፈጣሪ ተባለ? የሚለውን ስንመለከት ልቡናችንን ወደ ጥርጥር ከመክተት ይልቅ በእውነትም የባሕርይ አምላክ ነው ብለን እንድንቀበል ያደርገናል፡፡*

*በመጽሐፍ ቅዱስ "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡" ተብሎ ተጽፏል፡፡ (ሐዋ. ፳፥፳፰) ይህም ፈጣሪነቱን ያስረዳል፡፡ ምክንያቱም ከአብ ከወልድ ጋር ጳጳሳትን ሿሚ መሆኑን ነግሮናልና፡፡ እንዲያውም ክህነትን የመሳሰሉ ረቂቅ የሆኑ ስጦታዎች ሀብተ መንፈስ ቅዱስ፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እየተባሉ ይገለጻሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ አገላለጾች መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር አንዲት ሥልጣን፣ አንዲት ባሕርይ፣ አንዲት ፈቃድ ያለችው የባሕርይ አምላክ መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው፡፡*

*ባጭሩ በቅዱሳት መጻሕፍት ለአብ ለወልድ የተነገረው ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስ ተነግሮ እናገኘዋለን ይህ ደግሞ ፈጣሪነቱን አምላክነቱን በሚገባ ያስረዳል፡፡ ተወዳጁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ይላል፡፡ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን" (፪ቆሮ.፲፫፥፲፫)*

*ከአብ ከወልድ ጋር አስተካክሎ እየነገረን መሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡ አምላክ ባይሆን ኑሮ ከአብና ከወልድ ጋር አስተካክሎ አይነግረንም ነበር፡፡ ደግሞም ጸጋ የሦስቱም ስጦታ ሲሆን ለኢየሱስ ክርስቶስ፣ ፍቅርም የሦስቱም ሲሆን ለአብ ሰጥቶ አንድነትም የሦስቱ ሲሆን ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ መናገሩ ለአብ ለወልድ የሆነው ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስም መሆኑን ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ የሆነው ሁሉ ለአብም መሆኑን፣ ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ የሆነው ሁሉ ለወልድም መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ነው፤ የባሕርይ አምላክም ነው እንላለን፡፡*

***ሐመር፡- መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በእሳት አምሳል ወረደ ይላልና ለምን በእሳት አምሳል ወረደ? በእሳት አምሳል ለሐዋርያት የወረደው በትክክል መንፈስ ቅዱስ መሆኑስ በምን ይታወቃል?***



መጋቤ ሐዲስ ኤፍሬም

**መጋቤ ሐዲስ ኤፍሬም ፦** ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ ለአእምሮ የረቀቀውንና የራቀውን ጉዳይ የተሻለ ቅርብ እንዲሆን በምሳሌ ማስተማር የተለመደ ነው፡፡ነቢዩ ዳዊት "ነገሬን በምሳሌ እጀምራለሁ፤ ከቀድሞ ጀምሮ ያለውን ምሳሌ እናገራለሁ" (መዝ.፸፯፥፪) በማለት እንደተናገረው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በተግባር ያከናወነውንም ሆነ በቃል ያስተማረውን ትምህርት በምሳሌ ገልጾታል፡፡ እንደዚህ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል የወረደበት ምክንያት ምንም እንኳን ምሳሌው የማይተካከል ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውናቸው ተግባራት ከእሳት ተግባራት ጋር የሚያመሳስሉ ጉዳዮች ስላሉት የበለጠ ለአእምሮ ቅርብ ለማድረግ ነው፡፡ የሚያመሳስላቸውን ጉዳይ ለመመልከት ያህል፦

እሳት ረቂቅ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ረቂቅ ነው፡፡ እሳት ኃያል ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ኃያል ነው፡፡ እሳት ያቀረቡለትን ሁሉ ያቃጥላል፤ መንፈስ ቅዱስም የሕዝቡን የአሕዛቡን ጸሎት ይቀበላል፡፡ የአሕዛብን ጸሎት ተቀበለ ማለት ግን ለጣዖት ለአጋንንት የሚቀርብ ልመናን ሳይሆን ከአሕዛብነት የተመለሱትን ጸሎታቸውን የሚቀበል ለማለት ነው፡፡

እሳት በልክ ቢሞቁት ሕይወት ይሆናል፤ መንፈስ ቅዱስም ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስ መሆኑን ያስረዳል፡፡ በእሳት ሸክላ ሠሪ ሸክላዎቿን እየተኮሰች ታጸናበታለች፡፡ ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ፍሩኃን የነበሩ ጥቡዓን ሁነዋል፡፡ እሳት በልክ ከሞቁት ጤና ይሰጣል፤ መንፈስቅዱስም ለክርስቲያኖች ሕይወት ነውና፡፡ ያለ እሳት የሚሠራ ሥራ የለም፤ ያለ መንፈስቅዱስም የሚገኝ ጸጋ የለም፡፡

እሳት ለሥጋዊ ሕይወታችን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስም ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሸክላዎች ሁሉ የሚጸኑት በእሳት ሲተኮሱ ነው፡፡ የሐዋርያትም ሃይማኖታቸው የጸና ያለ ፍርሃት መስበክ የቻሉ መንፈስ ቅዱስ ከወረደላቸው በኋላ ነው፡፡ እሳት የነካው ምግብ ሁሉ ጣዕም አለው፤ መዓዛም አለው፡፡ ጣዕመ ጸጋም የሚገኘው በመንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ነው፡፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰዶምና የገሞራ ሰዎችን በእሳት አጥፍቷቸው ነበርና እሳት ለእጥፋት እንጂ ለምሕረት አልተፈጠረም እንዳይባል ለምሕረትም እንደተፈጠረ ለማስረዳት መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል ወርዷል፡፡

በእነዚህ ከላይ በተዘረዘሩትና በሌሎችም ምክንያቶች መንፈስ ቅዱስ በእሳት ተገልጧል፡፡ ይሁን እንጂ በእሳት አምሳል የታየ ወይም የተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ብቻ አይደለም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እስመ አምላክነ እሳት በላኢ ውእቱ፤ አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ (የሚያቃጥል/የሚባላ) እሳት ነውና፡፡" ይላል፡፡ (ዕብ.፲፩፥፳፱) ፡፡ አባ ሕርያቆስም እሳት ማሕየዊ ለርቱዓነ ልብ ለእለ ይገብሩ ፈቃዶ፤ እሳት በላዒ ለአማፅያን ለእለ ይክህዱ ስሞ፤ ልባቸው ቅን ለሆኑ የሚያድን እሳት ነው፤ ስሙን ለሚክዱ ዐመፀኞች ደግሞ የሚባላ እሳት ነው" ብሎ የገለጸው ሥጋውና ደሙ በእሳት አምሳል ስለሚገለጽ ነው፡፡ (ቅዳሴ ማርያም)

## መንፈስ ቅዱስ መሆኑስ በምን ይታወቃል ለሚለው

አስቀድሞ በተነገረው ቃል ይታወቃል ፡፡ "እርሱም ከእናንተ ጋር ይኖር ዘንድ ሌላ አጽናኝ ይልክላችኋል፤ እርሱም ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ እናንተ ግን ታውቁታላችሁ፤ በእናንተ ዘንድ ይኖራልና፤ ያድርባችሁማልና" ብሏል፡፡ (ዮሐ.፲፬፥፲፮-፲፯) ይህ ቃል መንፈስ ቅዱስ ከመውረዱ አስቀድሞ ሐዋርያት በተስፋ ይጠብቁት ዘንድ የተነገረ ኃይለ ቃል ነው፡፡ አንድም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን ሲያስተምር ወደ አብ እሄዳለሁ ዐርጋለሁ ይላቸው ነበርና እርሱ ትቶን ከሄደ ማን ያጽናናል ማንስ ያስተምረናል እንዳይሉ የሚያጽናናቸው የሚያስጨክናቸው እሳቱንና ስለቱን እንዳይፈሩ የሚያደርጋቸው መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ አስቀድሞ ነግሯቸዋል፡፡ በሉቃስ ወንጌል ፳፬፥፵፱ ስንመለከትም "አንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኀይለ እም አርያም፤ ኃይልን ከአርያም እስክትለብሱ ድረስ እናንተስ በኢየሩሳሌም ተቀመጡ" በማለት አስረድቷቸዋል፡፡ ነቢዩ ኢዩኤልም "ወእሰውጥ መንፈስየ ዲበ ኵሉ ዘሥጋ፤ በሥጋ ለባሽ ሁሉ መንፈሴን አሳድራለሁ" በማለት የመንፈስ ቅዱስን በሐዋርያት ላይ ማደር በትንቢት ቃል ተናግሮታል፡፡

መንፈስ ቅዱስ መሆኑ የሚታወቅበት ሌላኛው ደግሞ ሥራው ነው፡፡ ቋንቋ ሲያናገር ምሥጢር ሲገልጥ ትርጓሜ ሲያስተርጉም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነውና ባናገረው ቋንቋ በገለጠው ምሥጢር ታውቋል፡፡ በእርግጥ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው" በማለቱ ዓለም አምኖ ሊቀበለው ቢቸገር አያስደንቅም፡፡ እርሱን የሚያውቁትና አምነው የሚቀበሉት እንደ ሐዋርያት ጸጋውን የተቀበሉ፣ ቋንቋ የተገለጸላቸው፣ ምሥጢር የተረዳቸው ናቸውና ሥራውን

ተመልክቶ፣ ጸጋውን ተሳትፎ፣ ይልቁንም ከምንም በላይ በጽኑ እምነት ሆኖ ሊቀበሉት ይገባል እላለሁ።

**ሐመር፦ በማቴዎስ ወንጌል ፲፪፥፴፩ ላይ የሰውን ልጅ የሰደበ ኃጢአቱ ይሠረይለታል፤ መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ግን በዚህ ዓለምም ቢሆን በሚመጣው ዓለምም ቢሆን አይሰረይለትም ይላል።**

ሀ. ምን ማለት ነው?

ለ. ይህ አገላለጽ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ይበልጣል አያስብልም ወይ?

ሐ. በዚህ ዓለምም ቢሆን በወዲያኛው ዓለምም ቢሆን የሚለው በዚህ ዓለም ይቅር ያልተባለ በወዲያኛው ዓለም ይቅር የሚባል ኃጢአት አለን? ይህስ መካነ ንስሓ አለ የሚሉ አሉና እንዴት ይታያል?

**መጋቤ ሐዲስ ኤፍሬም፦** በዚህ ጥያቄ ሦስት ያህል መሠረታዊ ነጥቦች ተነሥተዋል። እያንዳንዳቸውን በአግባቡ መመልከት ተገቢ ስለሆነ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ሀ. ወል ድን ቢሰድቡት ሥጋን ተዋሕዶ ስለተገለጠ፣ እንደሰው ሲደክም፣ ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ስላዩት፣ ዕሩቅ ብእሲ ስለመሰላቸው ተሰናክለው ነውና ቢመለሱ ይቅር ይባላሉ ማለት ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በወንጌሉ ሲያስተምር "ወብፁዕ ውእቱ ዘኢተአቅፈ ብየ በኔ ያልተሰነካከለ ብፁዕ ነው" በማለት ተናግሯል። ወልድን ዕሩቅ ብእሲ ለማለት ለከሐዲ ሕሊና ቅርብ ነው ለማያስተውል ልቡናም መብላት መጠጣቱ፣ መድከም መበርታቱ አጠቃላይ ሰው መሆኑን የሚገልጹ ነገሮቹን አይተው የሚሰናከሉ ብዙዎች ስለሆኑ ነው። ኃይለ ቃሉንም የተናገረበት ምክንያት "በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል እንጂ በመንፈስ ቅዱስ አይደለም" ብለው የመንፈስ ቅዱስን የሰይጣን ነው ስላሉ ነው።

ስለዚህ እንዲህ ከሆነ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል መበላለጥን አያስከትልም ወይ የሚለውን ጥያቄ ከማንሣት አስቀድሞ ኃይለ ቃሉ የተነገረበትን አግባብ መመልከት ያስፈልጋልና ምን ማለት ነው ለሚለው ከላይ በተገለጸው መንገድ መረዳት ያስፈልጋል።

ለ. መንፈስ ቅዱስ ከወልድ የሚበልጥ አያስመስልም ወይ? ለሚለው ጥያቄ ግን ከላይ የተሰጠውን ማብራሪያ በቀና መንፈስ ከተመለከቱት ለዚህኛው ጥያቄም መልሱ አያሰኝም የሚል ይሆናል። ምክንያቱም ወልድ በመካከላቸው እየበላ እየጠጣ ነበርና የሚያስተምራቸው አምላክ አይደለህም ቢሉ እንኳን ሰው ብቻ መስሏቸው ባለማወቅ ነው። መንፈስ ቅዱስ ግን "በተዘጋ ቤቱ በተዳፈነ እሳቱ" እንዲሉ አበው ሳያዩት ሰድበውታልና ማለትም ሥራውን የጋኔን ሥራ ነው ብለዋልና እንዲህ አለ እንጂ የሚበልጠው አያስመስልም አይበልጠውምም።

መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ኃጢአቱ አይሠረይለትም ማለትም ሰውን ወደንስሓ የሚመልስ ልቡናን ከኃጢአት የሚለይ መንፈስ ቅዱስ ነውና በሚሰድቡት ሰዎች ልቡና ሊያድር የሚችል አለመሆኑን እርሱ ካላደረባቸው ደግሞ ንስሓ አለመግባታቸውን ንስሓ ካልገቡ ሥርየተ ኃጢአት የማይደረግ መሆኑን ለማሥረዳት እንጅ ንስሓ የማያስተሠርየው ኃጢአት አለ ለማለት አይደለም።

ስለዚህ በመጀመሪያ ንስሓ ከገቡበት ይቅር የማይባል ኃጢአት የለም። ሲቀጥል ደግሞ ኃጢአቱ አግባብ ነው ባይባልም ወደዚያ ኃጢአት ለመግባት ገፊ ምክንያቶች ሲስተዋሉ ለወልድ ምክንያት አለ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ግን ምንም ምክንያት የለም ከማለትና ያለምክንያት ኃጢአትን መሥራት እጅግ የሚያስጠይቅ መሆኑን ለማስረዳት እንጂ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል መበላለጥን ለመፍጠር አይደለም። ምክንያቱም በእነርሱ መካከል መቀዳደም፣ መበላለጥ፣ ስለሌለ ነው።

ሐ. በዚህ ዓለም በወዲያኛው ዓምም አይሠረይለትም። ሲል ይህ አነጋገር መካነ ንስሐ አለ ወይ? ወደሚል አስተሳሰብ ሊወስድ በፍጹም አይችልም። ምክንያቱም "እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት በሰማይም የታሠረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈቱት በሰማይ የተፈታ ይሆናል" ከሚለው ጋር አንድ አይነት ነው።

በዚህ ዓለም ንስሐ ገብቶ ኃጢአቱ ከአልተሠረየለት በወዲያኛው ዓለምም አይሠረይለትም ማለት ነው። ንስሐ ገብቶ መጽደቅ የሚቻለው በወዲሁ ዓለም ነው ለማለት ነውና። በዚህ ዓለም ሲኖሩ ሃይማኖትን አጽንቶ፣ በጎ ምግባር ሠርቶ፣ ንስሓ ገብቶ፣ ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ መኖር ካልተቻለ ሃይማኖትን የሚያጸኑበት፣ በጎ ምግባር የሚሠሩበት፣ ንስሓ የሚገቡበት፣ ምጽዋት የሚመጸውቱበት ሌላ ዓለም አለ ማለት አይደለም። ስለዚህ በዚህ ዓለምም በወዲያኛው ዓለምም ሲል በዚህ ዓለም ይቅር ያልተባለ ኃጢአት ሰማያዊውን ዓለም ፣ መንግሥተ ሰማያትን አያስወርስም፣ ለማለት ነው።

**ሐመር፦ በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነጥብ ካለ**

**መጋቤ ሐዲስ ኤፍሬም፦** በአጠቃላይ የምሥጢረ ሥላሴ፣ የምሥጢረ ሥጋዌ፣ የነገረ መንፈስ ቅዱስ ጉዳይ እንዲህ በአጭሩ ተገልጾ አያልቅም። ይሁን እንጂ ምእመናን በጽኑ ሃይማኖት ላይ ቆመው ግልጽ ያልሆነውንም ነገር ከሊቃውንቱ ቀረብ እያሉ በመጠየቅ፣ እንዲሁም ሆኖ ግልጽ ካልሆነ ጸሎት እያደረጉ ለራሱ ለመንፈስ ቅዱስ እየሰጡ ማለፍ ተገቢ ይሆናል እንጂ አንድ ኃይለ ቃል ባገኙ ቍጥር ወደአልተፈለገ ምርምር የሚሄዱ ከሆነ እንደነ አርዮስ፣ እንደነ መቅዶንዮስ፣ እንደነ ንስጥሮስ የከፋ አወዳደቅ ይወድቃሉ። ስለዚህ በጥንቃቄ መጓዝ ያስፈልጋል።

**ሐመር፦ጥሪያችንን አክብረው ላነሣናቸው ጥያቄዎችም ተገቢውን መልስ ስለሰጡን እናመሰግናለን።**

**መጋቤ ሐዲስ ኤፍሬም፦** እኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።✥